# ❦መጽሐፈ ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ❦
# በግእዝና በአማርኛ




አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ መምህር)


ሐምሌ ፳፯፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም

# ድጓ ዘዮሐንስ

## 💗መቅድመ ድጓ💗

ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዓለም ከሚታወቁባቸው በርካታ ድንቅ ነገሮች አንዱ የቅዱስ ያሬድ አክሱማዊ ዜማ ነው። የቅዱስ ያሬድ ዜማ በዮዲትና በግራኝ አማካኝነት በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ላይ በደረሰው ስደትና ሞት ምክንያት መጠነኛ ለውጥ ተከሥቶበታል። በተከሠተው ስልተ ድምፅ ምክንያት የአጫብር፣ የቤተልሔም፣ የቆማ፣ የወንጨር፣ የተጉለት ዜማ እየተባለ ተለይቷል። የአጫብር ድጓ የምስክር መምህር ስያሜው ሊቀ ማእምራን ሲሆን የቤተልሔም ድጓ ምስክር መምህር ደግሞ ስያሜው ሊቀ ምሁራን ነው። ድጓ የሚለው ቃል ጓ ሲላላ የቤተክርስቲያን ትጥቋ መቀነቷ ማለት ነው። በትግርኛ ድጓዕ ማለት መዝሙረ ኀዘን ሰቆቃው (ሙሾ) ማለት ነው። ድጓን የደረሰው ቅዱስ ያሬድ ነው። የቅዱስ ያሬድ አባቱ አዳም፣ እናቱ ታውክልያ ይባላሉ። ሚያዝያ 5 ቀን በ505 ዓ.ም በአክሱም ከተማ ተወለደ። የቅዱስ ያሬድ የዘር ሐረግ አለቃ ልሳነ ወርቅ በጻፉት ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘቅዱስ ያሬድ እንደሚከተለው ይገልጹታል። በእስራኤል ሀገር ከነበረው ከሊቀ ካህናቱ ከሳዶቅ እንደሚመዘዝ ይገልጻሉ። በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ነው።

1. ሊቀ ካህናት ሳዶቅ
2. አዛርያ
3. ሳዶቅ
4. ሌዊ (በግዑ)
5. ሕዝበ ራእይ
6. ሕዝበ ዋሂ
7. አኪን
8. ስምያን
9. እንበረም
10. ኢታምር
11. አብዩድ
12. ታውክልያ

13. ያሬድ

ቅዱስ ያሬድ ከእናቱ ወንድም (ጌዴዎን) ሲማር ትምህርት አልገባው አለ። በዚህ ምክንያት መምህሩ ጌዴዎን ስለሚቆጣውና ስለሚገርፈው መታገሥ ተስኖት ከወላጆቹ ቤት ወጥቶ ማይ ኪራህ ወደምትባል ቦታ ሄዶ ተደበቀ። ያሬድ በተደበቀበት ቦታ ወደ አንዲት ዛፍ ሥር ተጠግቶ እያለቀሰ ሳለ አንድ ትል አየ። ትሉም ወደላይ እወጣለሁ እያለ ከማዕከሉ ሲደርስ ይወድቅ ነበር። እንደዚህ እየሆነ ለስድስት ጊዜያት ያህል በተደጋጋሚ ሲወጣና ሲወርድ ከቆየ በኋላ በሰባተኛው ትሉ ከዛፍ ላይ ወጥቶ የዛፉን ፍሬና ቅጠል መብላት ሲጀምር ተመለከተ። ይህን ተመልክቶ ወደ መምህሩ ተመልሶ ተማረ። በአጭር ጊዜም መጻሕፍተ ብሉያትን መጻሕፍተ ሐዲሳትን ተማረ። ድጓ በአራት ትልልቅ ክፍሎች ይከፈላል። እነዚህም ድጓ ዘዮሐንስ፣ ድጓ ዘአስተምሕሮ፣ ድጓ ዘፋሲካ፣ ጾመ ድጓ ናቸው። የእያንዳንዱ ወቅት ስያሜ እንደሚከተለው ነው።

፩. ዘመነ ዮሐንስ (ከመስከረም 1-7)

፪. ዘካርያስ (መስከረም 8)

፫. ዘመነ ፍሬ (ከመስከረም 9-15)

፬. ዘመነ መስቀል (ከመስከረም 16-25)

፭. ዘመነ ጽጌ (ከመስከረም 26- ኅዳር 5)

፮. ዘመነ አስተምሕሮ (ከኅዳር 6- ታኅሣሥ 6)

፯. ዘመነ ስብከት (ጀማሬ ከታኅሣሥ 7-13)

፰. ዘመነ ብርሃን (ከስብከት መጨረሻ ጀምሮ)

፱. ዘመነ ኖላዊ (ከብርሃን መጨረሻ ጀምሮ)

፲. ዘመነ መርዓዊ (ታኅሣሥ 27)

፲፩. አማኑኤል (ታኅሣሥ 28)

፲፪. ዘመነ ልደት (ከታኅሣሥ 29- ጥር 9)

፲፫. ናዝሬት (ከጥር 7-9)

፲፬. ገሐድ (ጥር 10)

፲፭. ዘመነ ጥምቀት (ከጥር 11- ጾመ ነነዌ)

፲፮. ዘመነ መርዓዊ (ከዐቢይ ጾም በፊት ሳምንቱ)

፲፯. ዘመነ ጾም (ከዐቢይ ጾም እስከ ትንሣኤ)

፲፰. ዘመነ ትንሣኤ (ከትንሣኤ እስከ ዕርገት)

፲፱. ዘመነ ዕርገት (ከዕርገት እስከ ጰራቅሊጦስ)

፳. ዘመነ ጰራቅሊጦስ (ከጰራቅሊጦስ-ሰኔ 16)

፳፩. ዘመነ አስተምሕሮ (ከሰኔ 17-25)

፳፪. ሰኔ 26-ሐምሌ 18 (ደመና፣ ዘርዕ፣ ዝናም

፳፫. ሐምሌ 19-ነሐሴ 9 (መብረቅ፣ ባሕር..)

፳፬. ነሐሴ 10-27 (ዐይነ ኵሉ፣ዕጐለ ቋዓት...)

፳፭. ነሐሴ 28-ጳጕሜን 5 (ጎሕ፣ ነግሕ፣...)

ይዘመራሉ። አስተምሕሮ ማለት ይቅር ማለት፣ ይቅርታን ከፈጣሪ ዘንድ መጠየቅ መማለድ ሲሆን ዘመነ አስተምሕሮ ማለት የይቅርታና የምሕረት ዘመን እንዲሁም የምሕላ ዘመን ማለት ነው። አስተርእዮ ማለት ደግሞ መገለጥ ማለት ነው። ዘመነ አስተርእዮ ማለት እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም በግልጥ በሰዎች መካከል እየተመላለሰ የታየበት ዘመን ማለት ነው።

## ድጓ ዘዮሐንስ

(ቅዱስ ያሬድ ባማረ የቋንቋ አገላለጽ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጠቀሰውን ትምህርት ይገልጻል። ቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅሳቸው ጥቅሶች ብዙ ናቸው። ልዩ አገላለጽ ያላቸውን ብቻ እየለየን እናቀርባለን። ትርጉሙ ቃል በቃልና አልፎ አልፎ ደግሞ ዐውድ ተኮር ነው)።

## ❖ነገረ ክርስቶስ

ቅዱስ ያሬድ ዮሐንስ መጥምቅን ጠቅሶ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት፣ ፀሐይ፣ ንጉሥ፣ ብርሃን፣ ቸር፣ ቃል፤ ሊቅ እያለ ባማረ ሥነ ጽሑፉ ገልጾታል። ቀጥታ ወደሊቁ አገላለጽ እንሂድ።

**ነገረ ክርስቶስ፦** ዮሐንስ መጥምቅ ክርስቶስን ባየው ጊዜ እነሆ [የእግዚአብሔር] በግ አለ። ካህን ዮሐንስ ብርሃን ክርስቶስን ባየ ጊዜ እነሆ [የእግዚአብሔር] በግ አለ። ሰማዕት ዮሐንስ ሕይወት ክርስቶስን ባየው ጊዜ እነሆ [የእግዚአብሔር] በግ አለ። መምህር ዮሐንስ ንጉሥ ክርስቶስን ባየው ጊዜ እነሆ [የእግዚአብሔር] በግ አለ። ድንግል ዮሐንስ ክርስቶስ ቃልን ባየው

ጊዜ እነሆ [የእግዚአብሔር] በግ አለ። የተመረጠ ዮሐንስ ፀሐይ ክርስቶስን ባየ ጊዜ እነሆ [የእግዚአብሔር] በግ አለ። መምህር ዮሐንስ ቸር ክርስቶስን ባየ ጊዜ እነሆ [የእግዚአብሔር] በግ አለ። (#በግእዝ፦ ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ መጥምቅ ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ሊቅ። ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ ካህን ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ብርሃን። ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ ሰማዕት ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ሕይወት። ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ ሰንኮሪስ ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ንጉሥ። ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ ድንግል ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ቃል። ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ ኅሩይ ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ፀሐይ። ነዋ በግዑ ይቤ ዮሐንስ መምህር ሶበ ርእዮ ለክርስቶስ ኄር)።

**ቤተክርስቲያን፦** ቤተክርስቲያን ወደ ዮሐንስ ክርስቶስ አንተ ነህን ስትል አሰምታ ተናገረች። እርሱን እኔስ ክርስቶስን አይደለሁም አላት። (#በግእዝ፦ ጸርሐት ቤተክርስቲያን ኀበ ዮሐንስ ወትቤሎ አንተኑ ክርስቶስ ወይቤላ አንሰ ኢኮንኩ ኪያሁ)

**●ዮሐንስ መጥምቅ●፦** ዮሐንስ ሆይ ንዑድ ክቡር ነህ። መታሰቢያህ በርእሰ ዐውደ ዓመት ተጻፈ። በረከትህን እነሣ ዘንድ ባርከኝ። [እግዚአብሔር] ሰላምን እሰብክ ዘንድና በውሃ አጠምቅ ዘንድ [እኔን ዮሐንስን] ላከኝ። ጌታውን መራ ወደ ዮርዳኖስም አደረሰ በዚያም ዮሐንስ ፈጽሞ ተደሰተ። መካን ኤልሳቤጥ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ጌታውን ያወቀ ድንግል ዮሐንስን ወለደች። ዮሐንስ ኢየሱስን በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቀው። ወንጌላዊና ክቡር የሆንክ ዮሐንስ ሆይ የሙሽራው ክርስቶስ ሚዜና በሥጋ ደግሞ ዘመዱ ተባልክ። በገዳም የሚናገር፣ ልባቸው ሰነፍ የሆኑ ሰዎችን በመንፈስ ብልህ የሚያደርግ፣ መምህር ክርስቶስን ያጠመቀ ካህን ዮሐንስ በእውነት ከመላእክት ይበልጣል። ዮሐንስ ሆይ የግንብ ቤቶችን ንቀህ በሰማያት ያለ ቤትን በማሰብ ልብስህን የግመል ጸጉር አደረግህ። ዮሐንስ ስለብርሃን ሰማዕት ይሆን ዘንድ መጣ። የእውነት ብርሃን የተባለውም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (#በግእዝ፦ ብፁዕ አንተ ዮሐንስ። ውስተ ርእሰ ዐውደ ዓመት ተጽሕፈ ተዝካርከ። ባርከኒ እንሣእ በረከተከ። [ይቤ ዮሐንስ] ፈነወኒ ኪያየ እስብክ ሰላመ ወአጥምቅ በማይ። እግዚኡ መርሐ ዮርዳኖሰ አብጽሐ ወበህየ ዮሐንስ ፍጹመ ተፈሥሐ። መካን ተበኵረት ዮሐንስሀ ድንግለ እምከርሠ እሙ እግዚኡ ዘአእመረ። አጥመቆ ዮሐንስ ለኢየሱስ በፈለገ ዮርዳኖስ። ዮሐንስ ክቡር ወንጌላዊ ገዳማዊ አርኩ ለመርዓዊ ወአዝማዱ በሥጋ ተሠመይከ። በገዳም ነባቢ፣ አብዳነ ልብ በመንፈስ አጥባቢ፣ ዮሐንስ ካህን ዘአጥመቀ ረቢ፣ አማን እመላእክት የዐቢ። አብያተ ዘውቅሮ መኒነከ በተዘክሮ ማኅደር ዘበሰማያት ጸጕረ ገመል ረሰይከ አራዘከ። ዮሐንስ መጽአ ሰማዕተ ይኩን በእንተ ብርሃን ወብርሃነ ጽድቅሰ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ)።

## መስከረም ፪ ወዘተከዚ

**❦ነገረ ክርስቶስ❦፦** ለሁሉ የሚያበራ የእውነት ፀሐይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ ዮሐንስን በውሃ አጥምቀኝ አለው። ዮሐንስም ኢየሱስን [አንተን] ማጥመቅ እንዴት ይቻለኛል አቤቱ አንተን ምን ውሃ ይሸከምሀል አለው። ኢየሱስም ዮሐንስን እኔ ካልተጠመቅሁ ውሃ አይቀደስም አለው። ዮሐንስም ኢየሱስን አጠመቀው። [ሲያጠምቀውም] በኢየሱስ ራስ ላይ ውሃዎች ፈሉ።

በጥምቀቱ ውሃ ተቀደሰ:: የእርሱንም የምስጋናውን ክብር አየን:: በዮርዳኖስ ወንዝ ያጠምቀው ዘንድ ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ዮሐንስ ሔደ:: (#በግእዝ፦ ፀሐየ ጽድቅ ዘያበርህ ለኵሉ ክርስቶስ:: ይቤሎ ኢየሱስ ለዮሐንስ አጥምቀኒ በማይ:: ይቤሎ ዮሐንስ ለኢየሱስ እፎኑ እክል አጥምቆተከ ዓይኑ ማይ እግዚኦ ይጸውረከ:: ይቤሎ ኢየሱስ ለዮሐንስ ኢይትቄደስ ማይ ለእመ ኢተጠመቁ አነ:: አጥመቆ ዮሐንስ ለኢየሱስ ፈልሐ ማያት ዲበ ርእሱ ወተቀደሰት ማይ በጥምቀቱ ወርኢነ ብዕለ ስብሐቲሁ:: ሖረ ኢየሱስ እምገሊላ ኀበ ዮሐንስ ከመ ያጥምቆ በፈለገ ዮርዳኖስ)::

**❁ሰማዕት❁፦** ሰማዕት ወደርስታቸው [ወደ መንግሥተ ሰማያት] ተሻገሩ:: በብዙ ትዕግሥት ጌታቸውን [እግዚአብሔርን] ደስ ያሰኙት ሰዎች በሰላም ወደ ሀገራቸው [መንግሥተ ሰማያት] ገቡ:: ጸሎታቸውን ሰማቸው ሰማዕት ተስፋቸውን አገኙ:: [በመልካም] ተጋድሏቸውና በትዕግሥታቸው ሰማዕት ተስፋቸውን አገኙ:: ሕግህን የሚጠብቁና በልጅህ በክርስቶስ የታመኑ ተስፋቸውን አገኙ:: ምድርንም [መንግሥተ ሰማያትንም] በደማቸው ገንዘብ አደረጉ:: (#በግእዝ፦ ዐደዉ ሰማዕት ውስተ ርስቶሙ:: በሰላም ቦኡ ሀገሮሙ እለ አሥመርዎ ለእግዚኦሙ በብዙኅ ትዕግሥት:: ሰምያሙ ጸሎቶሙ ሰማዕት ረከቡ ተስፋሆሙ:: በገድሎሙ ወበትዕግሥቶሙ ሰማዕት ረከቡ ተስፋሆሙ:: ለእለ የዐቅቡ ሕገከ ወነሥኡ ተአሚኖሙ ክርስቶስሀ ወልደከ አድምዑ ተስፋሆሙ ተሣየጡ ምድረ በደሞሙ)::

**❃ካህናት❃፦** መልካም አገልግሎትን ለሚያገለግሉ ለካህናት እጥፍ ክብር ይገባቸዋል:: ዐይን ያላየውን ጆሮም ያልሰማውን [መንግሥተ ሰማያትን] ይሰጣቸዋል:: ሀገርም በጸሎታቸው ትጠበቃለች:: የእስራኤል አምላክ ታቦት መሪ ሆናቸው ካህናት [ዮርዳኖስን] ተሻግረው በምድረ ከነዓን ሁሉ ተመላለሱ:: የብርሃን ልጆች ካህናት ንዑዳን ክቡራን ናቸው:: በሃይማኖት ከጦርነት ዳኑ:: (#በግእዝ፦ ለካህናት ለእለ ይትለአኩ ሠናየ መልእክተ ምክብዒተ ክብር ይደልዎሙ:: ዘዐይን ኢርእየ ወእዝን ኢሰምዐ የዐሥዮሙ:: ወትትዐቀብ ሀገር በጸሎቶሙ:: ዐደዉ ካህናት ወአንሶሰዉ ውስተ ኵሉ ብሔረ ከነዓን:: ታቦተ አምላከ እስራኤል መርሐ ኮነቶሙ:: ብፁዓን እሙንቱ ካህናት ውሉደ ብርሃን በሃይማኖት ድኅኑ እምኲናት)::

**✿ዮሐንስ መጥምቅ✿፦** በዮርዳኖስ በውሃ ያጠምቀው ዘንድ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ካህን በማድረግ ዮሐንስን እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አደረገው:: ዮሐንስ ኢየሱስን በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቀው:: ሰንበትን የቀደሰ [የክርስቶስን] የማትዳሰስ ራሱንም ዳሰሰው:: ዮሐንስ ከሌሎች [ነቢያት] በበለጠ የአብ ቃል ከሰማይ ወረደ እያለ ነገርን [ትንቢትን] ተናገረ:: የዮርዳኖስ ወንዝ ከመለኮት ግርማ የተነሣ ታወከ:: ዮሐንስ [ክርስቶስን] ካጠመቀ በኋላ ራሱ ተጠመቀ:: (#በግእዝ፦ አዕበዮ እግዚአብሔር ለዮሐንስ እምከርሠ እሙ ካህነ ረሰዮ ከመ ያጥምቆ በማይ በዮርዳኖስ:: አጥመቆ ዮሐንስ ለኢየሱስ በፈለገ ዮርዳኖስ ወገሠሦ እንተ ኢትትገሠሥ ርእሶ ለዘቀደሳ ለሰንበት:: ዮሐንስ አኀድአ እምካልኣኒሁ አንሀ ወክሐ እንዘ ይብል እምላዕሉ ወረደ ቃለ አብ ወተሐውከ ማየ ዮርዳኖስ እምግርማ መለኮት:: እምድኅረ አጥመቀ ለሊሁ ተጠምቀ)::

## ❖ዘዘወትር❖

**ነገረ ክርስቶስ፦** ሰማያዊ ጌታ በመሬታዊ [ዮሐንስ] እጅ ተጠመቀ፡፡ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ያጠመቀውን ክርስቶስን እናምናለን፡፡ ኢየሱስ ዮሐንስን ውሃ ተቀድሶ ለሰው ልጆች መድኀኒት ይሆን ዘንድ በውሃ አጥምቀኝ አለው፡፡ ዮሐንስም ሌላውን ሳጠምቅ በስምህ አጠምቃሁ አንተን በማጠምቅ ጊዜ አቤቱ ምን እላለሁ አለው፡፡ [ጌታም] ብርሃንን የሚገልጥ የቡሩኩ የአብ ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ ይቅር በለኝ በል አለው፡፡ ዮሐንስ ኢየሱስን እንዳጠመቀው እናምናለን፡፡ (#በግእዝ፦ ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ መሬታዊ፡፡ ነአምን ክርስቶስሀ መድኀኒ ዘዮሐንስ አጥመቆ በዮርዳኖስ፡፡ ይቤሎ ኢየሱስ ለዮሐንስ አጥምቀኒ በማይ ከመ ይትቀደስ ማይ ወይኩን መድኀኒተ ለውሉደ ሰብእ፡፡ አበዮ ዮሐንስ ወይቤሎ ባዕደ ሶበ አጠምቅ በስምከ አጠምቅ ወኪያከ ሶበ አጠምቅ እግዚኦ ምንተ እብል፡፡ ወልዱ ለቡሩክ ከሣቴ ብርሃን ወልደ እግዚአብሔር ተሣሀለኒ በል፡፡ ነአምን ከመ አጥመቆ ዮሐንስ ለኢየሱስ)

**ዮሐንስ መጥምቅ፦** ብርሃንን የምትሰብክ ሰማዕት ዮሐንስ ሆይ ጸሎትህ መድኀኒትና መጠጊያ ይሁነን፡፡ ከፈተናም ያድነን ይርዳንም፡፡ ቅዱሳት እጆችህ ሰማያዊ ሙሽራን ያጠመቁ ዮሐንስ ሆይ ንዑድ ክቡር ነህ፡፡ ዮሐንስ ከነቢያት በኋላና ከወልድ መምጣት በፊት የኃጢአታቸውን ቤዛ በውሃ አጠምቅ ዘንድ ተላክሁ ብሎ አሰምቶ ተናገረ፡፡ ከፍ ብሎ የሚበር ከሌዊ ወገን የተወለደ ካህንና ነቢይ ብርሃንን የሚሰብክ ዮሐንስ በውሃ ያጠምቅ ዘንድ ተላከ፡፡ የሙሽራው ሚዜ የተከበርክ ዮሐንስ ሆይ መምጣቱን ትናገር ዘንድ ቃል ላከህ፡፡ (#በግእዝ፦ ሰባኬ ብርሃን ዮሐንስ ሰማዕት ጸሎትከ መድኀኒት ፀወነ ይኩነነ ይርድአነ ወያድኅነነ እመንሱት፡፡ ብፁዕ አንተ ዮሐንስ እደዊከ ቅዱሳት እለ አጥመቃሁ ለመርዓዊ ሰማያዊ፡፡ ጸርሐ ዮሐንስ ወይቤ ድኅረ እምነቢያት እምቅድመ ምጽአተ ወልድ አነ ተፈኖኩ ቤዛ ኀጢአቶሙ አጥምቅ በማይ አንሰ ተፈኖኩ፡፡ ዘእምነገደ ሌዊ ካህን ወነቢይ ዮሐንስ ክቡር ዘልዑለ ይሠርር ተፈነወ ያጥምቅ በማይ ሰባኬ ብርሃን፡፡ ዮሐንስ ክቡር አርኩ ለመርዓዊ ምጽአቶ ትዜኑ ፈነወከ ቃል)፡፡

**ትርጓሜ፦** ይቅርታና ቅንነት ተገናኙ፡፡ እውነትና ሰላም ተስማሙ፡፡ ይቅርታ የተባለ ከሰማያት የወረደ ክርስቶስ ነው፡፡ ቅንነት የተባለ ደግሞ ከምድር የተገኘ ዮሐንስ ነው፡፡ (#በግእዝ፦ ሣህል ወርትዕ ተራከባ ጽድቅ ወሰላም ተሰዐማ፡፡ ሣህልሰ ክርስቶስ ውእቱ ዘወረደ እምሰማያት ወርትዕሰ ዮሐንስ ውእቱ ዘሠረፀ እምድር)፡፡

## ●ዘዘካርያስ●

**ዘካርያስ፦** አንተም ሕፃን የልዑል ነቢይ ትባላለህ ብሎ ዘካርያስ በልጁ ላይ ትንቢት ተናገረ፡፡ ከካህኑ ዘካርያስ ወገብ ኮከብ ወጣ፡፡ (#በግእዝ፦ ተነበየ ዘካርያስ ላዕለ ወልዱ ዮሐንስ ወይቤ ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ፡፡ እምሐቌ ዘካርያስ ካህን ኮከብ ሠረቀ)፡፡

**ዮሐንስ መጥምቅ፦** ዮሐንስ ማለት ትርጉሙ ደስተኛ ልጅ ማለት ነው፡፡ (#በግእዝ፦ ዮሐንስ ብሂል ፍሡሕ ወልድ ብሂል በትርጓሜሁ)፡፡

**ትርጓሜ፦** አቤቱ ከጥልቁ ልቤ ጠራውህ። ከጥልቁ ማለት ከልብ ሥር ማለት ነው። (#በግእዝ፦ እማዕምቀ ልብየ ጸዋዕኩከ እግዚኦ። እማዕምቅ ብሂል እምሥርወ ልብ ብሂል)

**ዘፍሬ ሰንበት**

**እግዚአብሔር፦** ቸርና ባዕለጸጋ አቤቱ ሁሉ አለህ። ሥውር መዝገብ ከአንተ ዘንድ አለ። ከቤትህ በረከት ለሁሉ ትመግብ ዘንድ እንግልድህለን። የሰንበት ጌታዋ ሆይ ለአንተ ምስጋና ይገባል። ክረምትንና በጋን በየወገኑ ሁሉንም በጊዜው ጊዜ ሠራ። የዱር እንስሳትና የሰማይ ወፎች እንዲሁም የባሕር ዓሣዎች እርሱን ያመሰግናሉ። አቤቱ ፍጥረት ሁሉ ወደ አንተ ያንጋጥጣሉ። ለሁሉ የሚሰጥ ለሁሉ የሚበቃ እግዚአብሔር ስሙ ይመስገን። [አቤቱ] አንተ በሰማይ አለህ፣ አንተ በምድር አለህ። ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም። [እግዚአብሔር] በየዓመቱ ክረምትን ያገባል። የተራበች ሰውነትን ያጠግብ ዘንድ ከምድር በረከትን ከሰማይ ዝናማትን ይሰጣል ምሕረትንም ያደርጋል። [አቤቱ] የተራበች ሰውነት እየጠገበች ታመሰግንሀለች። እግዚአብሔርን መፍራት የእውነት ፍሬ ነው። እንደ አምላካችን ይቅር ባይና ታጋሽ ማን አለ? ዝናምን በጊዜው ይሰጣል። የምድርን ፍሬም ባርኮ አሳምሮ እንዲያፈራ ያደርጋል። (#በግእዝ፦ ባዕል ወኄር ኵሉ ብከ መዝገብ ኅቡዕ ኀቤከ ሀሎ። ናስተበቍዐከ ትሴሲ ለኵሉ እምጠለ ቤትከ። ስብሐት ለከ እግዚኣ ለሰንበት። ኵሎ ሠርዐ በዕድሜሁ ክረምተ ወሐጋየ ዘበበዘመዱ። እንስሳ ገዳምኒ አዕዋፈ ሰማይኒ ወዓሣተ ባሕርኒ ኪያሁ ይሴብሑ። ወኵሉ ፍጥረት ያንቀዐድዉ ኀቤከ እግዚኦ። ይትአኰት ስሙ ለእግዚአብሔር ዘይሁብ ለኵሉ ወየአክል ለኵሉ። አንተ በሰማይ ወአንተ በምድር አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌከ። ያርኁ ክረምተ በበዓመት። ይገብር ምሕረተ እምሰማይ ይሁብ ዝናማተ ወእምድር በረከተ ከመ ያጽግብ ነፍሰ ርኅብተ። ነፍስ ርኅብት እንተ ጸግበት ተአኵተከ። ፍሬ ጽድቅ ፈሪሀ እግዚአብሔር። ወመኑ መሐሪ ወመስተዓግሥ ከመ አምላክነ ያሠምር ወያፈሪ ወይባርክ ፍሬሃ ለምድር ወይሁብ ዝናመ በጊዜሁ)።

**ጸሎት፦** በመጀመሪያ ሣርን በኋላ ሰብልን አቤቱ የምድርን ፍሬ ባርክ። (#በግእዝ፦ ቀዳማዌ ሣዕረ ደኃራዌ ሰብለ እግዚኦ ባርክ ፍሬሃ ለምድር)።

**መልካም ሥራ፦** ጌታችን የሕይወት ፍሬን ልቀሙ የመድኀኒት ቦርቦርቴንም [የራስ ቊርን] ተቀዳጁ አለ። መልካም መሥራትን ተማሩ። ሰላምን ፈልጓት [ሿት]። (#በግእዝ፦ ይቤ እግዚእነ እርሩ ለክሙ ፍሬ ሕይወት ዘጽድቅ ተቀጸሉ ጌራ መድኀኒት። ተመሀሩ ገቢረ ሠናይ። ኅሥዋ ለሰላም)።

**ሰንበት፦** [እግዚአብሔር] ሰውን በመውደዱ ሰንበትን ሠራ። ሰውን የሚወድ ክርስቶስ ሰንበትን ለዕረፍት ሠራልን። ስለ ሰው ብሎ ሰንበትን ሠራልን። እግዚአብሔር ሰንበትን አከበራት። ሰማይንና ምድርን ፈጥሮ ከሥራው ሁሉ በእርሷ አርፏልና። (#በግእዝ፦ ሠርዐ ሰንበተ በእንተ አፍቅሮተ ሰብእ። ሠርዐ ለነ ሰንበተ ለዕረፍት መፍቀሬ ሰብእ ክርስቶስ። እስመ

በእንተ ሰብእ ሠርዐ ሰንበተ፡፡ ቀደሳ እግዚአብሔር ለሰንበት እስመ ባቲ አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ ሰማየ ወምድረ ፈጢሮ)፡፡

**ትርጓሜ፦** በዕለተ ሰንበት ኢየሱስ ሐዋርያትን እንዲህ ብሎ አስተማራቸው፡፡ እነሆ ዘሪ በመልካም መሬት ሊዘራ ወጣ፡፡ [ያም መሬት] እጥፍን መቶን አፈራ፡፡ ባለ ስልሳ ያፈራ አለ ባለሠላሳ ያፈራ አለ፡፡ ዘሪውም ካህን ነው፡፡ እርሻውም ዓለም ነው፡፡ (#በግእዝ፦ ምህሮሙ ኢየሱስ ለሐዋርያቲሁ እንዘ ይብል በዕለተ ሰንበት ናሁኬ ወፅአ ይዝራዕ ዘይዘርዕ ውስተ ምድር ሠናይ፡፡ ፈረየ አመዐተ ወአመክዐበ ፻ ዘ፷ ወ፻ ዘ፴፡፡ ዘራዒሁሰ ካህን ውእቱ ወገራህቱኒ ዓለም ውእቱ)

## ዘዘወትር

**ምስጋና፦** ለእርሱ ምስጋና የሚገባው እግዚአብሔርን ፈጽማችሁ አመስግኑት፡፡ (#በግእዝ፦ አእኵትዎ ወሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ለዘሎቱ ይደሉ ስብሐት)፡፡

**እግዚአብሔር፦** እግዚአብሔር ሰማይ ዝናምን ይሰጥ ዘንድ፣ ምድርም ታርሳ የበረከት ፍሬን ትይዝ ዘንድ፣ ምድርም በየወገኑ ታስገኝ ዘንድ አዘዘ፡፡ የልቡናችንን ዓይን ይገልጽልን ዘንድ እንግዲህ የክርስቶስን መንፈስ እንቀበል፡፡ እርሱ ነጻነትን ሰብኮልናልና፡፡ [ጌታ ሆይ] ያዘኑትን የምታረጋጋ፣ ሰላምን የምትሰጥ፣ ለሚያምን ደስታ የሆንክ፣ ተስፋ ለቆረጡት ተስፋቸው፣ የተራቡትን የምታጠግባቸው፣ ለተራቆቱት ልብሳቸው የማትጠፋ ብርሃን [አንተ] ነህ፡፡ (#በግእዝ፦ ሰማይኒ ይሁብ ዝናመ ወምድርኒ ተሐሪሳ ትነሥእ ፍሬ በረከት ታውፅእ ምድር ዘበበዘመዱ አዘዘ እግዚአብሔር፡፡ ንትወከፍ እንከ መንፈሶ ለክርስቶስ ከመ ይክሥት አዕይንተ አልባቢነ እስመ ውእቱ ሰበከ ለነ ግዕዛነ፡፡ ናዛዜ ኅዙናን ወሀቤ ሰላም ፍሥሓ ለዘየአምን ተስፋሆሙ ለቅቡፃን መጽገቢ ለርኁባን ልብስ ለዕሩቃን ዘኢትጠፍእ ብርሃን)፡፡

## መስከረም ፲፩ ዘፋሲለደስ

**ቅዱስ ፋሲለደስ፦** ፋሲለደስ ሆይ በሞትህ ምስጋናን ያመሰግኑ ዘንድ የበኵር [ክርስቶስ] ማኅበር መሰብሰብን ተሰበሰቡ፡፡ ስለዚህም ቤተክርስቲያን ከከበሩ በዓላት አልቃ በጥበብና በእውቀት፣ በጸናጽልና በከበሮ በዓልህን ታከብረዋለች፡፡ ፋሲለደስ ሆይ ወደ አባትህ ወደክርስቶስ ለምንልን፡፡ ፋሲለደስ ልልጆቹ ሁሉ በሥጋችሁ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና አትፍሩ አላቸው፡፡ ነገሥታት እጆቻችሁን እግሮቻችሁን በማሰሪያ [በዛንጅር] ቢያሥሯችሁ፤ አጥንታችሁ እስኪታይ በመግረፊያ ጀርባችሁን ቢገርፏችሁ፤ በብረት አልጋ በእሳት ውስጥ ቢያስተኟችሁ፤ በብረት ምጣድ ቢያበስሏችሁ፤ የፈላ እርሳስን ከሙጫ ጋር አድርገው ቢያጠጧችሁ፤ በመስቀል ቢሰቅሏችሁ በችንካር ቢቸነክሯችሁ፤ ሰውነታችሁን በማረሻ ቢቀዷችሁ፣ አንገታችሁን በሰይፍ ቢቆርጧችሁ አትፍሩ አላቸው፡፡ [ፋሲለደስ ሆይ] በበዓልህ ማሕሌት የቆሙ ካህናት፣ ስምህን የጠሩ መታሰቢያህን ያደረጉ ኃጥኣን በኪዳንህ ይጸድቃሉ፡፡ [ፋሲለደስ ሆይ] መታሰቢያህን ያደረገ ስምህን የጠራ አማኝ በመንግሥተ ሰማያት ከአንተ ጋር ይነግሣል፡፡ ፋሲለደስ ተጋድሎን

በተጋደለ ጊዜ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ከእኔ ጋር ትነግሣለህ አለው:: (#በግእዝ፦ ማኅበረ በኵር አማኅበሩ አማኅብሮ:: በሞትከ ፋሲለደስ ይዘምሩ ዘምሮ:: ወበእንተዝ ፈድፋደ ለበዓልከ ታከብሮ:: እምበዓላት ክቡራት በጸናጽል ወበከበሮ:: ቤተክርስቲያን በጥበብ ወበአእምሮ:: ሰአል ለነ ፋሲለደስ ኀበ አቡከ ክርስቶስ:: ኢትፍርሆ ይቤሎሙ ፋሲለደስ ለደቂቁ ኵሎሙ ትሙቱ በሥጋክሙ:: እመኒ ነገሥት እደዊክሙ ወእገሪክሙ በመዋቅሕት ሞቅሑክሙ ኢ በአስዋጥ ቀሰፉ ዘባነክሙ እስከ ይትረአይ አፅምክሙ ኢ በአራተ ሐፂን ውስተ እሳት አስከቡክሙ ወበጤገን ዘብርት አብሰሉክሙ ኢ ምስለ ዝፍት ወፒሳ ለጕርዔክሙ ፍሉሐ አረር አስተዩክሙ ኢ በመስቀል ሰቀሉክሙ ወበቅንዋት ቀነዉክሙ ኢ በሞሰርት ሰተሩ አባለክሙ ወበሰይፍ መተሩ ክሳደክሙ ኢትፍርሆ ይቤሎሙ:: ይጸድቁ ኃጥኣን በኪዳንከ እለ ገብሩ ተዝካረከ ወጸውኡ ስመከ ወሐለዩ ካህናት ማሕሌተ በበዓልከ:: በመንግሥተ ሰማያት ይነግሥ ምስሌከ ምእመን አመ ገብረ ተዝካረከ ወጸውአ ስመከ:: በመንግሥተ ሰማያት ትነግሥ ምስሌየ እግዚአብሔር ይቤሎ ለፋሲለደስ አመ ተጋደለ ተጋድሎ)::

## 🍎መስከረም ፲፮🍎

**🌹ቤተክርስቲያን🌹፦** የኃጢአት ማስተሥረያ ትሆን ዘንድ ቤተክርስቲያንን በሰማያዊት መቅደስ አምሳል አነጿት ሠሯት:: በስሙ ተሠራች:: በደሙ ከበረች:: በዕፀ መስቀሉ ተባረከች:: (#በግእዝ፦ ሐነጽዋ ወሣረርዋ ለቤተክርስቲያን ከመ ትኩን አርአያ ዘበሰማያት ወከመ ትኩን ምስትሥራየ ኀጢአት:: ተሐንጸት በስሙ ወተቀደሰት በደሙ ወተዓትበት በዕፀ መስቀሉ)::

## ❤መስከረም ፲፯ ዘመስቀል❤

**ነገረ ክርስቶስ፦** [ክርስቶስ] በቀራንዮ የመስቀልን ኀፍረት ታገሠ:: በሰቀሉት ጊዜ ከልብስ አራቆቱት:: በጦር ጫፍ ወጉት:: ቤተክርስቲያን ውበቱ እንደ ፀሐይ ጨረር ያበራውን፣ በጎልጎታ ደሙ የፈሰሰውን [ክርስቶስን] በችንካር ተቸንክሮ አየችው:: በመስቀሉ ገነትን ለከፈተና መድኀኒትን ላደረገ [ለክርስቶስ] ፈጽመን እንዘምራለን:: ለክርስቶስ የመስቀሉ በዓል በሆነች በዚህች ዕለት ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን:: አቤቱ አዳምን ወደ ገነት የመለሰው መስቀልህ ለአመንን ለእኛም መሪ ይሁነን:: ኢየሱስ አይሁድን እንዲህ አላቸው:: "በእኔ እመኑ በአባቴም እመኑ:: ዛሬ ለእኔ ወገኖች በመስቀሌ አበራሁ":: ክርስቶስ ሆይ በመስቀልህ ረዳህን ሕይወትንም ሰጠህን:: (#በግእዝ፦ በቀራንዮ ኀፍረተ መስቀል ተዐገሠ ጊዜ ሰቀልዎ አዕረቅዎ ልብሰ በአፈ ኵናት ረገዝዎ:: ቤተክርስቲያን ርእየቶ ቅንወ ለዘበጎልጎታ ደሙ ተክዕወ:: ከመ እግረ ፀሐይ ስኑ ሐተወ:: ንሴብሕ ወንዜምር ለዘበመስቀሉ አርኀወ ገነተ ወገብረ መድኀኒተ:: ንዑ ንትፌሣሕ በእግዚአብሔር በዛቲ ዕለት በዓለ መስቀሉ ለክርስቶስ ወለእለኒ እለ አመነ መስቀልከ መርሐ ይኩነነ ለአዳም ዘአግብዖ ውስተ ገነት:: ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአይሁድ እመኑ ብየ ወእመኑ በአቡየ ዮምሰ ለእሊኣየ አበርህ በመስቀልየ:: በመስቀልከ ክርስቶስ ረዳእከነ ወሕይወተ ጸጎከነ)::

**መስቀል፦** እንጨትን ታመልካላችሁን? ለእንጨትስ በዓልን ታደርጋላችሁን የሚሉ አሉ:: [የክርስቶስ] ደሙ የእንጨት መስቀሉን አልቀደሰውምን? [ስለቀደሰው] እናመልከዋለን:: ክርስቶስ መስቀልን ተመርኩዞ ተአምራትን እያደረገ በሰሎሞን መመላለሻ ተመላለሰ:: መስቀል ለዓለም ሁሉ ብርሃን የቤተክርስቲያን መሠረት ነው:: መስቀል ቤዛችን ነው:: መሰቀል ጽንዓችን ነው:: መስቀል የነፍሳችን መድኀኒት ነው:: ያመንን በመስቀሉ ድነናል:: በመስቀሉ ኀይል ይጠብቀን የልቡናዎቻችንን ዓይኖችም ይግለጥልን:: መስቀል አሸነፈ ሞት ተሸነፈ:: በመስቀሉ ከኃጢአት ቀንበር ተቤዠን:: በመስቀሉ ምድር ሁሉ ተቀደሰች:: መስቀል የሕይወት እንጨት ነው:: መስቀል የመድኀኒት እንጨት ነው:: መስቀል የአሕዛብ ብርሃናቸው የነገሥታት መድኀኒታቸው ነው:: መስቀል ለደካሞች ረዳት ነው:: መስቀል ለተከዙት ደስታና ሰላም ነው:: ፊቴን በመስቀል ምልክት አማትባለሁ:: የሱራፌል ክብራቸው የተሰቀለበት ለፈያታይ ገነትን የከፈተ ዕፀ መስቀል ዛሬ ተገኘ:: በመስቀሉ መድኀኒትን አደረገ:: መስቀል የባሕር ጸጥታ የመርከቦች ወደብ ነው:: የክርስቶስ መስቀል ብርሃን ነው:: በክርስቶስ መስቀል ከሞት ዳንን:: መሰቀልህ መሪ ይሁነን:: ከጠላታችን እጅና ከሚጠሉን ሰዎች ሁሉ ያድነን ዘንድ በመንገድ ከእኛ ጋር ይሁን:: በመፈለግ የተገኘ መስቀል ቅዱስ ነው:: ጢስ ዕጣን ወዳመለከተበት ሰገደ:: ከጨረቃና ከከዋከብት ይልቅ መስቀል ለሁሉ አበራ:: በመስቀሉ ኀይል አጋንንትን አወጣ ለምጻሞችን አነጻ:: የዓለምን ኃጢአት ለዘለዓለሙ የሚያስወግድ መስቀል መመኪያ ነው:: በቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ በመስቀሉ አምኖ በቅጽበት ዳነ:: መስቀል ሆይ ስለቅዱስ ስምህ ርዳን አድነንም:: በላይ በሰማይ በታች በምድር ዛሬ የመስቀሉ በዓል ነው:: መስቀል የኃጥኣን መላሻቸው ነው:: (#በግእዝ፦ ሀለዉ እለ ይቤሉ ለዕፅኑ ታመልኩ ወለዕፅኑ በዓለ ትገብሩ:: ኢቀደሶኑ ደሙ ክቡር ለዕፀ መስቀሉ ወበእንተዝ ንሕነ ናመልኮ:: አንሶሰወ ኢየሱስ በሕዋረ ሰሎሞን እንዘ ይገብር መንክረ ወይትመረጎዝ መስቀለ:: ዮም መስቀል ተሰብሐ ለአኃው አብርሀ:: መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም መሠረተ ቤተክርስቲያን:: መስቀል ቤዛነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል መድኀኒተ ነፍስነ:: እለ አመነ በመስቀሉ ድኅነ:: በኀይለ መስቀሉ ይዕቀበነ ወይክሥት አዕይንተ አልባቢነ:: መስቀል ሞዐ ሞት ተሞዐ:: በመስቀሉ ቤዘወነ እምአርዑተ ኃጢአት፣ በመስቀሉ ተቀደሰት ኵላ ምድር:: መስቀል ዕፀ ሕይወት መስቀል ዕፀ መድኀኒት:: ብርሃኖሙ ለአሕዛብ መስቀል መድኀኒቶሙ ለነገሥት መስቀል:: መስቀል ረድኤት ለድኩማን ጽንዕ ለትኩዛን ፍሥሓ ወሰላም:: አአትብ ገጽየ በትእምርተ መስቀል:: ዮም ተረክበ ዕፀ መስቀል ሠናይ ዘአርኀወ ገነተ ለፈያታይ በዘቦቱ ተሰቅለ ዘሱራፌል ዕበይ:: በመስቀሉ ገብረ መድኀኒተ:: ዛኅኑ ለባሕር ወመርሶ ለአሕማር መስቀል:: መስቀሉሰ ለክርስቶስ ብርሃን:: በመስቀሉ ለክርስቶስ ድኅነ እሞት:: መስቀልከ መርሐ ይኩነነ በፍኖት የሀሉ ምስሌነ:: ከመ ያድኅነነ እምእደ ፀርነ:: ወእምእደ ኵሎሙ እለ ይጸልዑነ:: መስቀል ቅዱስ ዘተረክበ በኀሢሥ ዘዕጣን አንጸረ ሰገደ ጢስ:: መስቀል አብርሀ ለኵሉ እምወርኀ ወእምከዋክብት:: በኀይለ መስቀሉ አጋንንተ አውፅአ እለ ለምጽ አንጽሐ:: መስቀል ትምክሕት ኃጢአተ ዓለም ዘየዐትት ለዝሉፉ:: ፈያታዊ ዘየማን አምነ በመስቀሉ በቅጽበት ድኅነ:: መስቀል ርድአነ ወአድኅነነ በእንተ ስምከ ቅዱስ:: ዮም በዓለ መስቀሉ በሰማያት በላዕሉ ወበምድር በታሕቱ:: መስቀል መያጢሆሙ ለኃጥኣን)::

**ቤተክርስቲያን፦** የእግዚአብሔር የምስጋናው ማደሪያ መልካሟ ቤተክርስቲያን ተቀደሰች፡፡ የሰው እጅ ያልሠራት ፍጽምት የሆነች ድንኳን ናት፡፡ የምእመናን መስገጃቸው ቤተክርስቲያን በክቡር ደሙ በዕፀ መስቀሉ ተቀደሰች፡፡ በካህናት እጅ የተሠራች በጳጳሳት አፍ የተባረከች እናታችን ጽዮን ምስጋና የሚከባት የተለየችና የሰማዕት እናታቸው እንዲሁም የመለኮት ማደሪያ ፍጹም የሆነች ድንኳን ናት፡፡ (#በግእዝ፦ ማኅደረ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር ተቀደሰት ቤተክርስቲያን አዳም ወሠናይት ደብተራ ፍጽምት እንተ ኢገብራ እደ ሰብእ፡፡ በደሙ ክቡር በዕፀ መስቀሉ ተቀደሰት ቤተክርስቲያን ምስጋዶሙ ለመሃይምናን፡፡ እንተ ተሐንፀት በእደ ካህናት ወተቀደሰት በአፈ ጳጳሳት እምነ ጽዮን ቅድስት እንተ የዐውዳ ስብሐት እሞሙ ይእቲ ለሰማዕት ደብተራ ፍጽምት ማኅደረ መለኮት)፡፡

## ❤መስከረም 18 ዘኤዎስጣቴዎስ❤

**ኤዎስጣቴዎስ፦** አባ አባ ክቡር የእግዚአብሔር ሰው ኤዎስጣቴዎስ ሆይ ዜናህ በምድር ሁሉ ተሰማ፡፡ እግዚአብሔር የጻድቅን ጸሎት ይሰማልና አባ [ኤዎስጣቴዎስ] ሆይ ስለእኛ ጸልይልን፡፡ በደብር በገዳም የምትኖሩ ቅዱሳን አባቶች ሆይ በሰላም እንኖር ዘንድ አማልዱን፡፡ መምህር ኤዎስጣቴዎስ በባሕር ጀርባ ላይ ያለመርከብ በመንፈስ ይሔዳል፡፡ እንደ ዮሐንስ ቀሲስ አፉን እስኪስመው ድረስ ለንዑድ ኤዎስጣቴዎስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ሞገስ ተሰጠው፡፡ ካህን ነቢይና ወንጌላዊ ኤዎስጣቴዎስ ቸር እረኛና የመምህሩን የናዝራዊውን የአምላክ ልጅ [የኢየሱስ ክርስቶስን] አሰር [ዱካ] የሚከተል ነው፡፡ (#በግእዝ፦ አባ አባ ክቡር ኤዎስጣቴዎስ መምህር ብእሴ እግዚአብሔር ተሰምዐ ዜናከ ውስተ ኵሉ ምድር፡፡ አባ ጸሊ በእንቲኣነ እስመ ጸሎተ ጻድቅ ይሰምዕ እግዚአብሔር፡፡ አበው ቅዱሳን እለደብር ወገዳም አስተምሕሩ ለነ ነሀሉ በሰላም፡፡ በመንፈስ የሐውር ኤዎስጣቴዎስ መምህር እንበለ ሐመር ዲበ ዘባና ለባሕር፡፡ ተውህቦ ሞገስ ለብፁዕ ኤዎስጣቴዎስ እምኀበ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከነ አፉሁ ሰአሞ ከመ ዮሐንስ ቀሲስ፡፡ ካህን ወነቢይ ወንጌላዊ ኤዎስጣቴዎስ ኄር ኖላዊ አሰረ መሰቀለ መምህሩ ተላዊ ለወልደ አምላክ ናዝራዊ)፡፡

**ዕሌኒ፦** የክርስቶስን የእንጨት መስቀል ትፈልግ ዘንድ ንግሥት ዕሌኒ ወደ ጎልጎታ ሄደች፡፡ የታመነ ኪራኮስ ጸለየ፡፡ በዚያ ቦታ መዓዛው ያማረ ጢስ ወጣ፡፡ ክቡር የሆነው የእንጨት መስቀልም ከችንካሮቹ ጋር በምድር ላይ እያበራ ተገኘ፡፡ ዕሌኒም ለንጉሥ ልጅ ለቆስጠንጢኖስ ጠላቶቹን በሚያሸንፍበት ገንዘብ [ያሸንፍ ዘንድ] የፈረስ ልጓም [የመስቀል ምልክት ያለበት] ሥሩልኝ አለች፡፡ የመስቀል ችንካሮችን ባየች ጊዜ ዕሌኒ በአንደበቷ እልል አለች በእግሯም አሸበሸበች፡፡ ዕሌኒ መልአኩን ስለክርስቶስ መስቀል ንገረኝ አለችው፡፡ መልአኩም ስለ መስቀሉ ድንቅ ነገር ነው ወልድ በአባቱ አጠገብ ሳለ እኛ የመላእክት ማኅበር ስለክቡር የእንጨት መስቀል መናገር ጀመርን አላት፡፡ (#በግእዝ፦ ዕሌኒ ንግሥት ነገደት ጎልጎታ ኀበ ተኀሥሥ ዕፀ መስቀሉ ለክርስቶስ፡፡ ኀሠሠት ዕሌኒ መስቀለ ክርስቶስ ወተረክበ በቀራንዮ መካን፡፡ ጸለየ ኪራኮስ ምእመን ወፅአ ጢስ ዘመዓዛሁ ሠናይ በውስተ ውእቱ መካን ወተረክበ ዕፀ መስቀል ክቡር ወቅንዋቲሁ እንዘ ያበርህ ዲበ ምድር፡፡ ወትቤ ዕሌኒ ግበሩ ሊተ ልጓመ ፈረስ ለቆስጠንጢኖስ

ለወልደ ንጉሥ በዘይመውዕ ፀሮ ወጸላእቶ:: የበበት ዕሌኒ በአፉሃ ወአጽሐሰት በእገሪሃ ሶበ ትሬኢ ቅንዋተ መስቀል:: ትቤሎ ዕሌኒ ለመልአክ ንግረኒ በእንተ መስቀሉ ለክርስቶስ ወይቤላ መልአክ ዕፁብ ነገሩ በእንተ መስቀሉ እንዘ ሀሎ ወልድ ውስተ ሕፅነ አቡሁ ንሕነ ማኅበረ መላእክት ወጠነ ተናግሮ በእንተ ውእቱ ዕፀ መስቀል ክቡር)::

**መስቀል፦** አይሁድ በቅናታቸው ድንቅ ነገርን አደረጉ ጭንቅ ነገርንም መከሩ:: ሙታንን የሚያድን መስቀሉንም ደፈኑ:: ንግሥት ዕሌኒ ዕንባቆም ነቢይ ሥራውን ያደነቀውን መስቀሉን ፈለገች:: የክርስቶስ መስቀልስ ሙታንን ያስነሣል:: (#በግእዝ፦ መንክረ ገብሩ ወዕፁበ መከሩ በቅንዐቶሙ አይሁድ መስቀሎ ደፈኑ ዘያሐዩ ሙታነ:: ዕንባቆም ነቢይ ዘአንከረ ግብሮ ዕሌኒ ንግሥት ኅሠሠት መስቀሎ:: መስቀሉሰ ለክርስቶስ ያነሥእ ሙታነ)::

## መስከረም 10 ዘጼዴንያ

**ነገረ ማርያም፦** ማርያም ሆይ የወልድን መስቀል እየለበስሽ (ለብሰሽ) ፈጽሞ ደስ ይበልሽ:: ጽዮን ሆይ ዛሬ ደስ ይበልሽ:: (#በግእዝ፦ አብርሂ አብርሂ ማርያም አብርሂ መስቀሎ ለወልድ እንዘ ትትሞጦሂ:: ጽዮን ዮም ተፈሥሒ)::

**መስቀል፦** ሐዋርያት ስለመስቀል በጠፋው በሰይጣን ላይ የሕመም ምልክት ነው ይላሉ:: መስቀል ረድኤትና ሕይወት ነው:: መስቀል ለተጠሙት ምንጭ ነው:: (#በግእዝ፦ ይቤሉ ሐዋርያት በእንተ መስቀል ትእምርተ ሕማም ውእቱ በዲበ ሰይጣን ኀጉል:: መስቀል ረድኤት ወሕይወት:: መስቀል አንቅዕት ለጽሙዓን)::

**ትርጓሜ፦** ስለእርሱ ነቢዩ ዳዊት ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠኻቸው ብሎ የተናገረለት መስቀል ነው:: (#በግእዝ፦ መስቀል ዘበእንቲኣሁ ጸርሐ ዳዊት ነቢይ እንዘ ይብል ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ)::

## 💟ዘመስቀል ሰንበት💟

**እግዚአብሔር፦** ከያዕቆብ ጋር ሄደ፣ ከአብርሃም ጋርም ተወዳጀ:: ለሰው ዕረፍት ይሆን ዘንድም ሰንበትን ሠራ:: ሰማይን እንደ ባጥ የሰቀለውን፣ ምድር እንዳትነዋወጥ አድርጎ የሠራትን አይሁድ በእንጨት መስቀል ላይ ሰቀሉት:: [ክርስቶስ] ስለሰው ልጆች ብሎ በእንጨት ላይ ተሰቀለ:: ስሑታንን ይመልስ ዘንድ በእንጨት መስቀል ላይ ኃጥኣንን ታገሠ:: እንደ በደለኛ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ከሞት ነጻ አወጣን ወደ ሕይወትም መራን:: (#በግእዝ፦ ምስለ ያዕቆብ ነገደ ወምስለ አብርሃም ተአረከ ወሠርዐ ሰንበተ ለሰብእ ዕረፍተ:: ዘሰቀሎ ለሰማይ ከመ ቀመር ወሣረራ ለምድር ከመ ኢታንቀልቅል ሰቀልዎ አይሁድ ዲበ ዕፀ መስቀል:: ተሰቅለ ዲበ ዕፅ በእንተ ውሉደ ሰብእ:: ዲበ ዕፀ መስቀል ተዐገሠ ኃጥኣነ ከመ ይሚጥ ስሑታነ:: ተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ከመ ዕቡስ ወአግዐዘነ እሞት ወመርሐነ ውስተ ሕይወት)::

**መስቀል፦** መስቀል አጋንንትን የሚያባርር ነው [አጋንንትን የሚያባርር መስቀል ነው]። በክርስቶስ መስቀል ጨለማ [ዲያብሎስ] ተሰደደ። (#በግእዝ፦ መስቀል ሰዳዲሆሙ ለአጋንንት። በመስቀሉ ለክርስቶስ ተሰደ ጽልመት)።

**ቤተክርስቲያን፦** ተተውኩ የተጣልኩ ሆኜ ሳለ በመስቀልህ አበራህልኝ እያለች ቤተክርስቲያን [ኢየሱስን] ታመሰግነዋለች። ስለእኔ የርኩሳንን ምራቅ ታገሥክ። በትንሣኤህ ሕይወትን አገኘሁ። (#በግእዝ፦ ትዌድሶ ቤተክርስቲያን እንዘ ትብል በመስቀልከ አብራህከ ሊተ እንዘ ኅድግት ወግድፍት አነ። ምራቀ ርኩሳን ተዐገሥከ በእንቲአየ። ሕይወተ ረከብኩ በትንሣኤከ)።

**†ዘዘወትር†**

**መስቀል፦** መስቀል በመንገድ መሪ ነው። ለዕው*ራን መሪ ሆናቸው። ይህ መስቀል ለምናምን ለእኛ ደስታ ሆነን። ይህ መስቀል በሰማይ ነገሠ። ይህ መስቀል ጭንቅ ነገርን የሚያቀል ነው። ችግረኛን የሚረዳ ነው። መስቀል ለዓለም ሁሉ ብርሃን ነው። ሰነፎችን ጥበበኛ የሚያደርግ ነው። መስቀል የሁሉ ቤዛ ሆነ። መስቀል ተስፋ ለቆረጡት ተስፋቸው ነው። ፀሐይ ጠቅሰዋለችና ሽፍታው አመነ። መስቀል ሰላምን የሚሰጥ፣ ዓለምን ያዳነ፣ ብርሃንን የሚገልጥ ነው። (#በግእዝ፦ መስቀል መርሕ በፍኖት። ለዕው*ራን ኮኖሙ መርሐ። ለእለ ነአምን ዝንቱ መስቀል ኮነነ ፍሥሓ። ዝንቱ መስቀል በሰማይ ነግሠ። ዝንቱ መስቀል ዘዕፁብ ያቀልል። ረዳኤ ምንዱብ። መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም። መጥበቢሆሙ ለአብዳን። መስቀል ቤዛ ኵሉ ኮነ። መስቀል ተስፋ ቅቡፃን። አምነ ፈያታይ እስመ ፀሐይ ቀጸበቶ። መስቀል ወሀቤ ሰላም መድኅኔ ዓለም ከሣቴ ብርሃን)።

**እግዚአብሔር፦** ከጨለማ ወደ ብርሃን ያወጣን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ለሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ጌታን ሰቀሉት መከራንም አደረሱበት። ወደ ምድረበዳ ብሄድም ኀይሌ እግዚአብሔር ነው። ወደ መንገድ ስትሔዱ ክርስቶስ በሉ በመን*ፈቀ ሌሊት ስትተኙም አባታችን ሆይ በሉ። አይሁድ ግን አላወቁም በቅንዐታቸው መድኀኒታቸውን ሰቀሉ። ወደ ጨለማ [መከራ] ብሄድም ክርስቶስ በመስቀሉ ያበራልኛል። (#በግእዝ፦ ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ለዘአውጽአነ እምጽልመት ውስተ ብርሃን። ሰቀልዎ ወአሕመምዎ ለዘይጼጉ ሕይወተ ለኵሉ። እመኒ ሖርኩ ውስተ በድው ኀይልየ እግዚአብሔር። ሶበ ተሐውሩ ውስተ ፍኖት ክርስቶስ በሉ ወሶበ ትነውሙ መን*ፈቀ ሌሊት አቡነ በሉ። አይሁድሰ ኢያእመሩ በቅንዐቶሙ መድኀኒቶሙ ሰቀሉ። ወለእመኒ ሖርኩ ውስተ ጽልመት ያበርህ ሊተ ክርስቶስ በመስቀሉ)።

**ትርጓሜ፦** መስቀል አብርሃም ለመሠዊያ የፈለጠው የማይነቅዝ እንጨት ነው። ይህ እንጨት በጥፋት ውሃ ጊዜ ኖኅን ያዳነው ነው። አባታችን አብርሃም ይሠዋው ዘንድ ልጁን ይስሐቅን ወሰደው። [እግዚአብሔርም] ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ የተያዙ የይስሐቅ ቤዛ በግን አወረደለት። ዕፀ ሳቤቅ ማለት የሥርየት [የይቅርታ] እንጨት ማለት ነው። ሙሴ የብረት እባብን በገዳም በሰቀለ ጊዜ ለእስራኤል ልጆች መሪ ሆናቸው። እንደዚሁ ክርስቶስም በመስቀል ላይ ተሰቀሎ ለብዙዎች

ቤዛ ሆነ። (#በግእዝ፦ መስቀል ዕፅ ዘኢይነቅዝ ዕፅ ዘሠፀረ አብርሃም ለምሥዋዕ። ዝንቱ ዕፅ ዘአድኀና ለኖኅ አመ አይኅ። አቡነ አብርሃም ወሰዶ ለይስሐቅ ወልዱ ከመ ይሡዖ አውረደ ሎቱ ቤዛሁ በግዐ እኁዝ አቅርንቲሁ በዕፀ ሳቤቅ። ዕፀ ሳቤቅ ብሂል ዕፀ ሥርየት መስቀል። አመ ይሰቅል ሙሴ አርዌ ብርት በገዳም ወኮኖሙ መርሐ ለደቂቀ እስራኤል እስመ ከማሁ ክርስቶስኒ ተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ወኮነ ቤዛ ብዙኃን)።

**ነገረ ማርያም፦** [ድንግል ማርያምን] ጴጥሮስ የብርሃን እናት አላት። ጳውሎስም የነጻነት ድንኳን አላት። (#በግእዝ፦ ጴጥሮስኒ ሰመያ እመ ብርሃን ጳውሎስኒ ይቤላ ደብተራ ግዕዛን)።

**ቤተክርስቲያን፦** [ክርስቶስ] በመስቀል ላይ [በችንካር] ተቸንክሮ ሳለ ቤተክርስቲያን ስለማን ተሰቀልክ አለችው። እርሱም ልጆችሽን አድን ዘንድ ስለአንቺና ስለሕዝብሽ ተሰቀልኩ አላት። እርሷም ለአንተ ምስጋና ይገባል ለላከህም ምስጋና ይገባል አለችው። (#በግእዝ፦ ትብል ቤተክርስቲያን እንዘ ስቁል ወቅንው ዲበ ዕፀ መስቀል እግዚኦ በእንተ መኑ ተሰቀልከ። ወይቤላ በእንቲኣኪ ወበእንተ ሕዝብኪ። ከመ አድኅኖሙ ለውሉድኪ። ወትቤሎ ስብሐት ለከ ወለዘፈነወከ)።

**ነገረ ቅዱሳን፦** በመልካም ሥራ ያማራችሁና የጎለመሳችሁ [ቅዱሳን] ሆይ ጸሎታችሁ የጸናች ናት፣ ትክክለኛ ሃይማኖታችሁም በሁሉ የምትረዳ ናት። ይህንን ኀላፊ ዓለም የናቃችሁት [እናንተ] ነጻ አውጪዎች ናችሁ። ወንድሞቼ ወዳጆቼ እንደ እንግዳና እንደ መጻተኛ ኑሩ። የዚህ ዓለም ንብረቱ [አኗኗሩ] ምን ይጠቅመናል!? የዚህ ዓለም ሽልማቱስ ምን ይጠቅመናል!? በምድር ያለ ቤታችን ቢፈርስ በሰማያት ያለ ሕንፃ አለን። (#በግእዝ፦ ጸሎትክሙ ጽንዕት ሃይማኖትክሙ ርትዕት እንተ በኵሉ ትረድእ ሠናያን ወውርዝዋን በምግባረ ጽድቅ አግዓዝያን አንትሙ እለ መነንክምዎ ለዝንቱ ዓለም ኀላፊ። ከመ ነግድ ወፈላሲ ሀልዉ አኃውየ ፍቁራንየ። ምንት ይበቍዐነ ንብረቱ ለዝንቱ ዓለም ኢትርሲቱ ለዝንቱ ዓለም። እመኒ ተነሥተ ማኅደርነ ዘበምድር ብነ ሕንፃ ዘበሰማያት)።

## 💖መስከረም 21 ዘብዙኃን ማርያም💖

**ሰማዕት፦** ሰማዕታት በትዕግሥታቸው ሃይማኖታቸውን ጠበቁ ተስፋንም አገኙ። (#በግእዝ፦ በትዕግሥቶሙ ሰማዕት ዐቀቡ ሃይማኖቶሙ ወአድምዑ ተስፋ)።

**ካህናት፦** ጳጳሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሆይ በሃይማኖት ደፋሮች ሁኑ ምእመናንንም አጽኑ። ካህናት ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገሩ። ሕግ ከካህናት አንደበት ይወጣልና [ለካህናት] ሕግ አላቸው ሥርዓትም አላቸው። (#በግእዝ፦ ጥቡዓነ ኩኑ በሃይማኖት ጳጳሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወአጽንዑ ቤተክርስቲያን። ዐደዉ ካህናት እሞት ውስተ ሕይወት። ሎሙ ሕግ ወሎሙ ሥርዓት እስመ ሕግ ይወፅእ እምአፈ ካህናት)።

**ነገረ ማርያም፦** ድንግል ማርያም የደናግል መመኪያቸው ናት። ለተጨነቁት [ጭንቀታቸውን] የምታቀል የተመረጠች ቤት ናት። ለፍጥረት ሁሉ ትለምናለች። እርሷ ከኪሩቤል ከሱራፌል ትበልጣለች። የድንግል ማርያም ክብሯና ገናንነቷ ፍጹም ድንቅ ነው። መሠረቷ የከበረ ዕንቊ ነው። በውስጧ ሰው ተወለደ። እርሱም መልካሟ የእኔ ርግብ ሆይ ነይ ይላታል። በእርሷ ቃል ተሞሸረ በእርሷ ቃል ሰው ሆነ። (#በግእዝ፦ ማርያም ድንግል ምክሖን ለደናግል። ይእቲኬ ቤት ምስአል ዘአስተዐፀቡ ታቀልል። ለኵሉ ፍጥረት ትተነብል። ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል ወትፈደፍድ እምሱራፌል። መንክር ወመድምም ዕበያ ወክብራ ለድንግል። ክቡራት ዕንቊ መሠረታ ብእሲ ተወልደ በውስቴታ ውእቱኒ ይቤላ ንዒ እንቲኣየ ሠናይት ርግብየ እንተ በላዕሌሃ ተመርዐወ ቃል እንተ በላዕሌሃ ተሠገወ ቃል)።

**ሠለስቱ ምእት፦** ሥርዓትን ይሠሩ ዘንድ ሃይማኖትን ያጸኑ ዘንድ እግዚአብሔር ከየሀገሩ ሰበሰባቸው። 318ቱ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናትና ብዙ የሆኑ ሕዝቦች ሃይማኖትን የሚጠብቁ ናቸው። (#በግእዝ፦ ይሥርዑ ሥርዐተ ያጽንዑ ሃይማኖተ አስተጋብኦሙ እግዚአብሔር እምበሐውርት። ሠለስቱ ምእት ዐሠርቱ ወሰመንቱ ኤጲስ ቆጶሳት ጳጳሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ብዙኃን ሕዝብ ዐቃብያነ ሃይማኖት)።

**እግዚአብሔር፦** እግዚአብሔር የሰማዕታት አክሊል የካህናት ሿሚ ነው። ሕይወትን የሚሰጥ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ነው። (#በግእዝ፦ አክሊለ ሰማዕት ሰያሜ ካህናት ውእቱ። ዐማዪ ሕይወት ዘሀሎ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም)።

## 💖መስከረም 25 ፀአተ ክረምት💖

**ጳውሎስ፦** ቅዱስ ጳውሎስ በባሕርም በየብስም መከራን የሚታገሥ ሆነ። ቤተክርስቲያን አሳዳጅ ሲሰደድ ገፊ ሲገፋ ድንቅ ነገርን አይታ ምንኛ ታደንቃለች። ቀድሞ ይሳደብ የነበረው በኋላ ወንጌልን ለመስበክ ሲተጋ አይታ ቤተክርስቲያን ታደንቃለች። (#በግእዝ፦ ወኮነ ዘይትዔገሥ ምንዳቤ በባሕር ወበየብስ። እፎ ታነክር ቤተክርስቲያን ርእያ መንክረ ሰዳዲ እንዘ ይሰደድ ወገፋዒ እንዘ ይትገፋዕ። ዘቀዲሙ ይጼዕል ይእዜሰ ይተግህ ለሰቢከ ወንጌል)።

**ትርጓሜ፦** ቤተክርስቲያን ጴጥሮስንና ጳውሎስን አይታ ልጅ ወንድሜ ወደ አትክልት ቦታ ወረደ አለች። ወደ አትክልት ቦታ ማለት ወደ ሐዋርያት ርስት ማለት ነው። ኢየሱስ ጴጥሮስን በጎቼን ጠብቅ አለው። በጎቹ የተባሉም ወደ አትክልት ቦታ ወደ አበቦች የሚሰማሩ ሐዋርያት ናቸው። አበባ ማለትም ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት። (#በግእዝ፦ ጴጥሮስሀ ርእያ ወጳውሎስሀ ነጺራ ቤተክርስቲያን ወትቤ ወረደ ወልድ እኁየ ውስተ ገነት። ውስተ ገነት ብሂል ውስተ ርስቶሙ ለኵሎሙ ሐዋርያት ብሂል። ይቤሎ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ሪዐይኬ አባግዕየ። አባግዒሁሰ ለክርስቶስ እሙንቱ ሐዋርያት እለ ይትረአዩ ውስተ ገነት ኀበ ጽጌያት። ጽጌ ብሂል ቅድስት ቤተክርስቲያን)።

## ❤መስከረም 30 ዘያዕቆብ ወዮሐንስ❤

**ሐዋርያት፦** ሃይማኖታቸው የቀና ሐዋርያት ንዑዳን ክቡራን ናቸው። ኢየሱስ የዘብዴዎስ ልጆች ዮሐንስንና ያዕቆብን አግኝቷቸው ተከተሉኝ አላቸው። [እነርሱም] አባታቸውን ትተው ከኢየሱስ ክርስቶስ በኋላ ተከተሉ። [ክርስቶስም] የጠላትን ኀይል ሁሉ ይረግጡ ዘንድ ሥልጣንን ሰጥቶ አሰናበታቸው። የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ ቅዱሳን ሕዝብ፣ የዓለም ብርሃን፣ የቤተክርስቲያን ምሰሶዎች ናቸው። (#በግእዝ፦ ብፁዓን ሐዋርያት ርቱዓነ ሃይማኖት። ረከቦሙ ኢየሱስ ለያዕቆብ ወለዮሐንስ ደቂቀ ዘብዴዎስ ወይቤሎሙ ንዑ ትልዉኒ። ኅዲጎሙ አባሆሙ ተለዉ ድኅሬሁ ለኢየሱስ ወወሀቦሙ ሥልጣነ አብሖሙ ይኪዱ ዲበኵሉ ኀይለ ጸላዒ። ያዕቆብ ወዮሐንስ ፍቁራን ደቂቀ ዘብዴዎስ ብርሃኑ ለዓለም ሕዝብ ቅዱሳን አዕማደ ቤተክርስቲያን)።

## ❤ጥቅምት 4 አብርሀ ወአጽብሐ❤

**ነገረ ክርስቶስ፦** ክርስቶስ በመንግሥቱ የሰማያትና የምድር ንጉሥ ነው። ጻድቃን ስሙን እያመሰገኑ ይደሰታሉ። የነገሥታት ንጉሥ ክርስቶስ ምድርን በአበቦች አስጌጣት። (#በግእዝ፦ ክርስቶስ ንጉሠ ሰማያት ወምድር በመንግሥተ ዚአሁ። ጻድቃን ይትፌሥሑ ወይሴብሑ ለስሙ። ንጉሠ ነገሥት ክርስቶስ አሠርገዋ ለምድር በጽጌያት)።

## ❤ጥቅምት 6 ጳንጠሌዎን❤

**አባ ጳንጠሌዎን፦** የአባ ጳንጠሌዎን የልብሱ መዓዛ እንደ ነጭ ዕጣን መዓዛ ነው። የሐር ልብሱ የአበቦችን ውበት ሊያይ የወረደ ይመስላል። የአባ ጳንጠሌዎን ደብሩ በእርሷ ላይ ቃል የወረደባትን ደብረ ሲናን ትመስላለች። የቅዱሳን መዓዛቸው እንደ ወይን አበባ ያማረ ነው። አጥር ይከባታል። በመስቀል ምልክትም ጽጌረዳ ይከባታል። (#በግእዝ፦ ጼና አልባሲሁ ለአባ ጳንጠሌዎን ከመ ጼና ስሒን አልባሲሁ ዘሜላት ዘወረደ ውስተ ገነት ከመ ይርአይ ሥነ ጽጌያት። አዳም መዓዛሆሙ ለቅዱሳን ከመ ጽጌ ወይን። ደብሩሰ ለአባ ጳንጠሌዎን ትመስል ደብረ ሲና ዘወረደ ቃል ላዕሌሃ ሐጹር የዐውዳ ወጽጌረዳ በትእምርተ መስቀል)።

## ዘጽጌ ሰንበት

**❤እግዚአብሔር❤፦** ሕይወትን የሠራህ አንተ ነህ። ምድርን በአበቦች ውበትና በፍሬያት አጌጥካት። የፍጥረት ሁሉ አምላክና የሰንበት ጌታዋ እርሱ ነው። የአበቦች ውበት ሳይታይ በፊት የይቅርታ አባት ክርስቶስ ነበረ። እስከዚህች ላደረሰን ለክርስቶስ ምስጋና ይገባል። ዓለምን ሁሉ ለያዘ ለአብ ምስጋና ይገባል። ሰንበትን ለቀደሰ ለወልድ ምስጋና ይገባል። ምድርን በአበቦች ላስጌጠ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል። ሦስት ዕፀ ሕይወትን በምድር ላይ የተከለ የመላእክት ክብራቸው ክርስቶስ ነው። (#በግእዝ፦ አንተ ውእቱ ገባሬ ሕይወት። አሠርጎካ ለምድር በሥነ ጽጌያት በዘዚኣሁ ፍሬያት። ውእቱ እግዚኣ ለሰንበት አምላከ ኵሉ ፍጥረት እምቅድመ ያስተርኢ ሥነ ጽጌያት ሀሎ ክርስቶስ አቡሃ ለምሕረት። ለክርስቶስ ይደሉ ስብሐት ለዘአብጽሐነ እስከዛቲ

ሰዓት። ስብሐት ለአብ ለአኃዜ ኵሉ ዓለም ስብሐት ለወልድ ለዘቀደሳ ለሰንበት ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ለዘአሠርገዋ ለምድር በጽጌያት። ክብሮሙ ለመላእክት ክርስቶስ። ወተከለ ሠለስተ ዕፀ ሕይወት በዲበ ምድር)።

**❀ሐተታ ተፈጥሮ❀፦** እነሆ አበቦች አበቡ። እነሆ የሱፍ አበቦች አበቡ። ክረምት አለፈ በረከት ተተካ። ወይኖች አበቡ በለስ ቅጠልን አወጣ የአጨዳ ጊዜ ደረሰ። የሽመላ ድምፅ በምድራችን ተሰማ። ናርዶስ መዓዛውን ሰጠ ዝናምም በጊዜው ጊዜ አቆመ። ወይኖች አበቡ ሮማኖች አፈሩ። በጊዜው የተደሰተ ያዝናል። በጊዜው ያዘነ ይደሰታል። በጊዜው ድኻ የሆነ ባዕለ ጸጋ ይሆናል። በጊዜው ባዕለ ጸጋ የሆነ ድኻ ይሆናል። የዱር አበባም በጊዜው ያልፋል። የማያልፍ የለም። የሰው ሀብቱ እንደ ዱር አበባ ነው። የሰው ኀይሉ እንደ ሣር ደካማ ነው። (#በግእዝ፦ ናሁ ጸገዩ ጽጌያት። ናሁ ጸገዩ ጽጌ ደንጎላት። ኀለፈ ክረምት ቆመ በረከት። አውያን ጸገዩ ወበለስ አውፅአ ሠርፀ ጊዜ ገሚድ በጽሐ። ናርዶስ ጸገየ በውስተ ገነት። ቃለ ማዕነቅ ተሰምዐ በምድርነ። ናርዶስ ወሀበ መዓዛሁ ወዝናም ገብዐ በዕድሜሁ። አውያን ጸገዩ ወሮማን ፈረዩ። ዘተፈሥሐ በጊዜሁ የኀዝን ወዘኀዘነ በጊዜሁ ይትፌሣሕ ወዘነድየ በጊዜሁ ይብዕል ወዘብዕለ በጊዜሁ ይነዲ። ጽጌ ገዳምኒ በጊዜሁ የኀልፍ ወዘኢየኀልፍ አልቦ። ብዕሉሰ ለሰብእ ከመ ጽጌ ገዳም ወኀይሉሰ ለሰብእ ከመ ሣዕር ድኩም)።

**🌴ቅዱሳን🌴፦** የቅዱሳን መዓዛቸው በቆላ እንዳለ እንደ ሱፍ አበባ ነው። (#በግእዝ፦ መዓዛሆሙ ለቅዱሳን ከመ ጽጌ ደንጎላት ዘውስተ ቆላት)።

**♣ሰንበት♣፦** እግዚአብሔር አለ፦ ዕለተ ሰንበትን ቀደስኳት ከዕለታት ሁሉም ከፍ ከፍ አደረግኂት። ከዕለታት ሁሉ ሰንበት ትከብራለች። ይህቺ የክርስቲያን ሰንበት ታላቅ ናት። የሰላም አምላክ ክርስቶስ ሰንበትን ለዕረፍት ሠራ። (#በግእዝ፦ [ይቤ እግዚአብሔር] አነ ቀደስክዋ ለዕለተ ሰንበት ወአልዐልክዋ እምኵሉ ዕለት። እምኵሉ ዕለት ትከብር ሰንበት። ዛቲ ዕለት ዐቢይ ሰንበተ ክርስቲያን። አምላከ ሰላም ክርስቶስ ሠርዐ ሰንበተ ለዕረፍት)።

## 💗ጽጌ ዘዘወትር💗

**🌴ቤተክርስቲያን🌴፦** የቤተክርስቲያን መሠረቷና ምሰሶዋ የክብር ንጉሥ ክርስቶስ ነው። (#በግእዝ፦ ዐምዳ ወድዳ ለቤተክርስቲያን ክርስቶስ ውእቱ ንጉሠ ስብሐት)።

**🍃ነገረ ክርስቶስ🍃፦** የወልደ እግዚአብሔር ሥራው መልካም ነው። እንደሰው ፊት አይቶ የማያዳላ ከዓለም በፊት የነበረ ኢየሱስ ክርስቶስ የእውነት ፀሐይ ነው። መንግሥቱ የማይሻር ክርስቶስ ዘለዓለም ንጉሥ ነው። [ክርስቶስ ሆይ] የፍጥረት ሁሉ አስገኚው ፈጣሪው አንተ ነህ። አንተ ዓመታትን ሠራህ። ክረምትን ለዝናማት ሰጠህ መጸውን ለአበቦች ሰጠህ። የሰላም ንጉሥ ክርስቶስ ሆይ ሰላምህን ስጠን። የታላላቆች አባት የአዳም አምላክ ከአርያም በላይ በሰላም የምትኖር ነህ። (#በግእዝ፦ አዳም ግብሩ ለወልደ እግዚአብሔር። ፀሐየ ጽድቅ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘእምቅድመ ዓለም ሀሎ ከመ ገጸ ሰብእ ፍትሐ ዘኢያደሉ። ንጉሥ ውእቱ ዘለዓለም

ክርስቶስ ዘኢይሠዐር መንግሥቱ። አንተ ኬንያሁ ለኵሉ ፍጥረት። አንተ ሠራዕከ ዓመታተ። ክረምተ ወሀብከ ለዝናማት ወመጸወ ለጽጌያት። ንጉሠ ሰላም ክርስቶስ ሰላመከ ሀበነ። አበ ልዑላን አምላኩ ለአዳም ዘትነብር በሰላም መልዕልተ አርያም)።

**❧ትርጓሜ❧፦** ሁለቱ ጡቶቿ መንታነት እንዳላቸው እንደ ፌቆ ግልገሎች ናቸው። ሁለት ጡቶቿ የተባሉ የቤተክርስቲያን ሁለቱ ሕጎቿ ናቸው። (#በግእዝ፦ ክልዔ አጥባቲሃ ከመ ክልኤ ዕጕለ መንታ ዘወይጠል። ክልኤ አጥባቲሃ ክልኤ ሕግ ዘቤተክርስቲያን)።

**✿ሐተታ ተፈጥሮ✿፦** በምድራችን አበባ ታየ። ወይኖች አበቡ ሮማኖች አፈሩ። ምድር ከምታወጣው ፍሬ ሁሉ በረከትን የሰጠን አብን እናመሰግነዋለን። የዱር አበቦችን የሰጠን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። በደስታና በሰላም የዱር ፍሬዎችን እንልቀም። (#በግእዝ፦ ጽጌ አስተርአየ በውስተ ምድርነ አውያን ጸገዩ ወሮማን ፈረዩ። ነአኵቶ ለአብ ለዘጸገወነ በረከተ እምኵሉ ፍሬ ዘታወፅእ ምድር። ንሴብሖ ለእግዚአብሐር ለዘጸገወነ ጽጌያተ ገዳም። በፍሥሓ ወበሰላም ንዕርር ፍሬያተ ገዳም)።

## ✝ጥቅምት 12✝

**ቅዱስ ሚካኤል፦** የሁላችን አባት ሚካኤል ሊቅ ሆይ ስለኛ ፈጽመህ ለምንልን። በተቸገርን ጊዜ ቸል አትበለን ረዳት ሁነን እንጂ አትተወን። (#በግእዝ፦ ሚካኤል ሊቅ አበ ኵልነ ሰአል ወጸሊ በእንቲኣነ ረዳኤ ኩነነ ወኢትግድፈነ ወኢትትሐየየነ በዕለተ ምንዳቤነ)።

## ❖ዘአባ ሠርፀ ጴጥሮስ❖

**አባ ሠርፀ ጴጥሮስ፦** ብዙ የሆነውን ትዕግሥትህንና ትሕትናህን እናደንቃለን። ሠርፀ ጴጥሮስ የመንፈስ አባታችን ነው። በመንገዱ ሁሉ ሽንገላ የሌለበት ጻድቅና የዋህ እንዲሁም እንደተመረጠው ማቴዎስ ወንጌልን የሚሰብክ ነው። ሠርፀ ጴጥሮስ መንጋዎቹን ለመጠበቅ ሁልጊዜ የሚተጋና ሁልጊዜ የሚደክም እረኛ ነው። እንደ ጳውሎስ የሚያስተምር እንደ ጴጥሮስ ከአዳኝ ተኵላ አፍ በጎቹን የሚጠብቅ ነው። (#በግእዝ፦ ናስተበፅዕ ትሕትናከ ወብዙኀ ትዕግሥትከ። ሠርፀ ጴጥሮስ አቡነ አበ መንፈስነ። በኵሉ ፍናዊሁ ወበኵሉ ሑረታቲሁ ጻድቅ ወየዋህ ዘአልቦ ጽልሑት ሰባኬ ወንጌል ከመ ማቴዎስ ኅሩይ። ሠርፀ ጴጥሮስ ኖላዊ ለዐቂበ መርዔት ዘይተግህ ወትረ ወይጻሙ ዘልፈ። መገሥጽ ከመ ጳውሎስ ወከመ ጴጥሮስ ኖላዊ አባግዒሁ ዘየዐቅብ እምአፈ ተኵላ ነዓዊ)።

## ❤ጥቅምት 14 ዘአረጋዊ❤

**ጻድቃን፦** ጻድቃን ሆይ በጸሎታችሁ እንድን ዘንድ ለምኑልን። ደጋጎችና የዋሃን የከበሩ አባቶቻችን በመታመን ተጋድለው ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገሩ። ይህንን ኀላፊ ዓለም ጠልተው የናቁት አባቶቻችን ንዑዳን ክቡራን ናቸው። ስለሕይወትና ስለጽድቅ ሰውነታቸውን ለሞት

[አሳልፈው] ሰጡ። መከራን ተቀበሉ፣ ተራቡ፣ ተጠሙ፣ ተቸገሩም። በምድር ያለውን ንቀው በሰማያት ያለውን የማይጠፋውንና የማያረጀውን ተከተሉ። ከወርቅና ከብር ይልቅ ክርስቶስን አብልጠው በብዙ ድካም ተጋደሉ። የዚህን ዓለም መከራ ደስታ ያደረጉ አባቶቻችን ንዑዳን ክቡራን ናቸው። የሚጠብቁት የእግዚአብሔርን ጸጋ ተስፋ አድርገው የዚህን ዓለም መከራ ይረሣሉ። (#በግእዝ፦ ሰአሉ ለነ ጻድቃን ከመ ንድኀን በጸሎትክሙ። በተአምኖ ተጋደሉ ዐደዉ እሞት ውስተ ሕይወት ክቡራን አበዊነ ኄራን ወየዋሃን። ብፁዓን እሙንቱ አበዊነ እለ መነንዎ ወጸልዕዎ ለዝንቱ ዓለም ኀላፊ። መጠዉ ነፍሶሙ ለሞት በእንተ ጽድቅ ወሕይወት ሐሙ ርኀቡ ጸምዑ ወተመንደቡ። ዘበምድር መነኑ ዘበሰማያት ዴገኑ ኀበ ኢይበሊ ወኢይማስን። እስመ በብዙኀ ፃማ ተጋደሉ አብዲሮሙ ክርስቶስሀ እምወርቅ ወእምብሩር። ብፁዓን እሙንቱ አበዊነ እለረሰዩ ሕማመዝ ዓለም ትፍሥሕተ እስመ ቦሙ ይጸንሑ ጸጋ እግዚአብሔር ይረስዑ ሕማመዝ ዓለም)።

**ገብረ ክርስቶስ፦** ሰማያዊ ወታደር የሆነ ገብረ ክርስቶስ ሙሽራውን [ክርስቶስን] ተከትሎ በትዕግሥቱ ሰይጣንን አሸነፈው። ገብረ ክርስቶስ ክብርን ንቆ ሔደ ከችግረኞች ጋርም ኖረ። የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ አገኘ ዘንድ ጸልይልኝ። ጸሎትህ ቅድስት ናትና ለምንልኝ። እንደ ችግረኛ በአባትህ ደጅ ተቀመጥክ። የንጉሥ ቴዎዶስዮስ ልጅ ገብረ ክርስቶስ ንዑድ ክቡር ነው። (#በግእዝ፦ ወበሥነ ትዕግሥቱ ሞዖ ለአርዌ ገብረ ክርስቶስ ዘኮነ ሐራዌ ሰማያዌ ተሊዎ መርዓዌ። ወሖረ ገብረ ክርስቶስ መኒኖ ክብረ ምስለ ነዳያን ነበረ። ጸሊ ሊተ ከመ እርከብ ጸጋሁ ለመንፈስ ቅዱስ። ጸሊ ሊተ እስመ ጸሎትከ ቅድስት። ውስተ ዴዴ አቡከ ከመ ነዳይ ነበርከ። ብፁዕ ገብረ ክርስቶስ ወልደ ቴዎዶስዮስ ንጉሥ)።

**አረጋዊ፦** የገዳም ኮከብ የሆነው የአረጋዊ የሥራው ነገር በዓለም ተሰማ ተነገረ። (#በግእዝ፦ ደምፀ ወተሰብከ ውስተ ዓለም ዜና ምግባሩ ትሩፍ ለአረጋዊ ኮከበ ገዳም)።

## ❤ዘክብረ ቅዱሳን❤

**ነገረ ክርስቶስ፦** የጻድቃን መድኀኒታቸው ክርስቶስ ነው። የአባቶቻችን የቅዱሳን አምላካቸው ክርስቶስ ዓይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን [መንግሥተ ሰማያትን] ይሰጣቸዋል። (#በግእዝ፦ ክርስቶስ መድኀኒቶሙ ለጻድቃን። ዘዓይን ኢርእየ ወእዝን ኢሰምዐ ይሁቦሙ ዐስቦሙ ክርስቶስ አምላኮሙ ለአበዊነ ቅዱሳን)።

## ❖ጥቅምት 17 ዘእስጢፋኖስ❖

**እስጢፋኖስ፦** የክርስቶስ ሰማዕት እስጢፋኖስ ንዑድ ክቡር ነው። እስጢፋኖስ [በድንጋይ] ለወገሩት ይቅርትን ለመነ። ሕይወትንም ለመነላቸው። ስድብን ታገሠ። የሃይማኖት ምሰሶ እስጢፋኖስ ሆይ ጸሎትህ የመድኀኒት ወደብ ትሁነን። የሰማዕታት መጀመሪያ የዲያቆናት አለቃ ንዑድ ክቡር በሆነ በእስጢፋኖስ ጸሎት እንታመን፤ በዓሉን እናክብር መታሰቢያውንም እናድርግ። እስጢፋኖስ በአምላኩ ፍቅር ገድልን ተጋደለ። የአምላኩን ፈለግ በእውነት ተከተለ።

መልካም ገድልን ተጋድሏልና የአሸናፊነት የምስክርነት አክሊልን ገንዘብ አደረገ፡፡ በሃይማኖት አበባ ያጌጠ እስጢፋኖስ ንዑድ ክቡር ነው፡፡ ስለክርስቶስ ሰውነቱን አሳልፎ የሰጠ ሰማዕቱ እስጢፋኖስ ንዑድ ክቡር ነው፡፡ ሰማዕቱ እስጢፋኖስ ሆይ ዜናህ መድኀኒት ነው፡፡ በድንጋይ መወገርን በታገሠ በእስጢፋኖስ በዓል ዛሬ ደስታ ሆነ፡፡ ይህ ሰማዕት በመንፈስ ቅዱስ ያሸነፈ ነው፡፡ (#በግእዝ፦ ብፁዕ እስጢፋኖስ ሰማዕቱ ለክርስቶስ፡፡ እስጢፋኖስ ጸለየ ሕይወተ ሰአለ ሎሙ ሥርየተ ለእለ ወገርዎ አስተስረየ ሎሙ፡፡ እስጢፋኖስ ተዐገሠ ጽዕለተ፡፡ እስጢፋኖስ ዐምደ ሃይማኖት ጸሎትከ ትኩነነ መርሶ መድኀኒት፡፡ ንግበር ተዝካሮ ወናክብር በዓሎ ንትአመን ጸሎቶ ለብፁዕ እስጢፋኖስ ሊቀ ዲያቆናት መቅድመ ሰማዕት፡፡ እስጢፋኖስ በፍቅረ አምላኩ ተጋደለ ገድለ፡፡ አሰረ እግዚኡ በጽድቅ ዴገነ፡፡ አክሊለ ስምዕ ነሥአ ዘመዊዕ እስመ ተጋደለ ሠናየ ገድለ፡፡ ብፁዕ እስጢፋኖስ በጽጌ ሃይማኖት ሥርግው፡፡ ብፁዕ ሰማዕት እስጢፋኖስ ዘመጠወ ነፍሶ በእንተ ክርስቶስ፡፡ እስጢፋኖስ ሰማዕት ዜናከ መድኀኒት፡፡ ዮም ፍሥሓ ኮነ በበዓለ እስጢፋኖስ ውግረተ ዕብን ዕጉሥ፡፡ ዝንቱ ሰማዕት መዋዒ በመንፈስ ቅዱስ)፡፡

## ❤️ጥቅምት 21 ዘማርያም❤️

**ነገረ ማርያም፦** ሚልክያስም እግዚአብሔር በድንገት መጥቶ በአዳራሹ ያድራል አለ፡፡ [ድንግል ማርያምን] ሁሉም በየመዓርጋቸው አዲሲቷ ጊደር [ጥጃ] ማርያም ሆይ ሰላምታ ይገባሻል እያሉ ያመሰግኗታል፡፡ ትጉሃን ቅዱሳን ፈጽመው ያመሰግኗታል፡፡ ሰሎሞን መልካሚ ርግቤ ይላታል፡፡ የብርሃን ደጃፍ፣ የቃል መዝገብ፣ እውነተኛዋ ዕፀ ጳጦስ ናት፡፡ ከይሁዳ ወገን ለመድኀኒት የበቀለች የወይን ሐረግና የሱፍ አበባ ናት፡፡ የአፏ መዓዛ እንደ ሎሚ [እንደ እንኮይ] ነው፡፡ በሮማን ቅርፊትና በአሚናዳብ ሠረገላ መሰልኳት፡፡ የቅዱሳን መዓዛቸው የሕዝብ መድኀኒት የማትረግፍ አበባ ናት፡፡ ከንፈሮቿ እንደ ሮማን ቅርፊት ቀያይ ናቸው፡፡ የአማኑኤል እናት የድንግል ማርያም የልብሶቿ መዓዛ እንደ ነጭ ዕጣን ነው፡፡ የነገሯ ጣዕም ከወይን ይልቅ የሚጥም በእሾህ መካከል እውነተኛ የሃይማኖት አበባን ያበበች ናት፡፡ የሰማዕታት እናታቸው መልካሚ ማርያም ፈጣን ደመና ናት፡፡ ቅድስተ ቅዱሳን ይሏታል፡፡ በእሾህ መካከል ያለች እንኮይ ናት፡፡ ሰላማዊት ሆይ ሰላም ለአንቺ ይሁን፡፡ የልጅሽም ሰላም ከእኛ ጋር ይኑር፡፡ የጌታችን እናት የእኛም እናት ማርያም ሆይ ለምኝልን፡፡ (#በግእዝ፦ ሚልክያስኒ ይቤ እግዚአብሔርሰ ግብተ ይመጽእ ወየኀድር ውስተ ጽርሑ፡፡ ይዌድስዋ ኵሎሙ በበዕበዮሙ ወይብልዋ በሐኪ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ፡፡ ይዌድስዋ ትጉሃን ይቄድስዋ ቅዱሳን፡፡ ሰሎሞን ይቤላ ርግብየ ሠናይት፡፡ ዕፀ ጳጦስ እንተ በአማን መዝገቡ ለቃል አንቀጸ ብርሃን፡፡ ጽጌ ደንጎላት ሐረገ ወይን ዘእምነገደ ይሁዳ እንተ ሠረፀት ለመድኀኒት፡፡ መዓዛ አፉሃ ከመ ኮል፡፡ ከመ ቅርፍተ ሮማን አስተማሰልክዋ ሠረገላተ አሚናዳብ፡፡ ጽጌ እንተ ኢትትነገፍ መድኀኒተ ሕዝብ መዓዛሆሙ ለቅዱሳን፡፡ ቀይሕ ከናፍሪሃ ከመ ቅርፍተ ሮማን፡፡ ወዴና አልባሲሃ ከመ ዴና ስሒን ለማርያም ድንግል እሙ ለአማኑኤል፡፡ በማዕከለ አሥዋክ ዘጸገየት ጽጌ ጽጌ ሃይማኖት ዘበአማን ወጣዕመ ቃላ ይሤኒ እምወይን፡፡ ደመና ቀሊል፡፡ አዳም ወሠናይት እሞሙ ለሰማዕት ማርያም፡፡

ይብልዋ ቅድስተ ቅዱሳን:: ኮል በማዕከለ አሥዋክ:: ሰላማዊት ሰላም ለኪ:: ሰላመ ወልድኪ የሀሉ ምስለ ኵልነ:: ማርያም እምነ ወእሙ ለእግዚእነ ሰአሊ ለነ)::

## ❢ጥቅምት 22 ዘሉቃስ❢

**ነገረ ክርስቶስ፦** የነቢያት መመኪያቸው የሐዋርያት ጌጣቸው የዘለዓለም ዕረፍትና በመስቀሉ ለሁሉ የሚያበራው ክርስቶስ ነው:: (#በግእዝ፦ ምክሖሙ ለነቢያት ሠርጎሙ ለሐዋርያት ክርስቶስ ውእቱ ዘለዓለም ዕረፍት ዘበመስቀሉ ያበርህ ለኵሉ)::

## ❤ጥቅምት 28 ዘአባ ይምዓታ❤

**አባ ይምዓታ፦** የእግዚአብሔር ሰው ክቡር አባ ይምዓታ ሆይ ያለድካምና ያለሕመም በሰላም እንኖር ዘንድ ስለእኛ ወደ መድኀኒታችን ክርስቶስ ለምንልን:: (#በግእዝ፦ አባ ይምዓታ ክቡር ብእሴ እግዚአብሔር ጸሊ በእንቲኣነ ኀበ ክርስቶስ መድኀኒነ ከመ ነሀሉ በሰላም እንበለ ፃማ ወድካም እንበለ ደዌ ወሕማም)::

**ጻድቃን፦** የጻድቃን ብርሃናቸው አይጠፋም:: በገድላቸውና በትዕግሥታቸው ፊታቸው ከፀሐይ ይልቅ ያበራል:: (#በግእዝ፦ ኢይጠፍዕ ብርሃኖሙ ለጻድቃን:: በገድሎሙ ወበትዕግሥቶሙ እምፀሐይ ይበርህ ገጾሙ)::

**ነገረ ክርስቶስ፦** የጻድቃን ክብራቸው የዓለም ሁሉ ቤዛ ክርስቶስ ነው:: (#በግእዝ፦ ክብሮሙ ለጻድቃን ክርስቶስ ቤዛ ኵሉ ዓለም)::

## ❤ኅዳር 3 ዘዕንባቆም❤

**ዕንባቆም፦** ዕንባቆም ከነቢያት ይልቅ ፊቱ የሚያበራ፣ ሁልጊዜ ደስተኛ፣ አንደበቱ የተሳለ፣ ቁመቱ ረጅም፣ በደረቱ ላይ ጺሙ የወረደ ነው:: በጻድቅ ጸሎት ሀገር ሳትጠፋ ትድናለችና የእግዚአብሔር ነቢያት ሆይ ሁልጊዜ በጸሎታችሁ ተራዱን:: (#በግእዝ፦ ዘለዓለም ፍሡሕ ገጹ ብሩህ እምነቢያት ልሳኑ በሊሕ ዘለቆሙ ነዊኅ ዲበ እንግድዓሁ ጽሕሙ ስፉሕ:: ነቢያተ እግዚአብሔር ተራድኡነ ወትረ በጸሎትክሙ እስመ በጸሎተ ጻድቅ ትድኀን ወኢትማስን ሀገር)::

**ነገረ ክርስቶስ፦** [ክርስቶስን] ዳዊት ጠል በጸምር እንደሚወርድ ነው አለው:: ኢሳይያስ ደግሞ በሚያምር የሥጋ ልብስ ከኤዶም የሚወጣ የሚያምር ነው አለው:: ዕንባቆምም እግዚአብሔር ከቴማን ይመጣል ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ይመጣል አለ:: በመጀመሪያ ነቢያት ሰበኩት ሐዋርያት ከድንግል ማርያም ሰው ከመሆኑ የተነሣ በእጃቸው ዳሰሱት:: ነቢያት በማወቅ ቀደሙ:: ሐዋርያትም የወልደ እግዚአብሔርን ፈለጉን ተከተሉ:: (#በግእዝ፦ ዳዊትኒ ይቤ ከመ ጠል ውስተ ጸምር:: ኢሳይያስኒ ይቤ መካሕ ዘይወፅእ እምኤዶም በአጽፊ ባሶር ግሩም:: ዕንባቆምኒ ይቤ እግዚአብሔርሰ እምቴማን ይመጽእ ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን:: ነቢያት

እምቅድም ሰበክዎ ሐዋርያት በእድ ገሠሥዎ እማርያም ተሠጊዎ። ነቢያት ቀደሙ አእምሮ ሐዋርያት ተለዉ አሰሮ ለወልደ እግዚአብሔር)።

## ኅዳር 5 ዘአባ ዮሐኒ

**አባ ዮሐኒ፦** ይህ ሰው አኗኗሩ እንደ ዮሐንስ በዱር የሆነ የእግዚአብሔር ሰው ነው። አባ ዮሐኒ የሰማዩን ዋጋ ተስፋ አድርጎ በዚህ ዓለም ቤትን አልሠራም። በተራሮች ኖረ በበዓታትም ተንከራተተ። በእርሱ ላይ የኢዮብ ትዕግሥት ነበረ። አባ ዮሐኒ ሆይ ወደ ጻድቃን መንገድ ምራኝ። ንጹሕ ልብን ገንዘብ ላደረገ በገነት እንስሳት አራዊት አዕዋፋት ለአዳም እንደታዘዙት፤ ለዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ እንደታዘዙት፣ ለኖኅ በመርከብ ውስጥ እንደታዘዙት ሁሉ ይታዘዙለታል። በመልካም ሥራ ገድሉን የፈጸመ አባ ዮሐኒ ንዑድ ክቡር ነው። በትዕግሥትና በሰላም ጻድቃን ወደሚዋረሷት ወደ ብሔረ ሕያዋን ተሻገረ። አባ ዮሐኒ ሕይወትን አበበ። ሠላሳ ስሳ መቶ [ፍሬን] አፈራ። ድንገት ወደ ብሔረ ሕያዋን ተነጠቀ። አባ ዮሐኒ እግዚአብሔር የወደደውና ክንፍን እንደ ንስር የሰጠው ነው። በምድር እየተመላለሰ ሕይወቱ እንደ መላእክት ይመስላል። ንብ የዱር አበቦችን እንደሚሰበስብ እንዲሁ አባ ዮሐኒ ከቅዱሳን ሁሉ ጽድቅን ይሰበስባል። በእምነቱ እንደ ኖኅ በትዕግሥቱ እንደ ኢዮብ ነው። እንደ ሳሙኤል ከትንሽነቱ ጀምሮ በቤተ እግዚአብሔር የኖረ ነው። (#በግእዝ፦ ዝንቱሰ ብእሲ ብእሴ እግዚአብሔር ዘኮነ ንብረቱ ገዳም ከመ ዮሐንስ። አባ ዮሐኒ በዝ ዓለም ኢሐነፀ ቤተ ነበረ አድባረ ዔለ በዓታተ እንዘ ይጸንሕ ዘላዕሉ ዕሴተ። ወቦ ላዕሌሁ ዘኢዮብ ትዕግሥተ። አባ ዮሐኒ ውስተ ፍኖተ ጻድቃን ምርሐኒ። ለዘአጥረየ ልበ ንጹሐ ኵሉ ይትኤዘዝ ሎቱ በከመ ተአዘዝዎ ለአቡነ አዳም {እንስሳት፣ አራዊት፣ አዕዋፋት...} በውስተ ገነት ወለዳንኤል በግበበ አናብስት ወለኖኅ በውስተ ታቦት። ብፁዕ ውእቱ አባ ዮሐኒ ዘፈጸመ ገድሎ በምግባረ ጽድቅ። በትዕግሥት ወበሰላም ዐደወ ምድረ ሕያዋን እንተ ይትዋረስዋ ጻድቃን። አባ ዮሐኒ ጸገየ ሕይወተ ፈረየ ሠላሳ ወስሳ ወምእተ ብሔረ ሕያዋን ተመስጠ ግብተ። አባ ዮሐኒ ዘአፍቀሮ እግዚአብሔር ዘወሀቦ እግዚኡ ክንፈ ከመ ንስር። እንዘ በምድር ያንሶሱ ከመ መላእክት ይመስል ሕይወቱ። ወከመ ንሕብ ዘያስተጋብዕ ጽጌያተ ገዳም። ወከማሁ አባ ዮሐኒ ያስተጋብእ ጽድቀ ዘእምኵሎሙ ቅዱሳን። ከመ ኖኅ በእምነቱ ወከመ ኢዮብ በትዕግሥቱ። ከመ ሳሙኤል ዘሐይወ እምንእሱ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር)።

**ጻድቃን፦** ጻድቃን በእምነት ተስፋቸውን ወረሱ። በእምነት በሰማያት ተስፋን አገኙ የእሳትን ኀይልም አጠፉ። በሰማዕትነት ጊዜ የሰይጣንን ጦር ያሸንፉ ዘንድ በአሸናፊው አምላካቸው በክርስቶስ ስም ሰማዕት ከአምላካቸው ክርስቶስ ጋር ፊታቸውን አማትበው ይገባሉ። በጾም በጸሎትና በብዙ ምጽዋት ቀደምት አባቶች ዳኑ። (#በግእዝ፦ በተአምኖ ወረሱ ተስፋሆሙ ጻድቃን። በተአምኖ አድምዑ ተስፋ በሰማያት ወአጥፍዑ ኀይለ እሳት። ይበውኡ ሰማዕት በውስተ ስምዕ ምስለ ክርስቶስ አምላኮሙ ይበውኡ ወየአትቡ ገጾሙ ውስተ ስምዕ ከመ ይማዑ ጸብዖ ለሰይጣን በስመ ክርስቶስ አምላኮሙ መዋዒ። በጾም ወበጸሎት ወበብዙኀ ምጽዋት ድኅኑ አበው ቀደምት)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** [ክርስቶስ] ለባሮች ነጻነት፣ ለደካሞች ኀይል፣ ለሚፍገመገሙ ደግሞ መጽኛቸውና ምርኩዛቸው ነው። (#በግእዝ፦ ለአግብርት ግዕዛን ኀይሎሙ ለድኩማን ክርስቶስ ምርጕዞሙ ወጽንዖሙ ለእለ ይተነተኑ)።

## ❤ኅዳር 6 ዘቍስቋም❤

**ነገረ ማርያም፦** ራሱ ልዑል የሠራት ድንኳን እነኋት። እርሱ ተሸክሟት ሳለ እንዴት ተሸከመችው! የመለኮት እሳት አላቃጠላትም። ዘወትር በወርቅ የሚከድኗት በውስጧ ሕግ ያለባት ታቦት ናት። የሰማዕታት እናታቸው አደረጋት። የመላእክት እኅት ብሎ ጠራት። በምድር የምትመላለስ ሰማያዊት ናት። (#በግእዝ፦ ነያ ደብተራ እንተ ለሊሁ ልዑል ገብራ እፎ ጾረቶ እንዘ ውእቱ ይጸውራ ኢያውዐያ እሳተ መለኮት። ታቦት እንተ ውስቴታ ኦሪት ውቱረ ይከድንዋ በወርቅ። እሞሙ ለሰማዕት ረሰያ ወእኅቶሙ ለመላእክት ሰመያ ሰማያዊት እንተ በምድር ታንሶሱ)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** የቅድስት ማርያም ልጅ ሰፊ የሆነች መንግሥቱ ከዓለም በፊት የነበረች ናት። ከግሩማን ይልቅ ግሩም ነው። የማይጨልም የሕይወት ብርሃን ነው። በአርያም የሚመሰገን እርሱ በቍስቋም ተራራ አደረ። (#በግእዝ፦ መንግሥቱ ሰፋኒት ዘእምቅድመ ዓለም ወልደ ቅድስት ማርያም። ግሩም እምግሩማን ብርሃነ ሕይወት ዘኢይጸልም ኀደረ ደብረ ቍስቋም ዘይሴባሕ በአርያም)።

## ❤ኅዳር 7 ዘጊዮርጊስ❤

**ቅዱስ ጊዮርጊስ፦** በእሳት ባሕር ውስጥ የነበሩ ኃጥኣን የእግዚአብሔር ቅዱሱ ጊዮርጊስ ሆይ ለምንልን እያሉ ማለዱት። ሰማዕቱ ጊዮርጊስ በርትቶ በትዕግሥት አሸነፈ። ቤተክርስቲያን በእውነት የሚጋደል ነው እያለች ታመሰግነዋለች። አባ ጊዮርጊስ ሆይ ሰይጣን እንዳያሸንፈን ለምንልን። የክብር ኮከብ ጊዮርጊስ ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን። የሰማዕታት አለቃ የሆነ ኮከብ ጊዮርጊስን ቀጰዶቅያ ወለደች። (#በግእዝ) አስተብዕዕዎ ወይቤልዎ እለ ይነብሩ ፈለገ እሳት ሰአል ለነ ጊዮርጊስ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር። ጊዮርጊስ ሰማዕት ኀየለ ወሞዐ በትዕግሥት። ትዌድሶ ቤተክርስቲያን ወትብል መስተጋድል ዘበአማን። አባ ጊዮርጊስ በእንቲኣነ ጸሊ ከመ ኢይምዐነ ማኅጎሊ። ኮከበ ክብር ጊዮርጊስ በሐ። ቀጰዶቅያ ወለደት ኮከበ ጊዮርጊስሀ ለሰማዕታት መክብበ)።

## ❤ኅዳር 8 ዘ፬ቱ እንስሳ❤

አርባዕቱ እንስሳ፦ የእውነት አምላክን በአንድ ላይ ያመሰግኑታል። በሚሔዱ ጊዜ አይተያዩም። አንዱ ወዳመለከተበት ይሔዳሉ። በእግዚአብሔር ትእዛዝ ይጓዛሉ። ሁልጊዜም እርሱን ፈጽመው ያመሰግናሉ። ሲያመሰግኑ የመላእክትን ቃል በሰሙ ጊዜ ሰማይ ደስ ይለዋል ምድርም ትደሰታለች። የዱር ዕፀዋት ሁሉ ደስ ይላቸዋል። [ኪሩቤል] ለዓለም ሁሉ የሚለምኑ የእግዚአብሔር ዙፋኖች ናቸው። አራቱ እንስሳ ቃላቸው የተካከለ ነው። አኗኗራቸውም አንድ

ነው። እርሱ ራሱ ተሸክሟቸው የጌታቸውን ዙፋን ይሸከማሉ። ከመላእክት ሁሉ የአራቱ ኪሩቤል ክብር ይበልጣል። የማይተኙ ትጉሃን መላእክት በየሥርዓታቸው በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን በምድርም ሰላም እያሉ አሰምተው ይናገራሉ [ያመሰግናሉ]። ገጸ ሰብእና ገጸ እንስሳ ገጸ ንስርና ገጸ አንበሳ ለበደላችን ይቅርታን ለምኑልን። ሁልጊዜ የሚጣፍጥ ምስጋናን ያሳርጋሉ። መላእክትና ሊቃነ መላእክት በማያቋርጥ አንደበት ልዑልን ያመሰግናሉ። እሳትን ለሚጎናጸፍ ድካም የሌለበት ምስጋናን ያሳርጋሉ። መላእክት ወደ ምድር በሚወርዱ ጊዜ ድምፅ የላቸውም። የክንፋቸው ድምፅ አይሰማም። ለእግራቸው ዱካ አሰር የለውም። ሩጫቸው ከነፋሳት ይልቅ ይፈጥናል። (#በግእዝ፦ ኅቡረ ይባርክዎ ለአምላከ ጽድቅ። ሶበ ይሠሩ ኢይትናጸሩ ኀበ አንጸረ ቀዳማዊ የሐውሩ። ወየሐውሩ በኵሉ ትእዛዙ ለእግዚአብሔር። ወዘልፈ ኪያሁ ይሴብሑ ወይቄድሱ። ይትፌሣሕ ሰማይ ወትትሐሰይ ምድር ወይትሐሰዩ ኵሉ ዕፀወ ገዳም ሶበ ይሰምዑ ቃለ መላእክት እንዘ ይሴብሑ። መተንብላን ለኵሉ ዓለም መናብርቲሁ ለእግዚአብሔር። አርባዕቱ እንስሳ ዕሩይ ቃሎሙ ወኅቡር ህላዌሆሙ ይፀውሩ መንበሮ ለእግዚኦሙ እንዘ ውእቱ ይጸውሮሙ በመንፈስ። እምኵሎሙ መላእክት የዐቢ ክብሮሙ ለአርባዕቲሆሙ። ትጉሃን እለ ኢይነውሙ መላእክት በበሥርዓቶሙ ይጸርሑ ወይብሉ ስብሐት ለእግዚአብሔር በአርያም ወሰላም በምድር። ገጸ ሰብእ ወገጸ እንስሳ ገጸ ንስር ወገጸ አንበሳ ሰአሉ ለነ ሥርየተ አበሳ። ይቄድሱ ቅዱሰ ኵሎ አሚረ ሰብሐተ መዓርዒረ የዐርጉ ወትረ። መላእክት ወሊቃነ መላእክት ይሴብሕዎ ለልዑል በዘኢያረምም አፍ። ለዘይትዐፀፍ እሳተ የዐርጉ ስብሐተ ዘአልቦ ጽርዐት። ሶበሰ ይወርዱ መላእክት ዲበ ምድር አልቦሙ ድምፅ ወኢይሰማዕ ድምፀ ክነፊሆሙ ወአልቦ አሰር ለምክያዳተ እገሪሆሙ። ይቀልል ሩፀቶሙ እምነፋሳት)።

**እግዚአብሔር፦** የዘለዓለም ንጉሥ አቤቱ ቃልህ አይታበልም መንግሥትህም አይሻርም። ስምህ የተመሰገነ ነው። ምሕረት በእጅህ አለ። ፊት አይተህ የማታዳላ በትክክል የምትፈርድ ነህ። ትጉሃን መላእክት ከቃልህ የተነሣ ይንቀጠቀጣሉ። ከአፍህ የነበልባል ኀይል ይወጣል። በትእዛዝህ የሚኖሩ የብዙ ብዙ የሚሆኑ መላእክቶችህ ፈጽመው ያመሰግኑሀል። በህልውናህ ሥውር ነህ። መንበርህን የሚሸከሙት ቦታህን [ባሕርይህን] አያውቁም። በትጉሃን አንደበት የሚመሰገን ክርስቶስን ፈጽመን እናመሰግነዋለን። (#በግእዝ፦ ኢይትሔሰው ቃልከ ወኢይሠዐር መንግሥትከ እግዚኦ ንጉሥ ዘለዓለም። ስቡሕ ስምከ። ዘበርቱዕ ትኴንን ወኢታደሉ ለገጽ ምሕረት ውስተ እዴከ። ነበልባለ ኀይል ይወፅእ እምአፉከ ትጉሃን መላእክት ይርእዱ እምቃልከ። አእላፈ አእላፋት መላእክቲከ እለ የሐውሩ በትእዛዝከ የአኵቱከ ወይሴብሑከ። ሥውር አንተ በህላዌከ እለ ይጸውሩ መንበረከ ኢያእመሩ መካነከ። ንሴብሕ ወንዜምር ክርስቶስሀ በአፈ ትጉሃን ዘተሰብሐ)።

## ❤ኅዳር 11 ዘሐና❤

**ሐና፦** ሐና ሆይ የቅዱሳን አባቶችሽ ተስፋ በልጅሽ ተፈጸመ። ከጊዜ በፊት የነበረውን ቃልን የወለደች ድንግልን ወልዳታለችና ሐና ከሴቶች ሁሉ ትበልጣለች። ልጇ አንበሳዊት የሆነች መንፈሳዊት ነቢይት ናት። ሐና የሕይወት አበባን አበበች። (#በግእዝ፦ ተፈጸመ ሐና በወለትኪ

ተስፋ ቅዱሳን አበውኪ። ሐና እምአንስት ተዐቢ ወትትሌዐል እስመ ወለደታ ለድንግል ዘወለደት ቃለ ዘሀሎ እምቅድመ መዋዕል። ነቢይት መንፈሳዊት ብእሲት ዘዕጎልታ አንበሳዊት። ጸገየት ሐና ጽጌ ሕይወት)።

**ነገረ ማርያም፦** ኢሳይያስ ያማረ ሰው የኤዶም ገነት ይላታል። ማርያም ንጹሕ የመና ሙዳይ ናት። (#በግእዝ፦ ኢሳይያስኒ ይቤላ ገነተ ኤዶም ዘብእሲ መካሕ። ማርያም ይእቲ ሙዳየ መና ንጹሕ)።

## 💢ኅዳር 12 ዘሚካኤል💢

**ቅዱስ ሚካኤል፦** ሚካኤል በእስራኤል ከተማ ፊት እየሔደ ሌሊቱን ሁሉ በእሳት ብርሃን ቀኑን ደግሞ በደመና መራቸው። የምሕረት መላእክት ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ሱራፌል፣ ኪሩቤል፣ ዑራኤል፣ ሩፋኤል፣ ብርናኤል፣ አቅናኤል፣ ሱባኤል፣ ፍናኤል፣ ሰላትያኤል፣ ሰዳትያኤል፣ ሰላታኤል፣ ሰዳካኤል እና ኤልናኤል ለምሕረት የተዘጋጃችሁ ናችው። [ሚካኤል ሆይ] በዐሥራ አራቱ ታላቅ ልመናህና በድንቅ ትሕትናህ ማልድልን። እነሆ ስሙ ሚካኤል የሆነ መልአክ የመላእክት አለቃቸው ነው። የክብር ንጉሥ [ክርስቶስ] ስለምሕረት የሚለምን የመላእክት አለቃ ሚካኤልን የመላእክት አለቆች አለቃ አደረጎ ከፍ ከፍ አደረገው። ሚካኤል ለሰው ምሕረትን ይለምናል። ኃጢአትንም ያስተሠርያል። የመላእክት አለቃ ሚካኤል ስለሙሴ ሥጋ ከሰይጣን ጋር በተነጋገረ ጊዜ የስድብን ቃል ይናገር ዘንድ አልደፈረም። ይህ ሚካኤል ሹመቱ ከፍ ያለ መልአከ ኀይል ነው። ለእኛ ይለምንልን ረዳትም ይሁነን። በችግራችን ጊዜ ክንፉን ዘርግቶ በእኛ ላይ ይጋርድልን። ይህ የመላእክት አለቃቸው ነው። ስሙም ሚካኤል ነው። ዐይኑ የርግብ፣ ልብሱ የመብረቅ የወርቅ ሐመልማል ነው። ሚካኤል ማለት ድንቅ ነገር ማለት ነው። ገብርኤል ማለት የእግዚአብሔር ልጅ ማለት ነው። (#በግእዝ፦ መርሖሙ መዓልተ በደመና ወኵሎ ሌሊተ በብርሃነ እሳት እንዘ ሚካኤል የሐውር ቅድመ ትዕይንቶሙ ለእስራኤል። ሚካኤል ወገብርኤል ሱራፌል ወኪሩቤል ዑራኤል ወሩፋኤል ብርናኤል አቅናኤል ሱባኤል ወፍናኤል ሰላትያኤል ሰዳትያኤል ሰላታኤል ሰዳካኤል ኤልናኤል መላእክተ ምሕረት እለ ድልዋን ለሣህል። በዐሠርቱ ወአርባዕቱ ትንብልናከ ዐቢይ ልዕልናከ በመንክር ትሕትናከ አስተምሕር ለነ። ወነዋ መልአክ ሚካኤል ስሙ ለመላእክት ውእቱ ሊቆሙ። አዕበዮ ንጉሠ ስብሐት ለሚካኤል ሊቀ መላእክት ዘይስእል በእንተ ምሕረት መልአከ ሥረዊሆሙ ለመላእክት። ሚካኤል ይስእል ምሕረተ ለሰብእ ወያስተሠሪ ኀጢአተ። ወሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ይትበሀሎ ለሰይጣን በእንተ ሥጋሁ ለሙሴ ኢተኀበለ ቃለ ጽርፈት ይንብብ። ውእቱ ሚካኤል መልአከ ኀይል ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር ይስአል ለነ ረዳኤ ይኩነነ አመ ምንዳቤነ ሰፊሖ ክነፊሁ ይጸልል ዲቤነ። ውእቱ ሊቆሙ ወመልአኮሙ ሚካኤል ስሙ ዐይኑ ዘርግብ ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ። ሚካኤል ብሂል ዕፁብ ነገር። ገብርኤል ብሂል ወልደ እግዚአብሔር)።

## †ኅዳር 13 ዘአእላፍ†

**እግዚአብሔር፦** እግዚአብሔር በአርያሙ [በከፍታው] ድንቅ ነው። መላእክት [እርሱን] ማየትን ይመኛሉ። [እግዚአብሔር] የመላእክት ፈጣሪ፣ የሁሉ አባት፣ የዓለም ጌጥ፣ የማያልቅ ደስታ ነው። አኗኗራችን በጸጥታ ይሆን ዘንድ አቤቱ አምላካችን ሆይ እንማልድሀለን እንለምንሀለን። (#በግእዝ፦ መንክር እግዚአብሔር በአርያሙ መላእክት ይትሜነዩ ርእዮቶ። ገባሬ መላእክት አበ ኵሉ ሠርጎ ዓለም ፍሥሓ ዘኢየኀልቅ። ንስእለከ እግዚኦ አምላክነ ወናስተበቊዐከ ከመ በጽሙና ይኩን ንብረትነ)።

**መላእክት፦** የእግዚአብሔር መላእክት ፊታቸው ከፀሐይ ይልቅ ሰባት እጅ ያበራል። ሰውና መላእክት ማኅበራቸው አንድ ነው። በክርስቶስ መስቀል ምክንያት በአንድ የሚሰማሩ አንድ መንጋ ሆኑ። የመላእክት አለቃ ሚካኤል የእግዚአብሔር የምክር መልአክ [አማካሪ] / የኪዳን መልአክ ነው። (#በግእዝ፦ ምስብዒተ ይበርህ ገጾሙ እምፀሐይ ለመላእክተ እግዚአብሔር። መላእክት ወሰብእ አሐዱ ማኅበሮሙ በእንተ መስቀሉ ለክርስቶስ አሐደ መርዔተ ኮኑ። ሚካኤል ሊቅ ሊቀ መላእክት መልአከ ምክሩ መልአከ ኪዳኑ ለእግዚአብሔር)።

## 💖ዘዘወትር💖

**ሚካኤል፦** ምድር በሚካኤል ጸሎትና ልመና ታድራለች። ስለፍጥረት ሁሉ ይለምናል። የሚያስፈራ ባሕርን እንደ ግድግዳ አቁሞ በመካከሉ መንገድን አሳየ። ከመላእክት ሁሉ ዙፋኑ በክብር ይበልጣል። የሚካኤልን ታላቅነት ተመልከቱ። በደግነቱ ከመላእክት ይልቅ ከፍ ከፍ አደረገው። (#በግእዝ፦ በጸሎቱ ወበስእለቱ ለሚካኤል ተኀድር ምድር። ይስእል ወይተነብል በእንተ ኵሉ ፍጥረት። ባሕረ ግርምተ ገብረ አረፍተ ወበውስቴታ አርአየ ፍኖተ። እምኵሎሙ መላእክት ይትሌዐል መንበሩ በክብር። ርእዩ ዕበዮ ለሚካኤል ልዑለ ረሰዮ በኂሩቱ አዕበዮ እመላእክት)።

## 💖ኅዳር 15 ዘሚናስ💖

**ሚናስ፦** ይህ ሚናስ ቀድሞ የንጉሥ ጭፍራ [ወታደር] ነበር። አሁን ግን የክርስቶስ ጭፍራ [ወታደር] ሆኗል። [ሚናስ] ስለመንግሥተ ሰማያት በምድር ያለ ሕይወቱንና ክብሩን የናቀ ነው። ይህ ሚናስ ሁሉ ኀላፊ ጠፊ መሆኑን አውቆና የዚህን ዓለም ሽልማት ንቆ ስለእውነት ተጋደለ። ይህ ሚናስ የዋህና እውነተኛ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ክርስቲያን ነኝ እያለ አሰምቶ ተናገረ። ሚናስ በሰማይ አዳራሽ የተመረጠ ነው። ከገንዘብ ይልቅ ጽድቅን የመረጠ ነው። (#በግእዝ፦ ዝንቱሰ ሚናስ ቀዳሚ ሀሰ ሐራ ዘንጉሥ ይእዜሰ ኮነ ሐራ ዘክርስቶስ። ዘመነነ ክብረ ዘበምድር በሕይወቱ በእንተ መንግሥተ ሰማያት። ዝንቱሰ ሚናስ ዘተጋደለ በእንተ ጽድቅ መኒኖ ትርሲቶ ለዝንቱ ዓለም አእሚሮ ከመ ኵሉ ኀላፊ ውእቱ። ዝንቱሰ ሚናስ ጻድቅ ወየዋህ ውእቱ ጸርሐ እንዘ ይብል ክርስቲያናዊ አነ ሕዝበ እግዚአብሔር። ሚናስ ኅሩይ በታዕካ ሰማይ። ጽድቀ ዘአብደረ እምነ ንዋይ)።

**ጻድቃን፦** ለጻድቃን ሞገስ አላቸው። (#በግእዝ፦ ለጻድቃን ቦሙ ሞገስ)።

## ኅዳር 17 ዘወለተ ጴጥሮስ

**ወለተ ጴጥሮስ፦** [ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ሆይ] ሁሉ እንደ በደለኛ ገፉሽ። በንጉሥ ፊትም አቆሙሽ። የኬፋ ልጅ አንቺ ግን ስለዚህ ተስፋሽን አላጣሽም። ንጽሕት ወለተ ጴጥሮስ ሆይ ስለጽድቅሽ በየዓመቱ ካህናት ለአንቺ ማሕሌትን ይዘምራሉ። (#በግእዝ፦ ገፍዑኪ ኲሉ ከመ ዕቡስ ወአቀሙኪ ቅድመ ንጉሥ። አንቲሰ ወለቱ ለኬፋ ወበእንተዝ ኢኀጣእኪ ተስፋ። ማሕሌተ ለኪ ይዜምሩ ካህናት በእንተ ጽድቅኪ ለለዓመት ወለተ ጴጥሮስ ንጽሕት)።

## ኅዳር 21 ዘማርያም

**ካህናት፦** ከዓለም በፊት ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ምድርን ያለካህናትና ያለ ዲያቆናት አልተዋትም። (#በግእዝ፦ ኢኀደጋ ለምድር እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም እንበለ ካህናት ወዲያቆናት)።

**ቤተክርስቲያን፦** ዘካርያስ ሁለንተናዋ የወርቅ የሆነ፣ በቀኝና በግራዋ የዘይት ቅርንጫፎች ያሉባት፣ ሰባት መብራቶችና ሰባት ቧንቧዎች በላዩዋ ያለባት የብርሃን መቅረዝን አየ። ይህቺም ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት። ዕዝራም በሴት አምሳል አያት። ይህቺም እናታችን ቤተክርስቲያን ናት። (#በግእዝ፦ ዘካርያስ ርእየ ተቅዋመ ማኅቶት እንተ ኲለንታሃ ወርቅ በየማና ወበጸጋማ አዕፁቀ ዘይት ሰብዓቱ መኃትዊሃ ወሰብዓቱ መሣውር ዘዲቤሃ። ዛቲ ይእቲ ቅድስት ቤተክርስቲያን። ዕዝራኒ ርእያ በርእየተ ብእሲት እምነ ይእቲ ቤተክርስቲያን)።

**ነገረ ማርያም፦** ሕዝቅኤል የተዘጋች ምሥራቅ አላት፣ ዘካርያስ መቅረዝ አላት። የኤልሳዕ ማሰሮ የኢያሱ የምስክርነት ሐውልት፣ የዳዊት ፀምር ናት። ሰሎሞን የዘመረልሽ የጳዝዮን ዕንቊ ጽዮን ሆይ ደስ ይበልሽ ደስ ይበልሽ። ስለእርሷ ቅዱሳን ነቢያት ምሳሌን የተናገሩላት ማርያም ይህቺ ናት። የኖኅ መርከብ፣ ነጭ ፀምር፣ የታተመች ጉድጓድ ናት። ማርያምስ ከጥንት ጀምሮ በአዳም ባሕርይ እንደ ነጭ ዕንቊ ታበራ ነበር። [እግዚአብሔር] ስለእርሷና ስለዘመዶቿ በእንጨት ላይ ተሰቀልኩ አለ። (#በግእዝ፦ ሕዝቅኤል ይቤላ ዕፁት ምሥራቅ ዘካርያስ ይቤላ ተቅዋም። ዘኤልሳዕ ቀሱት ዘኢያሱ ስምዐ ሐውልት ፀምር ዘዳዊት። አብርሂ አብርሂ ጽዮን ዕንቊ ዘጳዝዮን ዘሐለየኪ ሰሎሞን። ዛቲ ይእቲ ማርያም እንተ በላዕሌሃ አስተማሰሉ ቅዱሳን ነቢያት ታቦት እንተ ኖኅ ፀምር ጸዓዳ፣ ዐዘቅት ኅትምት። ማርያምሰ ተሐቱ እምትካት ውስተ ከርሡ ለአዳም ከመ ባሕርይ ጸዓዳ እስመ በእንቲኣሃ ወበእንተ አዝማዲሃ ተሰቀልኩ ዲበ ዕፅ ይቤ)።

## ኅዳር 24 ዘካህናተ ሰማይ

**ካህናት፦** [አቤቱ] የታመኑ ካህናቶችህ ፈጽመው ያመሰግኑሀል። ንጹሕ መሥዋዕትንም ያሳርጉልሀል። ካህናትን ዕንቊ አላቸው። እጆቻቸው እሳትን ይዳስሳሉ። በአባቱ ፊት ወልድን ይሠዉታል። ማዕጠንታቸውም እጅግ ይወደዳል። ካህን በተጋ ጊዜ ብርሃን ለዓለም ሁሉ ተገለጠ። የጻድቃን ፍጹም ደስታቸው ቤተክርስቲያንም ተቀደሰች። ካህናት በመንፈስ ቅዱስ

አጋዥነት የምስጋና መሥዋዕትን ያሳርጋሉ፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ካህናት ሆይ ጸልዩልን፡፡ እናንተን የአማልክት ልጆች ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ ይላችኋልና፡፡ (#በግእዝ፦ ካህናቲከ ምእመናኒከ የአኰቱከ ወይሴብሑከ መሥዋዕተ ንጹሐ የዐርጉ ለከ፡፡ ለካህናት ሰመዮሙ መረግደ እደዊሆሙ ይገሣ ነደ በቅድመ አቡሁ ይሠውዑ ወልደ ወማዕጠንቶሙ ይትፌቀር ፊድፋደ፡፡ ሶበ ይነቅህ ካህን ተከሥተ ብርሃን ለኵሉ ዓለም ወተቀደሰት ቤተክርስቲያን ትፍሥሕት ወሐሴት ለጻድቃን፡፡ ካህናት የዐርጉ መሥዋዕተ ስብሐት ዘምስለ መንፈስ ቅዱስ፡፡ ጸልዩ ለነ ካህናት አግብርተ እግዚአብሔር እስመ ለክሙ ይቤለክሙ አማልክት አንትሙ ወደቂቀ ልዑል ኵልክሙ)፡፡

**ካህናተ ሰማይ፦** ለሰው ሁሉ ምሕረትን የሚለምኑ ደጋግ አማላጆች የአብ ወዳጆች [ካህናተ ሰማይ] በአንድ ላይ አብን ያመሰግኑታል፡፡ ክብራቸው [ከሌሎች] መላእክት [ክብር] ይበልጣል፡፡ (#በግእዝ፦ ፍቁራኒሁ ለአብ ኄራን መተንብላን እለ ይስእሉ ምሕረተ ለውሉደ ሰብእ ኅቡረ ይባርክዎ ለአብ፡፡ ይሴብሑ ወይዜምሩ እንበለ ጽርዐት፡፡ የዐቢ ክብሮሙ እመላእክት)፡፡

## ✿ዘዘወትር✿

**ካህናት፦** ለካህናት ክብር ይገባቸዋል፡፡ በሕይወታቸው ለእርሱ የተገዙ ካህናትን አስጌጣቸው፡፡ ንጹሕ አክሊል በራሳቸው ላይ አለ፡፡ ፊታቸው ከፀሐይ ይልቅ ያበራል፡፡ (#በግእዝ፦ ለካህናት ክብር ይደልዎሙ፡፡ ለካህናት አሠርገዎሙ አክሊል ንጹሕ ዲበ ርእሶሙ እምፀሐይ ይበርህ ገጾሙ፡፡ እለ ሎቱ ተቀንዩ በሕይወቶሙ)፡፡

**እግዚአብሔር፦** እግዚአብሔር የጽድቅና የሕይወት መንገድ ነው፡፡ (#በግእዝ፦ እግዚአብሔር ውእቱ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት)፡፡

## ❁ኅዳር 25 ዘመርቆሬዎስ❁

**መርቆሬዎስ፦** ባስልዮስና ጎርጎርዮስ በቅዱስ መርቆሬዎስ ሥዕል ፊት ጸለዩ፡፡ ዑልያኖስን ገደልከውን አሉት፡፡ ሥዕሉም አዎ እንደሚል አዘነበለ፡፡ ባስልዮስና ጎርጎርዮስም ደስ አላቸው፡፡ ጸሎታቸውን ሰምቶ ጠላታቸውን ገደለ፡፡ መርቆሬዎስ ንጉሡን የወደድከውን አድርግ እኔስ ቸር አምላኬን አልተውም አለው፡፡ (#በግእዝ፦ ጸለዩ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ ኀበ ሥዕሉ ለቅዱስ መርቆሬዎስ ወይቤሉ ቀተልኮኑ ለዑልያኖስ ደነነ ሥዕል ከመ ኦሆ ዘይብል ወተፈሥሑ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ፡፡ ሰምዖሙ ጸሎቶሙ ወቀተለ ፀሮሙ፡፡ ይቤሎ መርቆሬዎስ ለንጉሥ ዘፈቀድከ ግበር አንሰ ኢየኀድጎ ለአምላኪየ ኄር)፡፡

## ✿ኅዳር 27 ዘናግራን✿

**ናግራን፦** [ናግራን ሆይ] ገነት የተባልሽ የእግዚአብሔር ሀገር ታላቅ ሀገር ነሽ፡፡ የሰማዕቶችሽ ደም እንደ ውሃ ፈሰሰ፡፡ ታላቂቱ ሀገር ናግራን ሆይ ኮከቦችሽ የሚያበሩ፣ ዕፀዋቶችሽ የቀሉ፣ ካህናቶችሽ ተናጋሪዎች፣ ዲያቆናቶሽ የሚላኩ፣ ሕዝቦችሽ በቅድስት ቤተክርስቲያን የተጠመቁ

የታመኑ ናቸው። ናግራን የአሸናፊዎች የሰማዕታት ሀገር ናት። (#በግእዝ፦ ዐባይ ሀገር ሀገረ እግዚአብሔር እንተ ተሰመይኪ ገነተ። ደሞሙ ለሰማዕታትኪ ውኅዘ ከመ ማይ። ኦ ሀገር ዐባይ ሀገረ ናግራን ከዋክብትኪ ብሩሃን ወዕፀውኪ ፍሡሓን ካህናትኪ ነባብያን ወዲያቆናትኪ ላዕካን ወሕዝብኪኒ መሃይምናን እለ ተጠምቁ በቅድስት ቤተክርስቲያን። ሀገረ ናግራን ሀገረ ሰማዕታት መዋዕያን)።

## ❁ኅዳር 29 ዘጴጥሮስ ሊቀ ጳጳሳት❁

**ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳሳት፦** ጴጥሮስ ወታደሮችን የተላካችሁበትን ፈጽሙ አላቸው። ልዩ የሆነች ቀሙሱን አውልቆ አንገቱን ሰጣቸው። በእውነትም ሰማዕት ሆነ። [እግዚአብሔር] ሃይማኖትን ታቀና ዘንድ መርጦ ሾመህ። የማይነዋወጥ መሠረት ጽኑ ምሰሶ የጳጳሳት አለቃ ጴጥሮስ ንዑድ ክቡር ነው። ለአሕዛብ የሕግ መምህር ነው። የተራቡትን አጠገበ የተራቆቱትን አለበሰ። የተማረኩትን ተቤዠ። የሰማዕታት መጨረሻ የጳጳሳት አለቃ ጴጥሮስ ንዑድ ክቡር ነው። (#በግእዝ፦ ይቤሎሙ ጴጥሮስ ለሐራ ፈጽሙ መልእክተክሙ አስሐወ ሎሙ ፈቃሮ ቅድስተ ወመጠዎሙ ክሳዶ ክብርተ ወኮነ ሰማዕተ በጽድቅ። ኅረየከ ወሤመከ ሊቀ ጳጳሳት ከመ ታስተራትዕ ኵሎ ሃይማኖተ። ብፁዕ ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳሳት ዐምድ ጽኑዕ መሠረት ዘኢያንቀለቅል። መምህረ ሕግ ለአሕዛብ። አጽገበ ርኁባነ ወአልበሰ ዕሩቃነ። ወቤዘዎሙ ለፂውዋን። ብፁዕ ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳሳት ተፍጻሜ ሰማዕት)።

**ካህናት፦** ሃይማኖታቸው የቀና ጳጳሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት እንዲሁም ከሁሉ በላይ የሆነች የጸናች አዳራሽ የቅድስት ቤተክርስቲያን ማሕበር ሁሉ ንዑዳን ክቡራን ናቸው። (#በግእዝ፦ ብፁዓን እሙንቱ ጳጳሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ርቱዓነ ሃይማኖት ወኵሉ ፍጻሜ ማኅበራ ለቅድስት አሐቲ እንተ ላዕለ ኵሉ ቤተክርስቲያን ጽርሕ ቀዋሚት)።

## ❦ዘጳጳሳት❦

**ካህናት፦** ጳጳሳትን፣ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ብርሃንን የሚገልጡ መምህራንና ቤተክርስቲያንን የሚጠብቁ እረኞች አድርጎ ሾማቸው። (#በግእዝ፦ ሤሞሙ አብ ጳጳሳተ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ መምህራነ ከሣትያነ ብርሃን ወኖሎተ ቤተክርስቲያን)።

## ❧ዘጻድቃን❧

***መልካም ሥራ፦*** አንተ የእግዚአብሔር ሰው ግን ከነውር ሽሽ እውነትንም ተከተል። የማሸነፍ ፍርዱ እስኪመለስ ተጠበቅ። በክርስቶስ ያላችሁ ሥጋችሁን አንጹ። የባልንጀራችሁን በደልም ይቅር በሉ። (#በግእዝ፦ ወአንተሰ ብእሴ እግዚአብሔር ጕይ እምነውር ወዴግን ጽድቀ ተዐቀብ እስከ ይገብዕ ፍትሐ መዊዖቱ። እለ በክርስቶስ ሀሎክሙ አንጽሑ ሥጋክሙ። ወኅድጉ አበሳ ለቢጽክሙ)።

**ጻድቃን፦** አባታቸው በጽዮን ዋጋቸውን በሰጣቸው ጊዜ ጻድቃን በእግዚአብሔር ደስ ይላቸዋል:: ሁሉ ከንቱ እንደሆነ አውቀው አብ ተስፋ ያስደረጋቸውን ተስፋቸውን በትዕግሥታቸው ማግር ወረሱ:: ለጻድቃን ንጹሕ ቤትን ያዘጋጀበት፣ ዕረፍት ያለበት፣ ገነት የተከፈተበት፣ ክርስቶስ ያለበትን በላይ ያለውን መረጡ:: ጻድቃን ሞት በሌለበት በኢየሩሳሌም ደስ ይላቸዋል:: [ጻድቃን ሆይ] ጸሎታችሁ በሀገር መካከል እንደ ምሰሶ ጽኑ ነው:: [ጻድቃን] ጥቂት መከራን ተቀብለው ብዙ ይደሰታሉ:: መንግሥተ ሰማያትን አገኙ ወደ ቅድስት ሀገርም ገቡ:: ክርስቶስን መርጠው በመንግሥተ ሰማያት ያድራሉ:: መከራን ታግሠው የዚህችን ዓለም ፍቅሯን ያቃለሉ፣ ኀላፊ ክብሯንም የናቁ የክርስቶስ ወታደሮች የድንግል በኵሯ [ክርስቶስ] በድንኳን ይቆምላቸዋል:: ክፉ ሐሳብን በብዙ መከራ ያሸንፉ ዘንድ የታገሡትን እናደንቃቸዋለን:: የጻድቃን ነፍሳት የጸኑ ተራሮች ይባላሉ:: የጻድቃን ሞታቸው ሕይወታቸው ነው:: የጻድቅ ሥልጣኑ በክብር ከፍ ከፍ ይላል:: እግዚአብሔርን ለሚፈራ ኋላው ያምራል የሞቱ ቀን ይባረካል:: [ጻድቃን] ክፉን በእምነታቸው አሸነፉ:: የብርሃን ልጆች ጻድቃን ሞትን አልፈሩም:: ሞት በሌለበትም ደስ ይላቸዋል:: ጻድቃን መከራን ተቀበሉ:: መከራቸውም ደስታ ሆናቸው:: እናንተ [ጻድቃን] ክፉን በትዕግሥታችሁ አሸነፋችሁት:: (#በግእዝ፦ ይትፌሥሑ ጻድቃን በእግዚአብሔር ሶበ ይሬእዩ ዕሤቶሙ ዘወሀቦሙ አቡሆሙ በጽዮን:: እስመ በሥነ ትዕግሥቶሙ ወረሱ ተስፋሆሙ አብ ዘአሰፈዎሙ አእሚሮሙ ከመ ኵሉ ከንቱ:: ዘበላዕሉ አብደሩ ኀበ ሀሎ ክርስቶስ ኀበ ተርኅወ ገነት ወኀበ ተነጽፈ ዕረፍት ዘአስተዳለወ ማኅደረ ንጹሐ ለጻድቃን:: ይትፌሥሑ ጻድቃን በኢየሩሳሌም በኀበ አልቦቱ ሞት:: እስመ ጸሎትክሙ ከመ ዐምድ ጽኑዕ በማዕከለ ሀገር:: ኅዳጠ ሐሚሞሙ ወብዙኀ ይትፌሥሑ:: አድምዑ መንግሥተ ሰማያት ወቦኡ ውስተ ሀገር ቅድስት:: ክርስቶስሀ አብደሩ መንግሥተ ሰማያት የኀድሩ:: ለዛቲ ዓለም እለ አስተሐቀሩ ፍቅራ ወእለ መነኑ ኀላፊተ ክብራ ተዐጊሦሙ መከራ ዘክርስቶስ ሐራ ይቀውም ሎሙ በደብተራ ለድንግል በኵራ:: ናስተበፅዖሙ ለእለ ተዐገሡ በብዙኀ ፃማ ከመ ይማዕዎ ለእኩይ ኀሊና:: አድባረ ድኅኃነ ይሰመዩ ነፍሳቲሆሙ ለጻድቃን:: ሞቶሙሰ ለጻድቃን ሕይወቶሙ ውእቱ:: እስመ ለጻድቅ ይትሌዐል ቀርኑ በክብር:: ለፈራሄ እግዚአብሔር ይሤኒ ደኀሪቱ ወይትባረክ ዕለተ ሞቱ:: ሞዕዎ ለእኩይ በእምነቶሙ:: ጻድቃን ውሉደ ብርሃን ኢፈርህዎ ለሞት:: ወይትሐሰዩ በኀበ አልቦቱ ሞት:: ሐሙ ጻድቃን ሕማሞሙ ትፍሥሕተ ኮኖሙ:: አንትሙ ሞዕክምዎ ለእኩይ በትዕግሥትክሙ)::

**መንግሥተ ሰማያት፦** እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጃት ዐይን ያላያት ጆሮ ያልሰማት ናት:: ሕመም የሌለባት፣ መከራ የሌለባት፣ ከዚህ በኋላ ዳግመኛ የማይሞቱባት ናት:: (#በግእዝ፦ ዘዐይን ኢርእየ ወእዝን ኢሰምዐ ዘአስተዳለወ ለእለ ያፈቅርዎ:: ኀበ አልቦ ደዌ ወአልቦ ሕማም ኀበ ኢይመውቱ እምዝ ዳግመ)::

**ነገረ ክርስቶስ፦** [ክርስቶስ] የጻድቃን ብርሃን ነው:: ሰውን የሚወድ ክርስቶስ ሁልጊዜ ይቅር ባይ ነው:: የጻድቃንን ሰውነት ይጠብቃል:: ከኃጥኣን እጅም ያድናቸዋል:: ለምእመናን ያበራላቸዋል:: የማያልቅ ደስታ ነው:: (#በግእዝ፦ ብርሃን ለጻድቃን ክርስቶስ:: መሓሪ ወትረ መፍቀሬ ሰብእ

ክርስቶስ የዐቅብ ነፍሰ ጻድቃን ወያድኅኖሙ እምእደ ኃጥኣን ወያበርህ ሎሙ ለመሃይምናን ፍሥሓ ዘኢየኀልቅ)፡፡

**☬ዘሰማዕት☬**

**ሰማዕት፦** በሰማዕታት ትዕግሥት ሀገር ትድናለች፡፡ [ሰማዕታት] በሃይማኖት ምስክር ሆኑ፡፡ ሰማዕትን እንደ ወርቅ በእሳት ፈተናቸው [ጠበሷቸው]፡፡ እንደመሥዋዕት ጽና ተቀበላቸው፡፡ የክርስቶስ ሰማዕታት ከዚህ ከኀላፊው ዓለም በተሰደዱ መጠን በሚመጣው ዓለም እጅግ ደስ ይላቸዋል፡፡ ሰማዕት በትዕግሥታቸው ጠላታቸውን አሸነፉ፡፡ እንደ ንጋት መንጋት፣ እንደ ፀሐይ መውጣት፣ በአትክልት ቦታ እንዳለ መብራት የቅዱሳን ሰማዕት ብርሃናቸው እንዲሁ ነው፡፡ በሃይማኖት የጸኑ ቅዱሳን ሰማዕት ሞትን አልፈሩትም፡፡ ስለሃይማኖት ዓለምን ናቁ ፍጹም መከራንም ታገሡ፡፡ የክርስቶስ ሰማዕት የሥጋ መከራን ታገሡ፡፡ (#በግእዝ፦ በትዕግሥቶሙ ለሰማዕት ትድኀን ሀገር፡፡ ሰማዕተ ኮኑ በሃይማኖት፡፡ ከመ ወርቅ በእሳት ፈተኖሙ ለሰማዕት ወከመ ጽንሐሐ መሥዋዕት ተወክፎሙ፡፡ ሰማዕታቲሁሰ ለክርስቶስ አምጣነ ተሰዱ እምዝንቱ ዓለም ኀላፊ ወፈድፋደ ይትፌሥሑ ገሐደ በዓለም ዘይመጽእ፡፡ ሰማዕት በትዕግሥቶሙ ሞዑ ፀሮሙ፡፡ ከመ ጎሐ ጽባሕ ወከመ ሠርቀ ፀሐይ ከመ ማኅቶት ዘውስተ ገነት ከማሁ ብርሃኖሙ ለቅዱሳን ሰማዕት፡፡ ኢፈርህዎ ለሞት ቅዱሳን ሰማዕት እለ ጽኑዓን በሃይማኖት፡፡ በእንተ ሃይማኖት መነኑ ዓለመ ወተዐገሡ መከራ ፍጹመ፡፡ ሰማዕተ ክርስቶስ ምንዳቤ ሥጋ ተዐገሡ)፡፡

**ነገረ ክርስቶስ፦** [ክርስቶስ] የመነኰሳት ተስፋ የቤተክርስቲያን ሙሽራዋ ነው፡፡ ለሰማዕት ኀይላቸው ክርስቶስ ነው፡፡ (#በግእዝ፦ ተስፋ መነኰሳት መርዓዊሃ ለቤተክርስቲያን፡፡ ኀይል ክርስቶስ ውእቱ ለሰማዕት)፡፡

# ❖መጽሐፈ ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ❖

## ዘአስተምሕሮ



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ መምህር)

ነሐሴ ፳፤ ፳፻፲፫ ዓ.ም

## ዘአስተምሕሮ

**እግዚአብሔር፦** [እግዚአብሔር] ቁጣ የሌለበት ይቅር ባይ፣ በደል የሌለበት ንጹሕ፣ ኃጢአት የሌለበት ጻድቅ፣ ፊት አይቶ የማያዳላ መኰንን ነው። ከኖኅ ጋር ኪዳንን ያደረግህ፣ ለእስራኤል ልጆች መናን ያወረድክ [እግዚአብሔር ሆይ] በቃልህ ሁሉ ይቻላል። እግዚአብሔር ሳያውቅ የሚሆን ነገር የለም። (#በግእዝ፦ መሓሪ ዘአልቦ መዓት ወንጹሕ ዘአልቦ ርስሐት ጻድቅ ውእቱ ዘአልቦ ኃጢአት መኰንን ውእቱ ዘኢያደሉ ለገጽ። ምስለ ኖኅ ኪዳነ ዘአቀምከ ለደቂቀ እስራኤል መና ዘአውረድከ ወኵሉ ይትከሀል በቃልከ። አልቦ ዘይከውን ዘኢያእመረ እግዚአብሔር)።

**ሰንበት፦** [ኢየሱስ ክርስቶስ] በሰንበት ወደ ታንኳ ወጣ፣ ባሕርን ጸጥ አደረገ፣ የታመሙትን ፈወሰ። ጌታ ከሥራው ሁሉ በሰንበት አረፈ። የክርስቲያኖች ሁሉ ሰንበት ናት። ይቺ ሰንበተ ክርስቲያን ለደከሙት ዕረፍታቸው ናት። ሰንበትን የሚያከብር የዘለዓለም ሕይወትን ያገኛል። በሰንበት ቀን ቤተክርስቲያንን ምስጋና ይከባታል። ሰንበትን መላእክት በሰማያት ጻድቃን በገነት ያከብሯታል። ባሕር፣ ዓሣዎች፣ አናምርትና ፍጥረታት ሁሉ ያከብሯታል። (#በግእዝ፦ በሰንበት ዐርገ ሐመረ ገሠፀ ባሕረ በሰንበት ፈወሰ ዱያነ። ሰንበቶሙ ይእቲ ለሕዝበ ክርስቲያን በዕለተ ሰንበት አዕረፈ እግዚእነ እምኵሉ ግብሩ። ዛቲ ዕለት ሰንበተ ክርስቲያን ዕረፍቶሙ ለሥሩሃን። ዘያከብር ሰንበተ ይረክብ ሕይወተ ዘለዓለም። በዕለተ ሰንበት ስብሐት የዐውዳ ለቅድስት ቤተክርስቲያን። ያከብርዋ ለሰንበት መላእክት በሰማያት ጻድቃን በውስተ ገነት። ታከብር ባሕር ወኵሉ ፍጥረት ዓሣት ወአናምርት)።

**ሐተታ ተፈጥሮ፦** ሰው ግን ከንቱን ይመስላል። የዛሬ ሰው የነገ አፈር ነው። ንብረቱም ምኞቱም በዚህ ዓለም የሚቀር ነው። (#በግእዝ፦ ሰብእሰ ከንቶ ይመስል ዘዮም ሰብእ ወጌሠመ መሬት። ንብረቱኒ ፍትወቱኒ በዝንቱ ዓለም ኀላፊ)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** ሰውን በእርሱ አርአያ የፈጠረ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ያልኖረበት ጊዜ የለም የማይኖርበት ጊዜም የለም። (#በግእዝ፦ አልቦ አመ ኢሀሎ ወአልቦ አመ ኢሀሎ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ዘገብሮ ለሰብእ በአርአያ ዚኣሁ። ኵሉ ውስተ እዴሁ። ውእቱ ይኴንን ሰማያተ ወምድረ)።

## ዘዘወትር

**እግዚአብሔር፦** የማይሾሙት ንጉሥ ነው፣ የማያበድሩት ባዕለ ጸጋ ነው። ሥልጣኑን የማይቀሙት ባለሥልጣን ነው። [አቤቱ] የማይጎድል መዝገብ አለህ። የችግረኞች አባት አንተ ነህ፣ ለተገፉት መጠጊያቸው የቤተክርስቲያን መሠረት ነህ። ከእንቅልፍ ያነቃህን የሁላችን አባት ሆይ ሲነጋ ሲነጋ [እየነጋ እየነጋ] እናመሰግንሀለን። አቤቱ አንተ የምትሠውር ረዳት ነህና ከጠላት ኀይል አድነኝ። አንተ አባታችን ነህ። አንተ በችግራችን ጊዜ የምትረዳን አምላካችን ነህ። አቤቱ እኛን በጎ ምግባር የሌለንን ሰዎች ብትምረን ያን ጊዜ ይቅር ባይ ትባላለህ። ባዕለ ጸጋ እግዚአብሔር ለሁሉ ይበቃል። ለእግዚአብሔር የተገዛ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ነጻ የወጣ

ነው። እግዚአብሔር እኔ በምድርም በሰማይም አለሁ አለ። ወርቅና ብር የእኔ ነው ለወደድኩት እሰጠዋለሁ። (#በግእዝ፦ ንጉሥ ዘኢይሠይምዎ ባዕል ውእቱ ዘኢይሌቅሕዎ ወዘኢየሐይድዎ ሥልጣኖ። መዝገብ ብከ ዘኢይቀብል። አንተ ውእቱ አበ ነዳያን ምስካዮሙ ለግፉዓን መሠረተ ቤተክርስቲያን። እንተ ጸብሐት ንባርከከ አበ ኵልነ ዘአንቃሕከነ እምንዋም። አድኅነኒ እግዚኦ እምኀይለ ጸላዒ ወፀር እስመ አንተ ረዳኢ ወመሠውር። አንተ አቡነ ወአንተ አምላክነ ወረዳኢነ በጊዜ ምንዳቤነ። ወለነኒ ለእለ አልብነ ምግባረ ሠናይ ለእመ መሐርከነ እግዚኦ ውእተ አሚረ ትሰመይ መሓሬ። እስመ ባዕል እግዚአብሔር የአክል ለኵሉ። ወኵሉ ዘተቀንየ ለእግዚአብሔር ግዑዝ ውእቱ በኀበ ኢየሱስ ክርስቶስ። ይቤ እግዚአብሔር አነ በሰማይ ወአነ በምድር ወርቅ ወብሩር ዚኣየ ውእቱ ወለዘፈቀድኩ እሁቦ አነ)።

**ቤተክርስቲያን፦** የኃጢአት ማስተሥረያ መስገጃ መለመኛ የሆነች ቤተክርስቲያንን በሰማያት ላለው አርአያ ትሆን ዘንድ ሠሯት። [እግዚአብሔር] ማረፊያዬ ይላታል። ማደሪያውም አደረጋት። አስቀድሞ በእጆቹ ሠራት። ይህቺ ጽዮን የንስር ዓይን ያላያት ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት። (#በግእዝ፦ ሐነጽዋ ወሣረርዋ ለቤተክርስቲያን ከመ ትኩን አርአያ ዘበሰማያት ምስአል ወምስጋድ ወምስትሥራየ ኃጢአት። ምዕራፍየ ይቤላ ወማኅደሮ ረሰያ በእደዊሁ አቅዲሙ ሣረራ ዛ ጽዮን ቅድስት ቤተክርስቲያን እንተ ኢርእያ ዐይነ ንስር)።

***መልካም ሥራ፦*** ጾምና ጸሎት ከሞት ያድናሉ። በሰማያትም ደስ ያሰኛሉ። አንተ ግን ራስህን ፈትን። ጾም ለምን ይጠቅማል አትበል። በጾም ኤልያስ ወደ ሰማይ ወጥቷልና ዳንኤልም ከአናብስት አፍ ድኗልና። ልጄ የወጣትነት ሥራን ተዋት የጽድቅ ሥራንም ተከተላት። በእግዚአብሔር ፊት መልካምን አስብ ክፋትንም አታድርግ። ልጄ መጻሕፍትን መመርመርን አትተው። በዚህ ፈሪሀ እግዚአብሔርን ታገኛለህና። ለሚወዱት ወዳዘጋጀው መንገድም ይመርሀል። ወዳጆቼ ወንድሞቼ ወርቅም ሆኖ ብርም ሆኖ የከበረ ልብስም ሆኖ የዚህ ዓለም ኑሮ ምን ይረባናል። በሞቱ ጊዜ ለሰው ምን ይጠቅመዋል። በሕይወቱ መልካምን ያደረገ ግን ዋጋውን ያገኛል። የሞታችሁን ቀን አታውቁምና ተዘጋጅታችሁ ኑሩ። ይቺ ጾም ለጠቢባን ደስታ ለሰነፎች ኀዘን ናት። (#በግእዝ፦ ጾም ወጸሎት ታድኅን እሞት ወታስተፌሥሕ በሰማያት። ወአንተሰ አመክር ርእሰከ ወኢትበል ምንት ይበቍዕ ጾም እስመ በጾም ኤልያስ ሰማያተ ዐርገ ወዳንኤል እምአፈ አናብስት ድኅነ። ወልድየ ኅድጋ ለምግባረ ውርዙት ወዴግና ለምግባረ ጽድቅ። ኅሊ ሠናየ ቅድመ እግዚአብሔር ኢትግበር እኩየ። ወልድየ ኢትኅድግ ተኀሦ መጻሕፍት እስመ በዝየ ትረክብ ፈሪሀ እግዚአብሔር ወይመርሐከ ፍኖተ ዘአስተዳለወ ለእለ ያፈቅርዎ። አኃውየ ፍቁራንየ ምንት ይበቍዐነ ንብረቱ ለዝንቱ ዓለም ኢወርቅ ወኢብሩር ወኢአልባስ ክቡር። ምንት ይበቍዖ ለሰብእ በዕለተ ሞቱ። ወዘሰ ገብረ ሠናየ በሕይወቱ ውእቱኬ ይነሥእ ዕሴቶ። ድልዋኒክሙ ንበሩ እስመ ኢተአምሩ ዕለተ ሞትክሙ። ዛቲ ጾም ፍሥሓ ለጠቢባን ለአብዳን ኀዘን)።

**ሰማዕት፦** ከዋክብት በውበታቸው ሰማይን እንደሚያስጌጧት ሰማዕታትም እንዲሁ በገድላቸው ቤተክርስቲያንን ያስጌጧታል። (#በግእዝ፦ በከመ ከዋክብት ያሠረግውዋ ለሰማይ በስኖሙ ወከማሁ ሰማዕትኒ ያሠረግውዋ ለቤተክርስቲያን በገድሎሙ)።

**ሐተታ ተፈጥሮ፦** ሰው ግን በኑሮው የሞቱን ቀን አላወቀም [አያውቅም]። ጭቃና ኩስ የሆንክ የሰው ልጅ ሆይ ራስህን ለምን ከፍ ከፍ ታደርጋለህ። (#በግእዝ፦ ሰብእሰ በሕይወቱ ኢያእመረ ዕለተ ሞቱ። ምንተ ትትሌዐል ኦ ሰብእ እንዘ ጽቡር አንተ ወኵስሕ)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** አርአያውን ይሰጠን ዘንድ ጌታችን ስለእኛ ጾመ። ኢየሱስ ክርስቶስ ያልተሠራና ያልተፈተለ ልብስ ነው። ለተገፉት መጠጊያቸው ተስፋ ለቆረጡት ተስፋቸው ነው። በአዳኛችን በክርስቶስ በማመን ሰላምን እናገኝ። ዐይኖቹ ከወይን ይልቅ የሚያምሩ፣ ጥርሶቹ እንደበረዶ ነጭ የሆኑ ናቸው። ልብሱን በወይን ያጥባል። መጎናጸፊያውንም በፍሬ ደም የሚያጥብ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የበልግ ዝናምን የሚሰጥ፣ ከምንጮች ከወንዞች ከባሕር አውጥቶ በጸደይ በጥቢ ውሃን የሚያፈስ ነው። (በግእዝ፦ እግዚእነ ጾመ በእንቲኣነ አርአያሁ ከመ የሀበነ። ልብስ ዘኢተአንመ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ወክዳን ዘኢተፈትለ። ምስካዮሙ ለግፉዓን ተስፋሆሙ ለቅቡጻን። ንርከብ ሰላመ በአሚን በክርስቶስ መድኀኒነ። ጸዓዳ ስነኒሁ ከመ በረድ ወፍሡሓት አዕይንቲሁ እምወይን። ወየሐጽብ በወይን ልብሶ ወበደመ አስካል አጽፎ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ። ዘይሁብ ዝናመ ተወን ጸደየ ወመጸወ ዘያውኀዝ ማየ እምባሕር ወእምአፍላግ ወሄላ ለምድር)።

## ☦ታኅሣሥ 1 ዘኤልያስ☦

**ነቢዩ ኤልያስ፦** ኤልያስ በጸሎቱ ከሰማይ ዝናምን አዘነመ። ኤልያስ በእሳት ፈረስ ሠረገላ ወደ ሰማይ ዐረገ። ኤልያስ በጸሎቱ ሰማይን ለጎመ። እግዚአብሔር በቀኙ ጋርዶላቸዋልና ሞትን ያልቀመሱ ነቢያት ሰዎች አሉ። የልዑልን ሕግ የጠበቀ የቴስብያ ሰው ክቡር ኤልያስ የአማልክትን ጣዖት አፈረሰ። ለእግዚአብሔርም የሰላም መሥዋዕትን አቀረበ። ከዓለም ደስታ የራቀ ክቡር ኤልያስ በንጽሕናና በቅድስና የሥጋውን ቤት ሠራ። በሠረገላም ወደላይ ተነጠቀ። የመንፈስ ቅዱስን ኀይል ታጥቆ ክቡር ኤልያስ ምኞቱን አገኘ። ሕይወቱንም እንደመላእክት አደረገ። ኤልያስና ዮሐንስ አኗኗራቸው አንድ ነው። አንድ ኀይልን ይለብሳሉ። የፍየል ሌጦዎችን ይታጠቃሉ። በወገባቸው መታጠቂያ አለ። ኑሯቸውም በገዳም ነው። (#በግእዝ፦ በጸሎቱ ኤልያስ እምሰማይ ዝናመ አውረደ። ኤልያስ ዐርገ ውስተ ሰማያት በሠረገላ አፍራሰ እሳት። ኤልያስ በጸሎቱ ለጎመ ሰማየ። ሀለዉ ዕደው ነቢያት እለ ኢጥእምዎ ለሞት እስመ እግዚአብሔር በየማኑ ከደኖሙ። ኤልያስ ክቡር ቴስብያዊ ዘዐቀበ ሕጎ ለልዑል ነሠተ ጣዖተ አማልክት ወገብረ መሥዋዕተ ሰላም ለእግዚአብሔር። በቅድስና ወበንጽሕ ምኵራበ ሥጋሁ ነደቀ በሠረገላ ሉዓሌ ተመጥቀ ኤልያስ ክቡር እምሐውዘ ዓለም ዘርኀቀ። ኀይለ መንፈስ ቅዱስ ቀኒቶ ኤልያስ ክቡር ረከበ ተምኔቶ። ከመ መላእክት አስተማሰለ ሕይወቶ። ኤልያስ ወዮሐንስ

አሐዱ ህላዌሆሙ ወአሐደ ኀይለ ይለብሱ ዘባድወ የዐጥቁ ዐዲም ውስተ ሐቋሆሙ ወንብረቶሙ ገዳም)።

**ታኅሣሥ 2 ዘሠለስቱ ደቂቅ**

**ሠለስቱ ደቂቅ፦** አናንያ፣ አዛርያና ሚሳኤል በእምነታቸው ጸሎታቸው ወደ ሰማይ ዐረገ የእሳት ምድጃም [የምድጃ እሳትም] አላቃጠላቸውም። የንጉሥ ቁጣ አላስደነገጣቸውም። የክርስቶስ ኀይል አጸናቸው። የእሳትን ኀይል በትዕግሥታቸው አጠፉ። አናንያ፣ አዛርያና ሚሳኤል ፊታቸውን በትእምርተ መስቀል አማተቡ። ወደእሳት ምድጃ ገቡ። ምንም የነካቸው የለም። (#በግእዝ፦ አናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል በእምነቶሙ ሰማያተ ዐርገ ጸሎቶሙ ዕቶነ እሳት ኢያውዐዮሙ። መዓተ ንጉሥ ኢያደንገጾሙ ወኀይለ ክርስቶስ አጽንዖሙ። አጥፍዑ ኀይለ እሳት በትዕግሥቶሙ። ጸለዩ አናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል ዐተቡ ገጾሙ በትእምርተ መስቀል ቦኡ ውስተ ዕቶነ እሳት ወአልቦ ዘለከፎሙ)።

**እግዚአብሔር፦** አናንያ በእሳት ምድጃ ውስጥ ሳለ ለጠላት የማትሸነፍ አንተ እግዚአብሔር ነህ እያለ ነገር ጀመረ። (#በግእዝ፦ ከሠተ አፉሁ አናንያ በውስተ እቶነ እሳት እንዘ ይብል አንተ እግዚአብሔር ዘኢትትመዋዕ ለፀር)።

**ዘስብከት**

**ነገረ ክርስቶስ፦** እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሳለ ማንም አይችለንም። በነቢያት ስሙ የተሰበከ አማኑኤል እግዚአብሔር ነው። ወልድ በክብር እንደሚመጣ ነቢያት ዜናን ነገሩን። ከዓለም በፊት የነበረውን የሚያድን ልጁን እንሰብካለን። ከሙሴ ሕግ እስከ ነቢያት ድረስ ስለአንዱ ስለእግዚአብሔር ልጅ መምጣት ነቢያት አስተማሩ። በኦሪት ሕግ የተነገረውን፣ ለጽዮን የደስታ ዜና የሚናገረውን የሰንበት ጌታ መምጣቱን ነቢያት አስተማሩ። ነቢያት ሰበኩት ምስክርም ሆኑት ወላዲ አብንም እጅህን ላክ አሉት። ክርስቶስ በቀጠሮው መጣ። በመስቀሉ እኛን የተቤዠንን እርሱን መድኀኒታችንን እንሰብካለን። ከሰማያት ወረደ ምድራዊት የሆነች ሥጋችንንም ተዋሐደ። የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣቱንና ማዳኑን ስበኩ። እስከ ምድር ጫፍ እስኪሰማ ድረስ ስበኩ። ወልደ እግዚአብሔር ያዘኑትን ያረጋጋ ዘንድ የተበተኑትን ይሰበስብ ዘንድ መጣ። ሰላማዊ [ክርስቶስ] ሰላምን ያደረግ ዘንድ መጣ። (#በግእዝ፦ እንዘ እግዚአብሔር አምላክነ ምስሌነ አልቦ ዘይክለነ። እግዚአብሔር ውእቱ አማኑኤል ስሙ ዘተሰብከ በነቢያት። ዜነዉነ ዜና ነቢያት ከመ ይመጽእ ወልድ በስብሐት። ወልዶ መድኀነ ንሰብክ ዘእምቅድመ ዓለም ሀሎ። እምኦሪተ ሙሴ እስከ ነቢያት ሰበኩ ምጽአቶ ለዋሕድ ለወልደ እግዚአብሔር። ዘተነግረ በሕገ ኦሪት ምጽአቶ ሰበኩ ነቢያት እግዚኣ ለሰንበት ዘይዜንዋ ለጽዮን ቃለ ትፍሥሕት በነቢያት ተሰብከ። ነቢያት ሰበክዎ ሰማዕተ ኮንዎ ፈኑ እዴከ ለወላዲ ይብልዎ። ክርስቶስ መጽአ በዕድሜሁ። ኪያሁ ንሰብክ መድኀነ ለዘበመስቀሉ ቤዘወ ኪያነ። እምሰማያት ወረደ ወለብሰ ሥጋነ ምድራዊተ። ስብኩ ምጽአቶ ዜንዉ አድኅኖቶ ለመድኀኒነ

ክርስቶስ። ስብኩ ይሰማዕ እስከ አጽናፈ ምድር። ወልደ እግዚአብሔር መጽአ ኀቤነ ያስተጋብእ ዝርዋነ ይናዝዝ ኲሎ ኅዙናነ። ይግበር ሰላመ መጽአ ሰላማዊ)።

## ❦ዘክብረ ቅዱሳን❦

**ነገረ ክርስቶስ፦** የጻድቃን ሞገሳቸውና ክብራቸው ክርስቶስ ወደ ዓለም መጣ። በእንጨት መስቀል ላይ ይሰቀል ዘንድ ከሰማያት መጣ። ከዓለም በፊት የነበረ እስከ ዘለዓለም የሚኖር ወልድን እንሰብካለን። ይህም ለቅዱሳን ክብር ይሆን ዘንድ የላክኸው ልጅህ ነው። ጻድቃን የሚመጣው ይምጣና ዓለምን ያድን አይዘግይ እያሉ ለመኑ። የነፍስ መምህር የጻድቃን መሪ ልጁን ቤዛችንን ላከ። (#በግእዝ፦ ሞገሶሙ ወክብሮሙ ለጻድቃን ክርስቶስ መጽአ ውስተ ዓለም። እምሰማያት መጽአ ከመ ይሰቀል ዲበ ዕፀ መስቀል። ንሰብክ ወልደ ዘእምቅድመ ዓለም ሀሎ ወይሄሉ እስከ ለዓለም። ዝኬ ውእቱ ወልድከ ዘፈኖከ ውስተ ዓለም ለክብረ ቅዱሳን። ሰአሉ ወይቤሉ ጻድቃን ይምጻእኬ ዘይመጽእ ወኢይጎንዲ ከመ ያድኅን ዓለመ። ሐዳፌ ነፍስ ለጻድቃን መርሕ ቤዛነ ኪያሁ ወልዶ ፈነወ)።

## ❀ታኅሣሥ 18 ዘሰላማ❀

**አባ ሰላማ፦** የጌታችንን የወንጌል ብርሃን የገለጠልን አባ ሰላማ ንዑድ ክቡር ነው። የአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ስሙ ፍሬምናጦስ ነው። ወንጌልን ይሰብክ ዘንድና ብርሃንን ይገልጥ ዘንድ ወደ ምድራችን የተላከ ታላቅ ጳጳስ አባ ሰላማ ንዑድ ክቡር ነው። (#በግእዝ፦ ብፁዕ ውእቱ አባ ሰላማ ከሠተ ለነ ብርሃነ ዜናሁ ለመድኀኒነ። ፍሬምናጦስ ስሙ ለአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን። ብፁዕ ውእቱ አባ ሰላማ ዐቢይ ጳጳስ ዘተፈነወ ውስተ ምድርነ ከመ ይስብክ ዜናሁ ወይክሥት ብርሃነ)።

## ☘ታኅሣሥ 19 ዘገብርኤል☘

**እግዚአብሔር፦** [ስለ እግዚአብሔር] አንተ ግን ለማወቅ ብትፈልግን በምድር ያለ ኀሊናን ተውና ከዋክብትንና መኖሪያቸውን አልፈህ ከዚህ ሁሉ ከፍ ብለህ በልብህ የማይከፈል ሦስት የሆነ አንድ [ጌታን] አስብ። (#በግእዝ፦ ወአንተሰ ለእመ ትፈቅድ ታእምር ኅድግ ኅሊና ዘበምድር ወዕድዎሙ ለከዋክብት ስነ ሥርዓቶሙ ወኑባሬሆሙ እምዝንቱ ኲሉ ተልዒለከ በልቡናከ ኅሊ አሐደ ሥሉሰ ዘኢይሴደቅ)።

**ነገረ ማርያም፦** ገብርኤል ማርያምን ልጅ ትወልጃለሽ እያለ አበሠራት። ሚካኤል መልአክ በክንፉ ተሸከማት። የደመና መጋረጃ ሠወራት። በደል የሌለባት በድንግልና ንጽሕት የሆነች ናት። ወልድ ከእርሷ ተወለደ። ኢሳይያስ አዲስ ጥጃ አላት። ድንግል ማርያም ሐርን ለደብተራ እየፈተለች ሳለ ገብርኤል የፍቁር ወልድን መምጣት አበሠራት። ሶልያና ወርቅን እየፈተለች ሳለ ገብርኤል የደስታ ብሥራትን አበሠራት። ማርያም ግን ይህንን ሁሉ ትጠብቀው ነበር። ይኸውም ገብርኤል የነገራት የተረዳ ነገር ነው። የዳዊት ልጅ በቤተ መቅደስ ያደገች ብልኻተኛና

ትሑት ናት። በእውነት ዕፀ ጳጦስ ለሆነች ለድንግል ማርያም የወልድን መምጣት ሰበከ። ማርያም ገብርኤልን ሰላም ለአንተ ይሁን ለላከህም ሰላም አለች። ቃልህን አሰማኝ ድገምልኝ ድገምልኝ አለችው። (#በግእዝ፦ አብሠራ ገብርኤል ለማርያም ወይቤላ ትወልዲ ወልደ። ሚካኤል መልአክ በክነፉ ፆራ መንጦላዕተ ደመና ሠወራ ንጽሕት በድንግልና አልባቲ ሙስና ወልድ ተወልደ እምኔሃ። ኢሳይያስ ይቤላ ሐዳስዩ ጣዕዋ። እንዘ ትፈትል ድንግል ሜላተ ለደብተራ ምጽአተ ፍቁር ገብርኤል አብሠራ። ገብርኤል አብሠራ ብሥራተ ፍሥሓ ጥዩቀ ለሶልያና እንዘ ትፈትል ወርቀ። ማርያምሰ ህለወት ተዐቅብ ዘንተ ኵሎ ዝኬ ውእቱ ገብርኤል ዘዜነዋ ጥዩቀ። ጠባብ ወትጎት በቤተመቅደስ ዘልህቀት ወለተ ዳዊት። ዕፀ ጳጦስ እንተ በአማን ገብርኤል ሰበከ ላ ዜና። ትቤሎ ማርያም ለገብርኤል ሰላም ለከ ወሰላም ለዘፈነወከ ድግም ድግም ዜናከ ወአስምዐኒ ቃለከ)።

**ገብርኤል፦** ገብርኤል ወደ ማርያም ተላከ የቃልን መምጣትም ለእርሷ ሰበከ። በምድር ላይ ሁሉ የደስታ ቃልን የሚናገር ገብርኤል ወደ ገሊላ ሀገር ወደ ማርያም መጣ። የተላከበትን ነገር ሁሉ በደስታ ነገራት። ወገቡም ጭኑም በአፌዝ ወርቅ [ያሸበረቀ] ገብርኤል የሚባል አንድ መልአክ አለ። ገብርኤል ማለት አምላክ የሆነ ሰው፣ ሰው የሆነ አምላክ ማለት ነው። የቃልን ሰው መሆን ለድንግል ይሰብክ ዘንድ ከእግዚአብሔር የተላከ መልእክተኛ ነው። ትርጓሜው አምላክ የሆነ ማርያምን ሰላም ያላት ገብርኤል የሚመጣውን ታላቅ ጠባቂ ሰላምታን አስቀድሞ ነገራት። የመላእክት ክብራቸው እንደ መንኰራኵር ወረደ። ሙሴን በዕፀ ጳጦስ መካከል የተናገረው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ ድንግል ማርያም ወረደ። (#በግእዝ፦ ተፈነወ ገብርኤል ኀበ ማርያም ድንግል ሰበከ ላቲ ምጽአቶ ለቃል። ገብርኤል መጽአ ዘይዜኑ ቃለ ትፍሥሕት ወሐሴት ውስተ ኵሉ ምድር ኀበ ማርያም ሀገረ ገሊላ አብሠራ ዘለአኮ ኵሉ ነገራ። አልኖሲሶ በዕዝና ኵሎ ዘለአኮ ነገራ። ወሀሎ አሐዱ መልአክ ዘስሙ ገብርኤል ሐቌሁኒ ወአቍያጺሁኒ በወርቀ አፌዝ። ገብርኤል ብሂል ብእሲ ወአምላክ እምኀበ እግዚአብሔር ዘተፈነወ ላእክ ሥጋዌ ቃል ለድንግል ይስብክ። ገብርኤል ስሙ ዘአምኃ ለማርያም ዘበትርጓሜሁ አምላክ ውእቱ አቅዲሙ ዜነዋ አምኃሁ ለዘይመጽእ ዐቢይ ኖላዊ። ክብሮሙ ለመላእክት ከመ መንኰራኵር ወረደ መልአከ እግዚአብሔር ኀበ ማርያም ድንግል ዘተናገሮ ለሙሴ በኀበ ዕፀ ጳጦስ)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** ኃጢአትን ይቅር የሚል የአንበሳ ልጅ አንበሳ ወልድ ተወለደ። የመላእክት ክብራቸው የዓለም ሁሉ ደስታ መጣ። ብርሃንን እንደ ልብስ የሚጎናጸፍ መድኀኒታችን በዳዊት ሀገር ተወለደልን። የገብርኤል ጌታው ከሰማይ ወደ ምድር ወረደ። አኗኗሩ ከዓለም በፊት የነበረው እግዚአብሔር የእርሱን መምጣት ይሰብክ ዘንድ ላከው። (#በግእዝ፦ ተወልደ አንበሳ ዕጓለ አንበሳ ወልድ ዘይሠሪ አበሳ። ክብሮሙ ለመላእክት መጽአ ፍሥሓ ውስተ ዓለም። እግዚኡ ለገብርኤል ወረደ እምሰማይ ዲበ ምድር። ተወልደ ለነ መድኀን በሀገረ ዳዊት ዘይትዐፀፍ ብርሃነ ከመ ልብስ። ዘእምቅድመ ዓለም ህላዌሁ ፈነዎ ለገብርኤል ይስብክ ምጽአተ ዚኣሁ)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** ወደ ዓለም የመጣው ብርሃን የጽዮን በኵር ይባላል፡፡ ከሁሉ በላይ የሆነ ከላይ የመጣ [ወልድ] ለሁሉ አበራ፡፡ በጻድቃን ላይ የሚያበራ የቅዱሳን መምህር ነው፡፡ የኀሊናችንን ጨለማ የሚያበራልን ዓለምንም ይቤዥ ዘንድ ወደ እኛ የመጣ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው፡፡ እውነትን የሚለብስ እውነተኛ አምላክ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም መጥቷልና ኑ በብርሃኑ እንመላለስ፡፡ ብርሃን ወደ ዓለም መጥቷልና ከዛሬ ጀምሮ መጻተኛና ስደተኛ አይደለንም፡፡ በጨለማ ሳለን ብርሃን ወጣልን የሚያድነንም ወደ እኛ መጥቶ ተወለደልን፡፡ ኃጢአታችንም ተሻረልን፡፡ የሰማያት ኀይልና ፍጥረት ሁሉ እርሱን የሚያመሰግኑት ክርስቶስ ነው፡፡ ሕይወትን የሚያድል እርሱ ወደእኛ መጣ፡፡ ሙሴ የሰበከው የይስሐቅ ቤዛ ይህ ልጅህ ነው፡፡ የማይጨልም ብርሃንን ሰጠኸን፡፡ የአብ የምክሩ አበጋዝና ልጁ እርሱ [ክርስቶስ] ነው፡፡ ጥበብ፣ ምክር፣ የክብር ብርሃንና ለእኛ የተሰጠ የተሠወረ መዝገብ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ነን እንጂ ስደተኛና መጻተኛ አይደለንም፡፡ የሚያድን ልጁን ልኮልናልና፡፡ ጨለማን ያስወገደ ብርሃን እነሆ የእግዚአብሔር በግ ነው፡፡ እንደ ዕጣን ንጹሕ የሆነ እንደ ፀሐይ ብሩህ የሆነ የጻድቃን ብርሃናቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው፡፡ በጻድቃን ላይ የሚያበራ ብርሃንና የሰላማችን ምልክት ነው፡፡ (#በግእዝ፦ ብርሃን ዘመጽአ ውስተ ዓለም በኵረ ጽዮን ይሰመይ፡፡ ዘመጽአ እምላዕሉ እመልዕልተ ኵሉ ወበምጽአቱ አብርሀ ለኵሉ፡፡ ዘያበርህ ላዕለ ጻድቃን መምህረ ቅዱሳን፡፡ ብርሃን ዘእምብርሃን ዘመጽአ ኀቤነ ከመ ይቤዙ ኵሎ ዓለመ ወያበርህ ጽልመተ ኀሊናነ፡፡ አምላክ ማእምር ዘይለብስ ጽድቀ፡፡ እስመ ኢየሱስ ክርስቶስ መጽአ ውስተ ዓለም ንዑ ናንሶሱ በብርሃኑ፡፡ እምይእዜሰ ኢኮነ ነግደ ወፈላሴ ብርሃን መጽአ ውስተ ዓለም፡፡ እንዘ ሀሎነ ውስተ ጽልመት ሠረቀ ለነ ብርሃን ወሠረፀ ለነ መድኅን መጽአ ኀቤነ ወኀየ ኃጢአትነ፡፡ ክርስቶስ ውእቱ ንጉሠ ስብሐት ዘኪያሁ ይሴብሑ ኀይለ ሰማያት ኵሉ ኀይል ወኵሉ ፍጥረት መጽአ ኀቤነ ዐሣዬ ሕይወት፡፡ ቤዛሁ ለይስሐቅ ዝኬ ውእቱ ወልድከ ዘሙሴ ሰበከ፡፡ ብርሃን ዘኢይጸልም ጸጎከነ፡፡ ወልዱ መልአከ ምክሩ ለአብ፡፡ ጥበብ ወምክር ወብርሃነ ክብር መዝገብ ኅቡዕ ዘተውህበ ለነ፡፡ ኢኮነ ነግደ ወፈላሴ ሰብአ ቤቱ ለእግዚአብሔር ንሕነ፡፡ እስመ ፈነወ ለነ ወልዶ መድኅነ፡፡ ብርሃን ዘሰደዶ ለጽልመት ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር፡፡ ንጹሕ ከመ ዕጣን ብሩህ ከመ ፀሐይ ብርሃኖሙ ለጻድቃን ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ ብርሃን ዘእምብርሃን ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ ትእምርተ ሰላምነ ብርሃን ዘያበርህ ላዕለ ጻድቃን)፡፡

### ❖ዘኖላዊ❖

**ነገረ ክርስቶስ፦** የፈረሰውን ይሠራ ዘንድ፣ ነፍሳትንም ይቤዥ ዘንድ ቸር እረኛ [ክርስቶስ] ከሰማይ ወረደ፡፡ ሰላምን ያደርግ ዘንድ ዓለምን ሁሉም ያድን ዘንድ ከዳዊት ዘር የመጣ እረኛ [ክርስቶስ] ነው፡፡ አብን ላኪ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ወልድን ተላኪ እንደሆነ እናምናለን፡፡ መንፈስ ቅዱስን የሚያድን [የሚያኖር] እና በሰማይ ያለ ታላቅ እረኛ [ጠባቂ] እንደሆነ እናምናለን፡፡ የሰማያት ሰማይ የማይችለው ምድርም የማይበቃው [ጌታ] እንዴት የድንግል ማሕፀን ተሸከመው!!! አልጫውን የሚያጣፍጥ ጨው [ክርስቶስ] ነው፡፡ ለአሕዛብ ያበራ ዘንድ ቃል

ከሰማያት ወረደ፡፡ (#በግእዝ፦ እምሰማይ ወረደ ኖላዊ ኄር ከመ ይቤዙ ነፍሳተ ወይሕንፅ ዘተመዝበረ፡፡ ኖላዊ ዘመጽአ እምዘርዐ ዳዊት ይግበር ሰላመ ወያድኅን ኵሎ ዓለመ፡፡ ነአምን አበ ፈናዌ ወልደ ተፈናዌ መንፈስ ቅዱሰ ማሕየዌ ዐቢየ ኖላዌ ሰማያዌ፡፡ ዘሰማየ ሰማያት ኢያገምሮ ወምድርኒ ኢያአክሎ እፎ እንከ ማሕፀነ ድንግል ፆሮ፡፡ ዔው ዘአጥዐሞ ለልሱሕ፡፡ እምሰማያት አይኅዐ ቃል ከመ ያብርህ ሎሙ አሕዛብ)፡፡

**ትርጓሜ፦** የያዕቆብን ደም ግባት የወደደ [እግዚአብሔር] ነው፡፡ የያዕቆብ ደም ግባት [ውበት] ያላትም መድኀኔዓለም ክርስቶስ ከማርያም የነሣት ሥጋ ናት፡፡ (#በግእዝ፦ ሥኖ ለያዕቆብ ዘአፍቀረ፡፡ ወሥኑሰ ለያዕቆብ ዘይቤ ይእቲ ሥጋ እንተ ነሥኣ መድኅን እማርያም)፡፡

## 🍎ዘመርዓዊ🍎

**ነገረ ክርስቶስ፦** ከዳዊት ዘር የመጣ ሰማያዊ ሙሽራን ኑ እንቀበል፡፡ የሁሉ ደስታ የሚሆን ሙሽራ ደርሷልና ኑ ለመቀበል እንሒድ፡፡ ከሴት ተወልዶ የኦሪትን ሕግ ፈጸመ፡፡ የአባቱን ፈቃድ ይፈጽም ዘንድ ወልድ በጊዜው ጊዜ [በቀጠሮው] ተወለደ፡፡ (#በግእዝ፦ ንዑ ንትቀበል መርዓዌ ሰማያዌ እምዘርዐ ዳዊት ዘመጽአ፡፡ ንዑ ንሑር ውስተ ቀበላሁ መርዓዊ በጽሐ ፍሥሓ ለኵሉ፡፡ ተወልደ እምብእሲት ወገብረ በሕገ ኦሪት፡፡ ከመ ይፈጽም ፈቃደ አቡሁ ወልድ ተወልደ በዕድሜሁ)፡፡

## ✿ዘጌና✿

**ነገረ ክርስቶስ፦** ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ከድንግል ተወለደ፡፡ ከሰማያት ወረደ በድንግል ማሕፀንም አደረ፡፡ መምጣቱ ድንቅ ነው፡፡ መወለዱም ድንቅ ነው፡፡ መድኀኒታችን በተድላ መለኮት ተወለደ፡፡ እነሆ የዓለም መድኀኒት ተወለደ፡፡ መድኀኒታችን ተወልዷልና ዛሬ ታላቅ ደስታችን ነው፡፡ [ሰብአ ሰገል] ስለክህነቱ ዕጣን አገቡለት ስለመንግሥቱ ወርቅ አመጡለት፡፡ ከክብር ዙፋኑ ሳይለይ ከዳዊት ዘር በሰው ሥጋ የተወለደ ወልድን እንሰብካለን፡፡ (#በግእዝ፦ ዘሰማየ ገብረ ወምድረ ሣረረ እምድንግል ተወልደ፡፡ እምሰማያት ወረደ ውስተ ማሕፀነ ድንግል ኀደረ፡፡ መንክር ምጽአቱ ወመንክር ልደቱ፡፡ ወተወልደ መድኀኒነ በተድላ መለኮት፡፡ ወነዋ ተወልደ መድኀኔዓለም፡፡ ዮምሰ ዐባይ ትፍሥሕትነ እስመ ተወልደ መድኀኒነ፡፡ ዕጣነ ያበውኡ በእንተ ክህነቱ ወርቀ ያመጽኡ በእንተ መንግሥቱ፡፡ ንሰብክ ወልደ እምዘርዐ ዳዊት ዘመጽአ ወተወልደ በሥጋ ሰብእ እንዘ ኢየዐርቅ እመንበረ ስብሐቲሁ)፡፡

## ❀ዘልደት❀

**ነገረ ክርስቶስ፦** እናቱ በድንጋይ በረት አስተኛችው የበለስ ቅጠልም አለበሰችው፡፡ መድኀኒታችን ተወልዷልና እንግዲህ ሰላምን እንከተል፡፡ ክርስቶስ ከድንግል ስለተወለደ ዛሬ ደስታ ሆነ፡፡ የልደቱ ምስጋና በእውነት ድንቅ ነው፡፡ አዳኝ የሆነ ጌታ በበረት ተኛ በጨርቅም ተጠቀለለ፡፡ የዓለም ሁሉ መድኀኒት [ቤዛ] ዛሬ ተወለደ፡፡ ዛሬ መላእክት በሰማያት ይደሰታሉ፡፡ (#በግእዝ፦

አስከበቶ እሙ ውስተ ጎለ ዕብን ከደነቶ እሙ ቄጽለ በለሶን። ይእዜኒ ለሰላም ንትልዋ መድኀኒነ ተወልደ ነዋ። ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ እምድንግል። አማን መንክር ስብሐተ ልደቱ። በጎል ሰከበ በአጽርቅት ተጠብለለ እግዚእ ወመድኀን ቤዛ ኵሉ ዓለም ዮም ተወልደ። ዮም ይትፌሥሑ መላእክት በሰማያት)።

## ✿ዘሕፃናት✿

**ነገረ ክርስቶስ፦** ሕፃንን [ክርስቶስን] አግኝተው ሰብአ ሰገል ተደሰቱ። ሕፃናትን በእናታቸው ማሕፀን የሚስል ክርስቶስ ተወለደልን። (#በግእዝ፦ አንፈርዐፁ ሰብአ ሰገል ረኪቦሙ ሕፃነ። ተወልደ ለነ ክርስቶስ ዘይሥዕሎሙ ለሕፃናት)።

## ❁ጥር 1 ዘእስጢፋኖስ❁

**እስጢፋኖስ፦** የሰማዕታት መጀመሪያ እስጢፋኖስ ለሰዎች ምሕረትን የሚለምን ነው። በመልካም ትዕግሥቱ ዲያቆን ሆነ በሃይማኖትም ሰማዕት ነው። ዲያቆን እስጢፋኖስ እንደ ስንዴ ቅንጣት ፍሬው የበዛ ነው። እስጢፋኖስ በሃይማኖት አበባ አጌጠ አምላኩን በመውደድ ሞትን ወደደ። ስለእውነትና ስለሕይወት ደሙን አፈሰሰ። የዲያቆናት አለቃ እስጢፋኖስን ሾሙት። (#በግእዝ፦ እስጢፋኖስ ቀዳሚ ሰማዕት ዘይስእል ምሕረተ ለሰብእ። ሰማዕተ ኮነ በሃይማኖት ወዲያቆነ ኮነ በሥ[ስ]ነ ትዕግሥት። እስጢፋኖስ ዲያቆናይ ፍሬሁ ጽሩቅ ከመ ሠዊተ ሥርናይ። እስጢፋኖስ በጽጌ ሃይማኖት ተሠርገወ በፍቅረ አምላኩ መዊተ ፈተወ። በእንተ ጽድቅ ወሕይወት ደሞ ከዐወ። ሤምዎ ለእስጢፋኖስ ርእሰ ዲያቆናት)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** በመወለድ ብቸኛ የሆነ [የሠለጠነ] ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ተወለደ። በመወለዱም ደስታና ሰላም ሆነ። ሰማይን የዘረጋ በበረት ተኛ። ከእናቱ ጡት ወተትን ጠባ። ኢሳይያስ በትንቢቱ እንደተናገረ ለነፍስ ዋስ የሚሆን [ክርስቶስ] የሥጋ ልብስን ለብሶ ከድንግል ተወለደ። ወልድ በክብር በምስጋና እንደሚመጣ ነቢያት ትንቢትን ነገሩን። አንቺም የሳይዳ ምድር ቤተልሔም ከአንቺ የይሁዳ ንጉሥ ይወጣል። የጢሮስ ቆነጃጅትም ያን ጊዜ ይሰግዳሉ። ነጻነትን ይሰብክ ዘንድ ዓለምንም ያድን ዘንድ ሕፃን ተወለደልን። ዲያቆናትን ቀሳውስትንና ጳጳሳትን የሚሾም ወልድ ተወለደ። (#በግእዝ፦ ተወልደ እምድንግል ብሑተ ልደት ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ። በልደቱ ኮነ ፍሥሐ ወሰላም። ሰማየ ዘረበበ ውስተ ጎል ሰከበ እምአጥባተ እሙ ጠበወ ሐሊበ። ኢሳይያስ በትንቢቱ በከመ ደረሰ ተወልደ እምድንግል ዘይትሐበይ ነፍሰ ተዐጺፎ ዘባሦር አልባሰ። ዜነዉነ ዜና ነቢያት ከመ ይመጽእ ወልድ በስብሐት። ወአንቲኒ ቤተልሔም ምድረ ሳይዳ እምኔኪ ይወፅእ ንጉሠ ይሁዳ አዋልደ ጢሮስ አሜሃ ይሰግዳ። ሕፃን ተወልደ ለነ ከመ ይቤዙ ኵሉ ዓለመ ይስብክ ግዕዛነ። ወልድ ተወልደ ዘይሠይም ጳጳሳተ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ)።

## 🎖ጥር 3 ዘመጣዕ🎖

**አባ መጣዕ (አባ ሊባኖስ)፦** [መጣዕ] ስለእውነትና ስለሕይወት ራሱን ድኻ ያደረገ ከዓለም ደስታም የሸሸ ነው። መጣዕ ደሜ ከፈሰሰበት ሥጋዬ ከተቀበረበት በዚያ በረከት ይሁን አለ። በመልካም ሥራ የተመረጥክ ሊባኖስ ሆይ ስለእኛ ወደ አዶናይ ለምንልን። (#በግእዝ፦ በእንተ ጽድቅ ወሕይወት ርእሶ ዘአንደየ እምሐውዘ ዓለም ዘጎየ። ይቤ መጣዕ ኀበ ተክዕወ ደምየ ወተቀብረ ሥጋየ ህየ ይኩን በረከተ። ሊባኖስ ኄሩይ በምግባረ ሠናይ ርሡይ ሰአል ወጸሊ በእንቲኣነ ኀበ አዶናይ)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** ሥርዓትን ይተክል ዘንድ ቅዱሳንንም ይመራ ዘንድ ከሰማይ ወደ ምድር ወረደ። ለዓለም ሁሉ የሚነግሥ የቅዱሳን ክብር አዳኝ ወልድ በበረት ተኛ። ከተሠወሩት ይልቅ የተሠወረ እውነተኛ እግዚአብሔር ለቅዱሳን ተገለጠ። ከያዕቆብ ወገን የወጣ የቅዱሳን ፀሐይ ክርስቶስ የሃይማኖት ጥሩር ነው። (#በግእዝ፦ ሥርዓተ ይትክል ቅዱሳነ ይምራሕ ወረደ እምሰማይ ዲበ ምድር። ወልደ መድኅን ክብረ ቅዱሳን ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም ሰከበ በጎል። ዘኅቡዕ እምኅቡዓን ተከሥተ ለቅዱሳን እግዚአብሔር ዘበአማን። እምቤተ ያዕቆብ ዘሠረቀ ፀሐየ ቅዱሳን ክርስቶስ ድርዓ ሃይማኖት)።

**መንግሥተ ሰማያት፦** ከእውነተኛ ሰዎች ነፍስ ጋር ሁሉ እንገባባት ዘንድ የእኛስ ሀገራችን ከላይ ያለችዋ መንግሥተ ሰማያት ናት። (#በግእዝ፦ ወለነሰ ሀገሪትነ እንተ እምላዕሉ ቅድስት ይእቲ ከመ ንባእ ምስለ ነፍሰ ኵሎሙ ሰብእ ጻድቃን)።

## ❦ጥር 4 ዘዮሐንስ❦

**ዮሐንስ ወንጌላዊ፦** የነጎድጓድ ልጅ ዮሐንስ ሆይ ትማልድልን ዘንድ እንለምንሃለን። የጥበባት ባሕር፣ የልሳናት አባት፣ ከፍ ብሎ የሚበር ንስር፣ ወንጌላዊ፣ ምሥጢርን ያየ፣ ነገሩ በመለኮት ጨው የጣፈጠ ነው። በእጁ የወንጌልን ቃላት እየጻፈ አየራትን ያያል ምሥጢራትን ይናገራል። ሞትን ያልቀመሰ ዮሐንስ ድንግል ወገቡን በጌታው መታጠቂያ ታጠቀ። በቅድስና ያጌጠ፣ በድንግልና የጸና ዮሐንስ ስድብን እየታገሠ እስኪያሳምናት ድረስ በማንደጃ ቤት ለሮምና አገለገለ። ከልጅነቱ ጀምሮ ያለበደል ያደገ፣ ከእሳት አጠገብ የተቀመጠ ዮሐንስ ነው። [ዮሐንስ ሆይ] በስብከትህ አብርተሀልና ኮከብ ብለን ጠራንህ። ደስ የሚያሰኝ ምሥጢርን ያየህ በምድር ያለህ መልአክ ነህ። ከአማረ የዮሐንስ አፍ ሽቱ ተገኘ። እነሆ በወንድሞች መካከል ወንጌልን የሚሰብክ ነው። ወልድ መረጠህ በአፉም ሳመህ። ሐዋርያት በመልካም ሥራህ ያመሰግኑሀል በቃልህ ጣዕምም ይደሰታሉ። አቡቀለምሲስ የማርያም ልጅ የመረጠው ሐዋርያና ድንግል ነው። (#በግእዝ፦ አስተምሕር ለነ ሰአልናከ ወልደ ነጎድጓድ ዮሐንስ። ባሕረ ጥበባት አበ ልሳናት ንስር ሠራሪ ልዑለ ስብከት ዮሐንስ ወንጌላዊ ሬዓዬ ኅቡዓት ነገሩኒ ቅሱም በጼወ መለኮት። ይኔጽር አየራተ ይነግር ኅቡዓተ እንዘ ይጽሕፍ በእደዊሁ ዘወንጌል ቃላተ በቅናተ እግዚኡ ሐቋሁ ቀነተ ዮሐንስ ድንግል ዘኢጥዕመ ሞተ። ዮሐንስ ሥርግው በቅድስና ዮሐንስ ቅኑት በድንግልና ውስተ ቤተ ምንዳድ ተቀንየ ለሮምና እንዘ ይትዔገሥ ጽእለተ እስከ አእመና። ዮሐንስ ውስተ ሕፅነ እሳት ዘረፈቀ እንበለ ርስሐት እምንዕሱ ዘልህቀ። ኮከበ ሰመይናከ እስመ አብራህከ በስብከትከ።

መልአክ ዘበምድር ረዓዬ ምሥጢር ምዑዝ። እምአፈ ዮሐንስ ሥርግው ተቀስመ አፈው ሰባኬ ወንጌል ነዋ በማዕከለ አኃው። ኀረየከ ወልድ ወሰአመከ በአፉሁ። ይዌድሱከ ሐዋርያት በእንተ ሥነ ግብርከ ወይትፌግዑ በጣዕመ ቃልከ። አቡቀለምሲስ ድንግል ወሐዋርያ ዘኀረዮ ወልደ ማርያ)።

## ❧ዘሰንበት❧

**ነገረ ክርስቶስ፦** ፀሐይ ወጣ። ጌታ ተገኘ። አምላክ ተመሰገነ ከቅድስት ድንግልም ተወለደ። መለኮቱ አልጠፋም። (#በግእዝ፦ ፀሐይ ሠረቀ ወእግዚእ ተረክበ ወአምላክ ተአኰተ ወተወልደ እምቅድስት ድንግል እስመ መለኮቱ ኢማሰነ)።

## ❦ዘዘወትር❦

**ነገረ ክርስቶስ፦** [ኢየሱስ] ኪሩቤል ሳያዩት የድንግልን ቁልፍ ሳይከፍት ወደ ዓለም መጣ። ማደርያው ኢዮር ዙፋኑ ኪሩቤል የሆኑለት እግዚአብሔር ከእርሷ ሰው የሆንኩባትን ድንግልን እኔ ራሴ በእጄ ፈጠርኳት አለ። በአካል ሦስት የሆነ ማለትም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የተባለ እግዚአብሔር በባሕርይ አንድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የገነት ምንጭ፣ የሕይወት ውሃ ጉድጓድ ነው። አብ ልጁን በብዙዎች ዘንድ በኵር ትሆን ዘንድ ና ከሰማይ ወደ ምድር ውረድ አለው። [ክርስቶስ] የዋህ በግ፣ ንጹሕ ዕንቍ ነው። ከዳዊት ዘር የተገኘ ዕንቍ ነው። ሕፃናትን በማሕፀን ውስጥ የሚፈጥር፣ ዳዊት የዘመረለት፣ ነቢያት የሰበኩት [ክርስቶስ] ከሰማያት ወደ ምድር ወረደ። የጠፋውን ያገኝ ዘንድ ወልድ ምድራዊት በሆነች በሥጋ ተሰቀለ። እሺ ብሎ መጥቶ ሥጋችንን ተዋሐደ። በዚህች ከአዳም በነሣት ሥጋም ተሰቀለ። ከዕሴይ ሥር የክብር ፍሬ ወጣ። በቃሉ የሚያድን ጌታ ልደቱ እውነት ነው። በምድር መካከል መድኀኒትን አደረገ። ቅዱሳት እጆቹን በመስቀል እንጨት ላይ ዘረጋ። የሚያምንበት አይታወክም አይደነግጥምም። የርስታችን ፈለማ ፍጹም ውበታችንና ሽልማታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አባታችን አዳምን ከልጅህ እወለዳለሁ አልከው። ቃልህ አልታበለም እውነት ሆነ። እርሱ የሚሰግድለት የሌለ ለእርሱ ሁሉ ለሚሰግድለት ለእርሱ እንስገድ። ለእርሱ ሁሉ የሚገዛለት እርሱ ለማንም ለማይገዛ ለእርሱ እንገዛ። ከበደላችን ያድነን ዘንድ ክርስቶስ ወደእኛ መጣ። (#በግእዝ፦ መጽአ ውስተ ዓለም ዘድንግል መናሥግተ ኢያርኂዎ ወኪሩቤል ኢርእዮ። ለልየ በእዴየ ለሐኰዋ ለድንግል እንተ እምኔሃ ተሰባእኩ ይቤ እግዚአብሔር መንበሩ ዘኪሩቤል ዘኢዮር ማኅደሩ። አሐዱ ውእቱ እግዚአብሔር አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ። ዐዘቅተ ማየ ሕይወት ነቅዐ ገነት ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ። ይቤሎ አብ ለወልዱ ነዓ ረድ እምሰማይ ዲበ ምድር ከመ ትኩን በኵረ በላዕለ ብዙኃን። ባሕርይ ንጹሕ በግዕ የዋህ። ባሕርይ ዘተረክበ እምዘርዐ ዳዊት። ዘይሥዕሎሙ ለሕፃናት በውስተ ማሕፀን እምሰማያት ወረደ ዲበ ምድር ዘዳዊት ዘመሮ ነቢያት ሰበክዎ። ተሰቅለ ወልድ በሥጋ ምድራዊት ከመ ይርከብ ዘተኀጕለ። አሆ ይቤ ወመጽአ ለብሰ ሥጋነ ተሰቅለ በይእቲ ሥጋ እንተ እምአዳም ነሥአ። እምሥርወ ዕሴይ ሠረፀ ፍሬ ስብሐት። አማን ልደቱ ዘያሐዩ በቃሉ። ገብረ መድኀኒተ በማዕከለ ምድር ሰፍሐ ዕደዊሁ ቅዱሳት ዲበ ዕፀ

መስቀል። ዘየአምን ቦቱ ኢይደነግጽ ወኢይትሐወክ። ዐረቦነ ርስትነ ፍጹመ ሥንነ ወትርሢትነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ትቤሎ ለአቡነ አዳም እትወለድ እምወለትከ እሙነ ኮነ ኢተሐሰወ ቃልከ። ንስግድ ሎቱ ዘሎቱ ኵሉ ይሰግዱ ውእቱሰ አልቦ ለዘይሰግድ ለዘሎቱ ኵሉ ይገኒ ውእቱሰ አልቦ ለዘይገኒ። ከመ ያድኅነነ እምጌጋይነ ክርስቶስ መጽአ ኀቤነ)።

**ትርጓሜ፦** ዳዊትም ጠል በፀምር እንደሚወርድ ነው አለ። ፀምር የተባለች ማርያም ናት። በትር ከዕሴይ ሥር ትወጣለች። ከግንዱም አበባ ይወጣል። ይቺ በትር የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት። ከእርሷ የወጣው አበባም የወልድ ምሳሌ ነው። (#በግእዝ፦ ዳዊትኒ ይቤ ወይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር። ፀምርሰ ይእቲ ማርያም። ትወፅእ በትር እምሥርወ ዕሴይ ወየዐርግ ጽጌ እምጕንዱ። ይእቲ በትር አምሳለ ማርያም ቅድስት ይእቲ። ወጽጌ ዘወፅአ እምኔሃ አምሳሉ ለወልድ)።

**ነገረ ማርያም፦** ማርያምስ የእግዚአብሔር ድልድይ ሆነችልን። የነጻነታችን ምስክር መመኪያችን ይቺ ናት። ሥጋዋን አንጽቶ በእርሷ አደረ። (#በግእዝ፦ ማርያምሰ ተንከተመ እግዚአብሔር ኮነት ለነ። ዛቲ ይእቲ ትምክህትነ ስምዐ ግዕዛንነ። አንጺሖ ሥጋሃ ኀደረ ላዕሌሃ)።

## ዘክብረ ቅዱሳን

**ነገረ ማርያም፦** ነቢያትና ሐዋርያት ሁላቸው ድንግል ማርያምን መቻልን የማይቻለውን እንዴት ቻልሽው መሸከምን የማይሸከመውን እንዴት ተሸከምሽው አሏት። ማርያምም እስኪ ጠይቁ ብነግራችሁ ከአፌ እሳት ወጥቶ ዓለምን ሁሉ ያጠፋል አለቻቸው። (#በግእዝ፦ ይቤልዋ ኵሎሙ ነቢያት ወሐዋርያት ለማርያም ድንግል እፎ ጾርኪዮ ለዘኢይጾወር ተጾውሮ እፎ አግመርኪዮ ለዘኢይትገመር ተገምሮ። ወትቤሎሙ ማርያም እስኩ ጠይቁ እመ ነገርኩክሙ ይወፅእ እሳት እምአፉየ ወያውዒ ኵሎ ዓለመ)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** ወልድ ሰው በሆነ ጊዜ መላእክት አላወቁም። ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደውን እረኞች አዩት መላእክት አመሰገኑት። ከክብሩ ሳይጎድል መለኮቱን ሠውሮ ወደ ሥጋችን ወረደ። (#በግእዝ፦ ሶበ ይወርድ ወልድ ኢያእመሩ መላእክት። ኖሎት ርእይዎ አእኰትዎ መላእክት ለዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል። እንዘ ኢየሐጽጽ ወረደ ውስተ ሥጋነ ኀቢያ መለኮቶ)።

## 🌹ጥር 6 ዘግዝረት🌹

**ነገረ ክርስቶስ፦** በሰምንተኛው ቀን ይገዝሩት ዘንድ ሕፃኑን ወሰዱት። ስሙንም አማኑኤል አሉት። በእስራኤል ሕግ መሠረት አማኑኤል ዛሬ ተገዘረ። (#በግእዝ፦ ወአመ ሰሙን ዕለት ወሰድዎ ለሕፃን ከመ ይግዝርዎ ወሰመይዎ ስሞ አማኑኤል። ተገዝረ ዮም አማኑኤል በከመ ሕጎሙ ለእስራኤል)።

## ●ዘናዝሬት●

**ነገረ ክርስቶስ፦** በቤተልሔም ተወለደ በናዝሬት አደገ። ናዝራዊ ይባል ዘንድ ወደ ናዝሬት ገባ። አብ ከልጁ አይበልጥም ልጁም ከአባቱ አይጎድልም። (#በግእዝ፦ በቤተልሔም ተወልደ ወበናዝሬት ተሐፅነ። ቦአ ናዝሬተ ከመ ናዝራዊ ይሰመይ። ኢየዐቢ አብ እምወልዱ ወኢየሐጽጽ ወልድ እምወላዲሁ)።

## ❦ጥር 11 ዘጥምቀት❦

**ነገረ ክርስቶስ፦** ክርስቶስ በዓለም ታየ። ከድንግል ተወለደ። ለዘመዶቹ እየታዘዘ ተገለጠ። ሰው ሆኖ በዮርዳኖስ ተጠመቀ። የክርስቶስ የመለኮት ውበት መገለጥ ሆነ። ይቤዠን ዘንድ በዮርዳኖስ ተጠመቀ። ወልድ ከሰማያት ወደ መጠመቂያዎች በደስታና በሰላም ወረደ። የመላእክት ማኅበር ሁሉ በሰው ሥጋ የተገለጠውን [ክርስቶስን] ፈጽመው ያመሰግናሉ። የሕይወት መንፈስና የመንፈስ ክብር የሆነ የከበረ ደሙንና እኛን የሚያነጻን ውሃን [ማየ ገቦን] ሰጠን። ክርስቶስ ተወለደ ክርስቶስ ተጠመቀ። ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ወለደን። የእውነት ፀሐይ መገለጡ እውነት ሆነ። በየጥቂቱ አደገ በሠላሳ ዓመት በዮርዳኖስ ተጠመቀ። ዙፋኑ በኢዮር ላይ የሆነ መመላለሻው ደመና የሆነ፣ አዳራሹ የእሳቱ ጣሪያው ውሃ የሆነ [እግዚአብሔር] ነው። ያ ቃል ሰው ሆነ ከባሕርዩም አልተለወጠም። መገለጥ ሆነ በግልጥ ታየ። መሬታዊ በዮርዳኖስ አጠመቀው። ታላላቆች አዩት፣ አመሰገኑት፣ አደነቁት። (#በግእዝ፦ ክርስቶስ አስተርአየ ውስተ ዓለም። እምድንግል ተወልደ ክሡተ ኮነ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ። ከዊኖ ሰብአ በዮርዳኖስ ተጠምቀ። አስተርእዮ ኮነ ዘክርስቶስ ሥነ መለኮት። በዮርዳኖስ ተጠምቀ ከመ ይቤዝወነ። ወረደ ወልድ እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት በፍሥሓ ወበሰላም። ኵሎሙ ማኅበረ መላእክቲሁ ይሴብሑ ወይዜምሩ ለዘበሥጋ ሰብእ አስተርአየ። ወደሞ ክቡረ መንፈሰ ሕይወት ወቅድሳተ መንፈስ ወሀበነ ማየ መንጽሔ ዚኣነ። ክርስቶስ ተወልደ ክርስቶስ ተጠምቀ ወለደነ ዳግመ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ። እሙነ ኮነ ለፀሐየ ጽድቅ አስተርእዮቱ። በበሕቅ ልህቀ በሠላሳ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ። ዘዲበ ኢዮር መንበሩ ደመና መንኰራኵሩ እሳት ጽርሑ ማይ ጠፈሩ። ውእቱ ቃል ተሠገወ ወኢተመይጠ እምህላዌሁ። አስተርእዮ ኮነ ወአስተርአየ ገሐደ። መሬታዊ አጥመቆ በዮርዳኖስ ልዑላን ርእይዎ አንከርዎ አስተብፅዕዎ ወሰብሕዎ)።

**ምሥጢረ ሥላሴ፦** በአብ እናምናለን በወልድም እናምናለን በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን። (#በግእዝ፦ ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ)።

## ❦ጥር 12 ዘቃና ዘገሊላ❦

**ነገረ ክርስቶስ፦** ከእኛ ተሠውሮ ሲኖር ዛሬ ግን የተገለጠ ሆነ ውሃውንም ወይን አደረገው። የማይታየው ታየ። (#በግእዝ፦ እንዘ ሥውር እምኔነ ይእዜሰ ክሡተ ኮነ ወለማይኒ ረሰዮ ወይነ። አስተርአየ ዘኢያስተርኢ)።

### ✤ዘቴዎድሮስ✤

**ቅዱስ ቴዎድሮስ፦** ሰማዕት ቴዎድሮስ የመስቀልን ስቃይ አልፈራም። ኀያል ቴዎድሮስ የቃል ሰማዕት ነው። ሰማዕት ቴዎድሮስ የንጉሥን ትእዛዝ አልፈራም። ቴዎድሮስ ማለት መሥዋዕት ማለት ነው። በዕለተ ዓርብ አምላክ የተቀበለውን መከራ አስቦ መከራን ሲቀበል በእንጨት መስቀል ላይ ችንካርን ሲታገሥ ባዩት ጊዜ ኀይላት አደነቁት። (#በግእዝ፦ ስቃየ መስቀል ኢፈርሀ ሰማዕት ቴዎድሮስ። ቴዎድሮስ ኀያል ሰማዕተ ቃል። ቴዎድሮስ ሰማዕት ኢፈርሀ ትእዛዘ ንጉሥ። ቴዎድሮስ ብሂል መሥዋዕት ብሂል። ያስተበፅዕዎ ኀይላት ለቴዎድሮስ አመ ርእይዎ ዲበ ዕፀ መስቀል እንዘ ይትዔገሥ ቅንዋተ ወያበዝኅ ሕማማተ በዘነለየ ወተዘከረ ሕማመ አምላክነ ዘዓርብ)።

## ☦ዘክብረ ቅዱሳን☦

**ነገረ ክርስቶስ፦** ወልደ አምላክ ቤዛችን ተስፋችን ነው። የቅዱሳን ክብር የሆነ ክርስቶስ ተወለደ። በመጠመቁም መለኮቱ ታወቀ። ለፍጥረት ሁሉ በረከትን የሚመግብ [ክርስቶስ] ወተትን ጠባ። ነጭ ወፍ፣ ንጉሥ የሆነ አንበሳ ስለእኛ በዮርዳኖስ ወንዝ በውሃ ተጠመቀ። (#በግእዝ፦ ቤዛነ ተስፋነ ወልደ አምላክ። ተወልደ ለነ ክርስቶስ ክብረ ቅዱሳን። ወበጥምቀቱ ተዐውቀ መለኮቱ። ሐሊበ ጠበወ ለኵሉ ፍጥረት ዘይሴሲ በረከተ። ዖፍ ጸዓዳ ንጉሥ አንበሳ ተጠምቀ በማይ በዮርዳኖስ ቀላይ በእንቲኣነ)።

## ❀ዘመርዓዊ❀

**ነገረ ክርስቶስ፦** ለዓለም ሁሉ አባትና እናት የሆነ ሰማያዊ ሙሽራ ወደእኛ መጣ። (#በግእዝ፦ መርዓዊ ሰማያዊ መጽአ ኀቤነ አብ ወእም ለኵሉ ዓለም)።

## ❀ዘዘወትር❀

**ትርጓሜ፦** የልጅ ወንድሜ መዓዛ በአትክልት ቦታ እንዳለ እንደ ነጭ ዕጣን ነው። ይህም በልደት ብቸኛ የሆነ ልጅህ ነው። የእስራኤል ኀይላቸው በሰው ሥጋ ታየ። (#በግእዝ፦ መዓዛሁ ለወልድ እኁየ ከመ ጼና ስሒን ዘውስተ ገነት ዝኬ ውእቱ ወልድከ ብሑተ ልደት። ኀይሎሙ ወጽንዖሙ ለእስራኤል አስተርአየ በሥጋ ሰብእ)።

## ❤ዘክብረ ቅዱሳን❤

**ነገረ ክርስቶስ፦** እንደ ሰው [ሰው እንደመሆኑ] ታይቶ [እየታየ] ተመላለሰ። በአባቱ ፈቃድ መለኮቱን ከሥጋችን አዋሐደ። ከግሩማን ይልቅ ግሩም የሆነ፣ ወደ ዓለም የመጣ፣ የቅዱሳን ክብራቸው፣ ያዘኑትን የሚያረጋጋ [ክርስቶስ] ነው። (#በግእዝ፦ አንሶሰወ ወአስተርአየ ከመ ሰብእ ተመሰለ። በፈቃደ አቡሁ ደመረ ውስተ ሥጋነ መለኮቶ። ግሩም እምግሩማን ዘመጽአ ውስተ ዓለም ክብሮሙ ለቅዱሳን መናዝዜ ኅዙናን)።

## ♥ጥር 15 ዘቂርቆስ♥

**ቅዱስ ቁርቆስ፦** ሕፃን እናቱን 'እናት ጨክኚ እንጂ አትጠራጠሪ። ዛሬ ከአርያም የኀበኘን አምላካችንን ደስ እናሰኘው ዘንድ ምስክርነታችንንና ተጋድሏችንን እንፈጽማለን' አላት። ንዑድ ክቡር ቁርቆስን የሚበልጠው የለም። (#በግእዝ፦ ይቤላ ሕፃን ለእሙ ጥብዒኬ እም ወኢትናፍ*ቂ ዮም ንፈጽም ገድለነ ወስምዐነ ከመ ናሥምሮ ለአምላክነ ለዘሐወፀነ እምአርያም። ለብፁዕ ቁርቆስ አልቦ ዘይሞግሦ)።

## ❖ጥር 21 ዘማርያም❖

**ነገረ ማርያም፦** በእርሷ ቃል የተሞሸረባት ፍጽምት ድንኳን ማርያም ናት። አዲስ መርከብ፣ ለፍጥረት ሁሉ ምግብ የሆነ መና ያለባት ቀና ናት። በድንግል ማርያም ዕረፍት ጊዜ ወልድ ከልዕልና ወረደ። እንደ ሰው ሁሉ ሞት በኀበኛት ጊዜ የአምላክ እናት እንዴት አለቀሰች!!! (#በግእዝ፦ ደብተራ ፍጽምት እንተ በላዕሌሃ ተመርዐወ ቃል። ሐዳስ ሐመር ዘመና ጎሞር ሲሳየ ኵሉ ፍጡር። ጊዜ ዕረፍታ ለሶልያና ወረደ ወልድ እምዲበ ልዕልና። እፎኑመ እመ አምላክ በከየት ደንጊፃ ከመ ኵሉ ሰብእ ሞት ሶበ ሐወጻ)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** ነበልባልን የሚጎናጸፍ ሰውነትን ተዋሐደ። ሰማይን የዘረጋ ከድንግል ተወለደ። እርሷን እናቱ አደረጋት። በደልን የሚያነጻ ውሃን ሰጠን። ብርሃናትን እንደ ልብስ የሚጎናጸፍ ብዙ መላእክት የሚያመሰግኑት ጌታ ከድንግል ተወለደ። ሙሴና ዳዊት ጠል ያሉት ቃልን ማርያም ወለደችው። ቃል በቃሉ ተናገራት በመልአክ አምሳል ታያት። በማርያም ማሕፀን ተፀነሰ በጨርቅ ተጠቀለለ። (#በግእዝ፦ ለብሰ አባለ ዘይትዐፀፍ ነበልባለ። ዘሰፍሐ ሰማየ እምድንግል አስተርአየ እሞ ወላዲቶ ኪያሃ ረሰየ መንጽሔ አበሳ ወሀበነ ማየ። ብርሃናተ ከመ ልብስ ዘይትዐፀፍ አስተርአየ እምድንግል ዘይሴብሕዎ አእላፍ። ሙሴ ወዳዊት ዘሰመይዎ ጠለ ማርያም ወለደት ቃለ። አስተርአያ ለማርያም በአምሳለ መልአክ ቃል በቃሉ ተናገራ። ውስተ ማሕፀና ለማርያም ተዐቍረ ተፀውረ በከርሣ ተጠብለለ በአጽርቅት)።

## ❤ዘማኅበር❤

**ነገረ ክርስቶስ፦** ከግሩማን ሁሉ ግሩም የሆንክ፣ ታላቅነት ገንዘብህ የሆነ፣ ክብርህ ድንቅ የሆነ [ክርስቶስ ሆይ] በቅዱሳን ማኅበር ምስጉን ነህ። ለደካሞች ኀይላቸው ነው። በታላላቆች የሚያድር በትሑታን የሚመሰገን፣ ዓለምን ሁሉ የያዘ ነው። ከዓለም በፊት ብርሃንን የፈጠረ፣ የመንግሥት ክብሩ በእውነት ጸንቶ የሚኖር፣ ነገሥታትንና ካህናትን እርሱ ራሱ የሚሾም ነው። የተሠወረ ምሥጢሩን በቅዱሳን ማኅበር ገለጠ። ታላቁ እረኛ ደስተኞች ከሆኑ ከብዙ መላእክት ጋር እስኪመጣ ድረስ እንግዲህ ለመቀበል የተዘጋጃችሁ ሁኑ። አብ ወልድን ለእኛ ክብር እንደላከ እናምናለን። እውነተኛ አምላክ የማይጨልም ብርሃን ነው። ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው በጥምቀቱም ውሃ ተቀደሰ። የነዳያን ገንዘብ፣ የመላእክት ክብራቸው ነው። ዘጠና ዘጠኙን ነገድ ትቶ ከሰማያት ወረደ። (#በግእዝ፦ ግሩም እምግሩማን ዕበይ ብከ ወመንክር ስብሐቲከ ስቡሕ አንተ ክርስቶስ በውስተ ማኅበረ ቅዱሳን። በማኅበረ ቅዱሳን ይሴባሕ። ኀይል

*ወጽንዕ ለድኩማን:: ዘየኀድር በልዑላን ወይሴባሕ በትሑታን:: አኃዜ ኵሉ ዓለም:: ዘእምቅድመ ዓለም ብርሃነ ኀታሚ ስብሐተ መንግሥት በጽድቅ ቀዋሚ ነገሥተ ወካህናተ ለሊሁ ሠያሚ:: በማኅበረ ቅዱሳን ከሠተ ምሥጢሮ ኅቡዐ:: ኵኑ እንከ ድልዋኒክሙ ለቀበላሁ እስከ ይመጽእ ዐቢይ ኖላዊ እምሰማይ በአእላፍ መላእክቲሁ ፍሡሓን:: ነአምን ከመ ፈነወ አብ መድኅነ ለክብረ ዚኣነ:: አምላክ ዘበአማን ዘኢይጸልም ብርሃን:: አጥመቆ ዮሐንስ ለኢየሱስ ተቀደሰት ማይ በጥምቀቱ:: ክብሮሙ ለመላእክት ንዋየ ነዳያን:: ኀዲጎ ፺ ወ ፱ተ ነገደ እምሰማያት ወረደ)::*

## ❢ዘማርያም እንተ ዕፍረት❢

**ማርያም እንተ ዕፍረት፦** ለዚህች ሴት የአብ የጸጋው ክብር በእርሷ ላይ ሆነ:: ከክፉ ወደ መልካም ነጻ አወጣት:: ስሟንም በዓለም ሁሉ ያስቡ ዘንድ አደረገ:: *(#በግእዝ፦ ለዛቲ ብእሲት ሠረቀ ላዕሌሃ ብዕለ ጸጋሁ ለአብ ወአግዐዛ እምእኩይ ውስተ ሠናይ እሞት ውስተ ሕይወት ወረሰየ ይዝክሩ ስማ ውስተ ኵሉ ዓለም)::*

## ❤የካቲት 8 ዘስምዖን❤

**ስምዖን፦** የሚያስፈራ አንበሳን ተሸከመ ጩኸቱ አላስፈራውም:: ካህን ስምዖን ሕፃኑን ተሸከመው ኪሩቤልንም መሰለ:: ስምዖን ሕፃኑን በእቅፉ ተቀበለው:: *(#በግእዝ፦ ፆሮ ለአንበሳ ግሩም ወኢያፍርሆ ጥኅረቱ ስምዖን ካህን ፆሮ ለሕፃን ወተመሰለ ከመ ኪሩቤል:: ስምዖን ተወክፎ ውስተ ሕፅኑ ለሕፃን)::*

## ❤የካቲት 16 ዘኪዳነ ምሕረት❤

**ነገረ ማርያም፦** ማርያም ሆይ ኪዳንሽ ለእኛ ለኃጥኣን ተስፋ ሆነ:: አንቺ ምሥራቅ ነሽ ልጅሽም የእውነት ፀሐይ ነው:: በእውነት ኪዳንሽ አያልቅም:: ድንግል ሆይ እህልን ትቶ ሥጋ ሰብእን የሚበላ [በላኤ ሰብእ] በኪዳንሽና በስምሽ በታመነ ጊዜ በእፍኝ ውሃ ከገሃነም ስቃይ ዳነ:: በኪዳንሽ የንስሓ መንገድን ምሪኝ:: ድንግል ማርያም የእግዚአብሔር ማደሪያ ናት:: ማርያም ሆይ ኪዳንሽ ከባርነት ነጻ ያወጣናል:: *(#በግእዝ፦ ኪዳንኪ ኮነ ማርያም ለኃጥኣን ተስፋነ:: አንተ ምሥራቅ ወወልድኪ ፀሐየ ጽድቅ አማን ኪዳንኪ ኢየኀልቅ:: አኮኑ ድንግል ሶበ በስምኪ ተወከለ ወበኪዳንኪ ተአመነ ኀዲጎ እክለ በላዔ ሥጋ ሰብእ ዘኮነ በሕፍነ ማይ እምሥቃየ ገሃነም ድኅነ:: በኪዳንኪ ምርሕኒ ፍኖተ ንስሓ:: ማርያም ድንግል ለእግዚአብሔር ማኅደሩ:: ኪዳንኪ ማርያም ያግዕዘነ እምግብርናት)::*

## 💘መጋቢት 5 ዘገብረ መንፈስ ቅዱስ💘

**ገብረ መንፈስ ቅዱስ፦** ቤተክርስቲያን ከምንላት አቅሌስያ የወጣ ብሩህ ኮከብ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያ ለግብጽና ለኢትዮጵያ ሰዎች በእውነት አባት ሆናቸው:: የዋህና ጻድቅ ገብረ ሕይወት የመላእክት ወገናቸው ነው:: የሥጋ ልብስን ያልለበሰ ገብረ ሕይወት የዱር አናብስትን

አዘዘ:: የሰው ነፍሳትን ከመገዛት ነጻ አወጣ:: ከተድላ ይልቅ ትካዝን አበዛ:: ክንፋቸው እሳት የሆኑ ግሩማን ሱራፌልና ኪሩቤል በእውነት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ኀይልን የሚያደርግ ነው በማለት ሊቀበሉት ወረዱ:: ዓለምን የናቀ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የጌታውን መንገድ ተከትሏልና ሰይጣንንና ሞትን ገዛ:: (#በግእዝ፦ ኮከብ ብሩህ ዘሠረቀ እምአቅሌስያ ቤተክርስቲያን ዘንሰምያ ኮናሙ አበ ለሰብአ ግብጽ ወኢትዮጵያ አማን ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያ:: ጻድቅ ወየዋህ ገብረ ሕይወት ዘውኀሙ ለመላእክት:: ገብረ ሕይወት አናብስተ ገዳም አዘዘ ወነፍሳተ ሰብእ እምቅንየት አግዐዘ እስመ ኢፈቀደ ዘሥጋ አራዘ ወህየንተ ተድላ አብዝኀ ትካዘ:: ግሩማን መላእክት ሱራፌል ወኪሩቤል እለ አክናፊሆሙ ነበልባል ወረዱ ዮም ይትቀበሉ በብሂል አማን ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገባሬ ኀይል:: ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዓለመ ዘመነነ ፍኖተ እግዚኡ እስመ ዴገነ ቀነየ ሞተ ወሰይጣነ)::

# ድጓ ዘፋሲካ ወዘክረምት በግእዝና በአማርኛ ማስታዎሻ



**አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ**

**(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ መምህር)**

**ነሐሴ ፲፩፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም**

## ❤ዘፋሲካ❤

**ፋሲካ፦** ይህቺ ፋሲካ ደገኛዪቱ ሕግ ናት። ሰማያት በዓልን ያደርጋሉ ደመናዎች በዓልን ያደርጋሉ። ምድርም በክርስቶስ ደም ታጥባ ፋሲካን ታደርጋለች። [ክርስቶስ] በሦስተኛው ቀን ሞትን አሸንፎ በሰንበት ትንሣኤን አደረገ። ቅዳሜ ማታ ለእሑድ አጥቢያ ትንሣኤ ሆነ። ክርስቶስ በታላቅ ኀይልና ሥልጣን ከሙታን መካከል ተነሣ። ሰይጣንን አስሮ አዳምን ነጻ አወጣው። ከዛሬ ጀምሮ ሰላም ይሁን። በሰንበት የጨለማ ኀይል ራቀ። ዛሬ በዚህች ቀን በሰማያት የሕይወት ተስፋ ተሠራ። ይቺ ፋሲካ የመድኃኒታችን የትንሣኤው መታሰቢያ ናት። ደገኛ የሆነች ይቺ ፋሲካ ክፉ የሆነ የሞት መርዝ የተሸነፈባት ናት። የፋሲካ በዓልን ትንሣኤ አላት። ትንሣኤህን ለምናምን ብርሃንን ወደእኛ ላክ። ፋሲካ ማለት በእርሱ ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገርንበት መሻገሪያ ማለት ነው። የዓለም መድኀኒት ክርስቶስ ዛሬ ከሙታን መካከል ተነሣ። ይቺ ፋሲካ የፍጹም ብርሃን ቀን ናት። በፋሲካው ቤቷን ሠራ ስሟንም የሰላም ቤት አላት። (#በግእዝ፦ ዛቲ ፋሲካ ቀዳሚት ሕግ። ይገብሩ በዓለ ሰማያት ይገብሩ በዓለ ደመናት ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ። አመ ሣልስት ዕለት ሞያ ለሞት ገብረ ትንሣኤ በሰንበት። ሠርከ ሰንበት ለጸቢሐ እሑድ ኮነ ትንሣኤ። ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዐቢይ ኀይል ወሥልጣን አሰሮ ለሰይጣን አግዐዞ ለአዳም ሰላም እምይእዜሰ ይኩን ሰላም። ተሰደ ኀይለ ጽልመት በሰንበት። ተሠርዐ ተስፋ ሕይወት በሰማያት ዮም በዛቲ ዕለት። ዛቲ ፋሲካ ተዝካረ ትንሣኤሁ ለመድኀኒነ። ዛቲ ፋሲካ ቀዳሚት ሕግ እንተ ባቲ ተሞዐ ሕምዘ ሞት ጸዋግ። ትንሣኤ ሰመያ ለበዓለ ፋሲካ። ትንሣኤከ ለእለ አመነ ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ። ፋሲካ ብሂል ማዕዶት ብሂል በዘቦቱ አዶነ እሞት ውስተ ሕይወት። ዮም ተንሥአ እሙታን ክርስቶስ መድኀኔዓለም። ዛቲ ፋሲካ ዕለተ በርህ ወዋካ። በፋሲካሁ ሐነፀ ጥቅማ ቤተ ሰላም ሰመየ ስማ)።

**ሰንበተ ክርስቲያን፦** ክርስቶስ ከሙታን መካከል ተነሥቷልና ዛሬ በሰንበተ ክርስቲያን ደስታ ሆነ። ከዕለታት ሁሉ ለይቶ አከበራት። ይቺ ቀን በመከራ ውስጥ ለነበሩት ፍጹም ዕረፍት ሆነቻቸው። ለጻድቃንም ታላቅ ደስታን ሆነቻቸው። ቀደምት ከሆኑ በዓላት የምትበልጪ ሰንበተ ክርስቲያን ሆይ በሰላም ነይ። (#በግእዝ፦ ዮም ፍሥሓ ኮነ በሰንበተ ክርስቲያን እስመ ተንሥአ ክርስቶስ እሙታን ቀደሳ ወአክበራ እምኵሎን መዋዕል አልዐላ። ዛቲ ዕለት ናህየ ወዕረፍተ ኮነቶሙ ለእለ ውስተ ደይን ወለጻድቃን ኮነቶሙ ዐቢየ ትፍሥሕተ። ንዒ በሰላም ሰንበተ ክርስቲያን እንተ ይእቲ ርእሰ በዓላት ቀደምት)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** ከሚነድ እሳት አዳነን። ብርሃናትን የሚጎናጸፍ [ጌታ] ተነሣልን። ቀድሞ ብዙ ሙታንን አስነሥቶ በሦስተኛው ቀን ተነሣ። ከዚህ በኋላ ዳግመኛ ሞት አያገኘውም። በድንቅ ጥበቡ ከሙታን መካከል የተነሣ ኢየሱስን ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በበፍታ ገነዙት። ክርስቶስ ተነሥቷልና አሕዛብ ሁላችሁ በእጃችሁ አጨብጭቡ። ቤዛችን ሲኦልን ረግጦ ሞትን ሽሮ ተነሣ። በምድር የነበረ ጥፋትን ሁሉ አስወገደ። ስለእኛ ተሰቀለ። እኛን ያድነን ዘንድ ሰውነቱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ። እንደችግረኛ በችግረኛ ቤት አደረ። ሰማያዊ እርሱ እንደ ባሪያ ራሱን ዝቅ

ዝቅ አደረገ:: ሞቶ የተነሣ እርሱ ብቻ ነው:: የሞትን ፃእረኝነት አጠፋ:: የእርሱን ሕይወት ሰጥቶ ወደ ደስታው አስገባን:: ሲኦልን ረግጦ ሞትን ሽሮ ሕያው ሆኖ ከሙታን መካከል ተነሣ:: (#በግእዝ፦ እምዕቶነ እሳት ዘይነድድ አንገፈነ ብርሃናተ ዘይትዐጸፍ ተንሥአ ለነ:: ብዙኃነ ሙታነ አንሢኦ ቅድመ ውእቱ ተንሥአ በሣልስት ዕለት:: እምዝ ዳግመ ኢይረክቦ ሞት:: ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ ገነዝዎ ለኢየሱስ በሰንዱናት ለዘተንሥአ እሙታን በመንክር ኪን:: ኵልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ እስመ ተንሥአ ክርስቶስ:: ተንሥአ ቤዛነ ሥዒሮ ሞተ ወከዪዶ ሲኦለ:: አሰሰለ ኵሎ ሙስና ዘበምድር:: ተሰቅለ በእንቲኣነ ከመ ኪያነ ያድኅነነ መጠወ ነፍሶ ለሞት:: ኀደረ ቤተ ነዳይ ከመ ምስኪን አትሐተ ርእሶ ከመ ገብር ውእቱ ሰማያዊ:: ውእቱ ባሕቲቱ ዘሞተ ወሐይወ:: ፃእረ ዘሞት ፈትሐ:: ከፈለነ ሕይወተ ዚኣሁ ወአብአነ ውስተ ፍሥሓሁ:: ሥዒሮ ሞተ ወከዪዶ ሲኦለ ሕያዉ ተንሥአ እሙታን)::

**መልካም ሥራ፦** አንደበቱ እንደሚጣፍት ሽቱ የሆነ ዕብራዊ  ጳውሎስ እንደተናገረ የጥንት የኃጢአት እርሾን ከልቡናችሁ አስወግዱ [አንጹ]:: ከጠላት መሳም የወዳጅ መግመስ ይሻላል:: (#በግእዝ፦ በከመ ይቤ ጳውሎስ ዕብራዊ ልሳነ ምዑዝ ዕፍረት እምልብክሙ አንጽሑ ብሑአ ኃጢአት ዘትካት:: ይኄይስ ፍቅሐታተ አርክ እምስዐመተ ጸላዒ)::

## ❤ዘፀአተ ሲኦል❤

**ነገረ ክርስቶስ፦** ሲኦል የተሰጡኝን ነፍሳት ይቀማኛልና ወዮልኝ ወዮልኝ አለች:: ጳጳሳትን፣ ቀሳውስትን፣ ዲያቆናትን፣ ሴቶችንና ወንዶችን ከእጄ ነጥቆ የጻድቃንን ነፍስ አዳነ አለች:: በክርስቶስ ትንሣኤ ሞት ተሸነፈ:: በመምጣቱ ጣዖትን ሻረው ገንዘቡን ሁሉ ዘረፈው:: በብዙዎች ላይ በኵር ይሆን ዘንድ በፈቃዱ ለሕማም የተሰጠ [ጌታ] የጻድቃንን ዘመን ባረከ:: አብ ልጁን ከሙታን መካከል አስነሣው:: በእንጨት መስቀል ላይ ባየችህ ጊዜ ሙሽራህ ቤተክርስቲያን ታመሰግንህለች ከፍ ከፍም ታደርግህለች:: ሰማይን እንደ ባጥ የሰቀለውን አይሁድ በእንጨት መስቀል ሰቀሉት:: ክርስቶስ በራሱ ሥልጣን ከሙታን መካከል ተነሣ:: [ጌታ ሆይ] በእንጨት መስቀል ላይ ትሕትናን አሳየህ:: በትንሣኤህ ጸጋን ገንዘብ አደረግን ሕይወትንም አገኘን:: ከሙታን ሁሉ የቀደምክ [አንተ] ስለእኛ የእኛን የርኩሳንን ምራቅ ታገሥክ:: እግዚአብሔር ወደ ሲኦል ወርዶ እንደ አድማስ ጽኑ የሆኑ መዝጊያ ቁልፎችን ቀጠቀጠ:: እኛን ወዶ በእኛ ፍቅር እስከ ሞት ደረሰ:: የብዙዎች ቤዛ የአዳም አባት [ክርስቶስ] ተነሣ:: ወልድ በሦስተኛው ቀን ተነሣ:: የካህናት አለቃ ክርስቶስ ከጻድቃን ነፍስ ጋር አንድ ያደርገን ዘንድ ከበደለኞች ጋር ተቆጠረ:: በፈቃዱ ታመመ በፈቃዱ ተቀበረ:: በቀራንዮ ተሰቀለ በጎልጎታ ተቀበረ:: ባለመሞት ላይ የሠለጠነውን ገዢ መኳንንት ፈረዱበት:: ራሱን በዘንግ መቱት:: የጻድቃን ማረፊያቸው የሆነ የማይሞት አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞተ:: በመድኀኔ ዓለም ትንሣኤ ለጻድቃን ብርሃን ወጣላቸው:: ሰማያትና ምድር በሚያልፉ ጊዜ አቤቱ በትንሣኤህ አስበኝ:: እርሱ የብዙዎች ቤዛ ሆነ:: ይህም ጨለማውን ያበራው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: (#በግእዝ፦ ትቤ ሲኦል አሌ ሊተ አሌ ሊተ እለ ተውህባኒ ነፍሳተ የሐይደኒዮን ጳጳሳተ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ እደ ወአንስተ እምእዴየ ሔደ ወአግዐዘ ነፍሰ ጻድቃን:: በትንሣኤሁ ለክርስቶስ ተሞዐ ሞት ወበምጽአቱ ሠዐሮ ለጣዖት

ኵሎ ንዋዮ በርበሮ። በፈቃዱ ዘተውህበ ለሕማም ከመ ይኵን በኵረ በላዕለ ብዙኃን ባረከ ዓመተ ጻድቃን። አብ አንሥኦ ለወልዱ እሙታን። ትሴብሐከ ቤተክርስቲያንከ ወታሌዕለከ መርዓትከ ሶበ ትሬእየኪ በዲበ ዕፀ መስቀል። ሰቀልዎ አይሁድ ዲበ ዕፀ መስቀል ለዘውእቱ ሰቀሎ ለሰማይ ከመ ቀመር። ተንሥአ ክርስቶስ እሙታን በዘዚኣሁ ሥልጣን። ትሕትና አርአይከ በዲበ ዕፀ መስቀል ጻጋ ነሣእነ ወረከብነ በትንሣኤከ። ዘዚኣነ ምራቀ ርኩሳን ተዐገሥከ በእንቲኣነ ተንሥኦ ዘቀደምከ እምኵሎሙ ምውታን። ወረደ እግዚአብሔር ውስተ ሲኦል ወቀጥቀጠ ኵሎ መናሥግተ መዓፁተ ዘአድማስ። አፍቂሮ ኪያነ በፍቅረ ዚኣነ በጽሐ እስከ ለሞት። ተንሥአ አቡሁ ለአዳም ቤዛ ብዙኃን። ተንሥአ ወልድ በሣልስት ዕለት። ሊቀ ካህናት ክርስቶስ ተኰለቈ ምስለ ጊጉያን ከመ ይደምረነ ምስለ ነፍሰ ጻድቃን። ሐመ በፈቃዱ ወተቀብረ በሥምረቱ። በቀራንዮ ተሰቅለ ወበጎልጎታ ተቀብረ። ኰነንዎ መኳንንት ለመኰንን ዘሥሉጥ ላዕለ ኢመዊት። ወኰርዕዎ ርእሶ በኅለት። አምላክ ዘኢይመውት ሞተ ምዕራፎሙ ለጻድቃን ዘውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ። በትንሣኤሁ ለመድኀኔዓለም በርሀ ሠረቀ ለጻድቃን። በትንሣኤከ እግዚኦ ተዘከረኒ አመ ይረስና ሰማያተ ወምድር። ውእቱ ኮነ ቤዛ ብዙኃን። ዝኬ ውእቱ ክርስቶስ ማኅቶተ ዘአብርሆ ለጽልመት)።

**መስቀል፦** በክርስቶስ መስቀል ከጠላት ዳንን። [መስቀሉ] የጥል ግድግዳንም አፈረሰ። መስቀል ጠላትን የሚያሸንፍ ብርሃን ነው። (#በግእዝ፦ በመስቀሉ ለክርስቶስ ድኅነ እምፀር ወነሠተ አረፍተ ማእከል እንተ ጽልዕ። መስቀል ብርሃን መዋዔ ፀር)።

**ትርጓሜ፦** የያዕቆብ ቃል የተባለ የወልድ ቃል ነው። በኋላ ዘመን በይስሐቅ የተነገረው በያዕቆብ እጅ የነበረውና ጸጕርህ የኤሳው ነው የሚለው ወልደ እግዚአብሔርን ለሞት አሳልፈው የሰጡት የአይሁድ እጅ ነው። (#በግእዝ፦ ቃልሰኬ ዘያዕቆብ ቃለ ወልድ ውእቱ ዘተነግረ በይስሐቅ በደኃሪ መዋዕል እንዘ ይብል ጸጕርሰኬ ዘኤሳው ዘውስተ እዴሁ ለያዕቆብ እደ አይሁድ ውእቱ እለ አግብዕዎ ለሞት ለወልደ እግዚአብሔር)።

## ዘቶማስ

**ነገረ ክርስቶስ፦** ታላቅ እረኛ ከሙታን መካከል ተነሣ። ቶማስም ጌታዬና አምላኬ አለ። በእጁ ክብር ያለውን ጌታ እንደባሪያ ፈረዱበት። ሞትን ይሽረው ዘንድ ሞተ። የሕይወት መንገድንም ጠረገልን። ከሆዱ የሕይወት ውሃ የሚወጣ የአምላክን የዋሃት፣ ትሕትናና ደግነት እንናገራለን። (#በግእዝ፦ ዐቢይ ኖላዊ ተንሥአ እሙታን። ወይቤ ቶማስ እግዚእየ ወአምላኪየ። ኰነንዎ ከመ ገብር ለዘውስተ እዴሁ ክብር። ሞተ ከመ ይሥዐሮ ለሞት ወጼሐ ለነ ፍኖተ ሕይወት። ንዜኑ ዘአምላክ ኂሩተ ትሕትና ወየዋሀተ። አፍላገ ሕይወት ይውኅዝ እምከርሡ)።

**ትርጓሜ፦** ከይሁዳ ነገድ ከዳዊት ሥር የተገኘ አንበሳ እነሆ አሸነፈ። አንበሳ ያለው የአምላክ ልጅ ነው። (#በግእዝ፦ ናሁ ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ እምነ ሥርወ ለዳዊት። አንበሳ ዘይቤ ወልደ አምላክ)።

## ❤ዘአዳም❤

**ነገረ ክርስቶስ፦** ሰው የሆነ ያ ሰማያዊ [ቃል] አዳም በተሸነፈ ጊዜ ስለአዳም ቀንቶ የእርሱን ሥጋ ለበሰ። በዚህች ሥጋ ይሰቀል ዘንድ። በሰቀሉት ጊዜ ሞት ተሸነፈ ሰይጣን ደነገጠ። እንደ አባታችን አዳም ሁላችንም እንደምንሞት እንዲሁ ስለክርስቶስ ሁላችንም በሕይወት እንኖራለን። ስለአዳም ሞት ተፈጠረ ስለክርስቶስ ደግሞ ትንሣኤ ሆነ። (#በግእዝ፦ ሰማያዊ ዝስኩ ዘምድረ ለብሰ አመ ይትመዋዕ አዳም ቀኒያ በእንተ አዳም ለብሰ ሥጋ ዚኣሁ ከመ በይእቲ ሥጋ ይሰቀል። አመ ይሰቅልዎ ተሞዐ ሞት ወደንገፀ ሰይጣን። በከመ አቡነ አዳም ኵልነ ንመውት ወከማሁ በእንተ ክርስቶስ ኵልነ ነሐዩ። በእንተ አዳም ተፈጥረ ሞት ወበእንተ ክርስቶስ ኮነ ትንሣኤ)።

## ❤ዘአንስት❤

**ቅዱሳት አንስት፦** ሴቶች አደነቁ ትንሣኤውንም ለደቀ መዛሙርቱ ተናገሩ። መግደላዊት ማርያም ከሙታን ከተነሣ በኋላ መድኅን ክርስቶስን አየችው። ኢየሱስን ያገለገሉ ሴቶችም ነበሩ። (#በግእዝ፦ አንስት አንከራ ትንሣኤሁ ወነገራ ለአርዳኢሁ። ማርያም ቅድስት መግደላዊት ርእየቶ ለኢየሱስ መድኅን እምድኅረ ተንሥአ እሙታን። ወሀለዋ አንስትኒ እለ ተልዕካሁ ለኢየሱስ)።

## ❤ዘሰንበት❤

**ነገረ ክርስቶስ፦** ለዓለም ሁሉ መድኀኒት ሆኖ ከኃጢአት ነጻ አወጣን። ሙታንን የሚያስነሣቸው ከሙታን ተነሣ። ከህልውናው አይጎድልም መንግሥቱ አይሻርም። አዲሲቱ ጥጃ የወለደችው የሰባ ፍሪዳ ታረደ። ከአዳም ጎን ሔዋንን የፈጠረ ጌታን አይሁድ በእንጨት መስቀል ላይ ሰቀሉት። (#መድኀኒተ ኮነ ለኵሉ ዓለም ወአግዐዘነ እምኃጢአት። መንሥኤ ሙታን ተንሥአ እሙታን። ኢየሐጽጽ እምህላዌሁ ኢይሠዐር መንግሥቱ። ላሕም መግዝዕ ተጠብሐ ዘወለደት ለነ ሐዳስ ጣዕዋ። ሰቀልዎ አይሁድ ዲበ ዕፀ መስቀል ዘእምገቦሁ ለአዳም ለሐኳ ለሔዋን)።

**ትንሣኤ፦** በዓልን በደስታ፣ በጸሎት፣ መጻሕፍትን በማንበብ እናክብር። ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቷልና ዛሬ ደስታ ሆነችልን። ጥፋት አለፈ ኀዘን ተረሳ። (#በግእዝ፦ ንግበር በዓለ በትፍሥሕት በጸሎት ወበተጸምዶ መጻሕፍት። ዮም ፍሥሓ ኮነት ለነ እስመ ተንሥአ እግዚእነ እሙታን። ኀለፈ ሙስና ተረስዐ ኀዘን)።

## ❤ዘዘወትር❤

**ነገረ ክርስቶስ፦** አይሁድ በአፉ ሐሰት ያልተገኘበትን ኃጢአትን ያልሠራ ጻድቅ ሰው ኢየሱስን ይሰቅሉ ዘንድ ወደዱ። ይሰቅሉት ዘንድ ደነፉ ፊቱን መቱት፣ በቃሉ የሚያድነውን የሁሉ ጌታ የሕይወታቸውን አለቃ መቱት። ይሁዳ አሳልፎ ሰጠው ጲላጦስ ፈረደበት። የሐሰት ምስክር

አቆሙበት። በገመዶች ጎተቱት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በሰቀሉት ጊዜ ምድር ተነዋወጠች፣ ፀሐይ ጨለመ፣ የምኵራብ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀደደ። በመስቀል ተሰቅሎ ሳለ እስኪ ከመስቀል ስትወርድ እንይና በአንተ እንመን እያሉ በመንገድ የሚያልፉ ሰዎች ሰደቡት። ከጥፋት መሸሻ የሆንከን [ክርስቶስ ሆይ] ወደ ሕይወት መንገድ መራሕን። የካህናት አለቆች ተሳለቁበት። የጽድቅ ሰማይ የሃይማኖት ሰማይ የእውነት መንፈስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከኤዶም የወጣውና መልካም የሥጋ ልብስን የለበሰ ጎበዝ ሞት ሊይዘው የማይችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከባድ የሆነ የኃጢአትን ሸክም ከእኛ ላይ ያስወግድ ዘንድ ሕመማችንን ተሸከመ። የቀድሞ በደላችንን ሳያስብ ሞትን አሸነፈው። (#በግእዝ፦ ፈቀዱ አይሁድ ኢየሱስሀ ይስቅሉ ብእሴ ጻድቀ ዘኢገብረ ኃጢአተ ወኢተረክበ ሐሰት ውስተ አፋሁ። ይስቅልዎ ወውዑ መላትሒሁ ጸፍዑ መልአከ ሕይወቶሙ ጸፍዑ እግዚአ ኵሉ ዘያሐዩ በቃሉ። ይሁዳ አግብዖ ጲላጦስ ኰነኖ። ወአቀሙ ሎቱ ሰማዕተ ሐሰት። ሰሐብዎ በአሕባል። አመ ይሰቅልዎ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ምድር አድለቅለቀት ወፀሐይ ጸልመ ወመንጦላዕተ ምኵራብ ተሰጠ እምላዕሉ እስከ ታሕቱ። ጸረፉ ላዕሌሁ ኅለፍተ ፍኖት እንዘ እግዚእ ስቁል ዲበ ዕፀ መስቀል ወይቤልዎ ረድ እስኩ እመስቀልከ ንርአይ ወንእመን ብከ። [ክርስቶስ] መራሕከነ ፍኖተ ሕይወት እሙስና ዘኮንከነ ምጕያየ። ተሣለቅዎ ሊቃነ ካህናት። ጠፈረ ጽድቅ ጠፈረ ሃይማኖት መንፈስ ቅዱስ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ። መካሕ ዘይወፅእ እምኤዶም ዘይትዐጸፍ ሠናየ አልባሰ ዘባሶር ዝኬ ውእቱ ክርስቶስ ዘኢይክል እኂዞቶ ሞት። ፆረ ሕማመነ ከመ ያሰስል ፆረ ኃጢአት ክቡደ እምላዕሌነ። ኢተዘኪሮ አበሳነ ዘትካት ሞዖ ለሞት)።

**ትርጓሜ፦** በነቢይ ከሙታን ነጻ የወጣ ነው አለ። ነጻ የወጣ ማለት ሞት አያገኘውም ማለት ነው። በፈቃዱ ወደ ሲኦል ወርዶ በሦስተኛው ቀን ተነሣ እርሱን ሞት መያዝ አይችልምና። ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ። የሞት መውጊያው ኃጢአት ነው። (#በግእዝ፦ ይቤ በነቢይ ግዑዝ ውስተ ሙታን። ግዑዝ ብሂል እስመ ኢይረክቦ ሞት አላ በፈቃዱ ወሪዶ ውስተ ሲኦል ተንሥአ በሣልስት ዕለት እስመ ኢይክል እኂዞቶ ሞት። አይቴ ሀሎ ቀንዖትከ ሞት ወቀኖቱሰ ለሞት ኃጢአት ውእቱ)።

**ነገረ ቅዱሳን፦** በመጀመሪያ ሐዋርያትን ዳግመኛ ነቢያትን ሦስተኛ ሊቃውንት ለቤተክርስቲያን ጆሮ አድርጎ ሰጠን። (#በግእዝ፦ ወሀበ እዝነ ለቤተክርስቲያን በቀዳሚ ዘሐዋርያት ወበዳግም ዘነቢያት ወበሣልስ ዘሊቃውንት)።

## ❢ሚያዝያ 23 ዘጊዮርጊስ❢

**ቅዱስ ጊዮርጊስ፦** ጊዮርጊስ የሰማዕታት አለቃ ነው። ጌታችን ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ወርዶ ከተኛህበት ተነሥ አለው። ጊዮርጊስ የሚጋደል ኀያል ነው። ከሰማይ የእኔ ወዳጅ የተመረጥክ ጊዮርጊስ ሆይ ጨክን የሚል ቃል ወረደ። አባ ጊዮርጊስ ገድሉን በትዕግሥት የፈጸመ ነው። አንዲት መበለት ሴት ቅዱስ ጊዮርጊስን መልካም ገድልን ተጋደልክ አለችው። የቤቴን ምሰሶ ያለመለምክ ጊዮርጊስ ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን አለችው። በሥላሴ ኀይል ሰይጣንን አሸነፈው።

የፋርስ ኮከብ የልዳ ፀሐይ የሆነ ንዑድ ክቡር ጊዮርጊስን እንደ ነፋስ ትቢያ በይድራስ ተራራ በተኑት፡፡ ወደ ደረቀ ጉድጓድም ጣሉት፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ መንኰራኩርን በተመለከተ ጊዜ በመሞት ለመመስከር ጮኸ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ አንገቱ በተቆረጠ ጊዜ ደም ውሃና ወተት ከአንገቱ መነጨ፡፡ ስለክርስቶስ ፍቅር መልካም ገድልን የተጋደለ ጊዮርጊስ ንዑድ ክቡር ነው፡፡ ሥልጣን ተሰጠው ምድርን ረግጦ ሙታንን አስነሣ፡፡ አንዲት መበለት ሴት ቅዱስ ጊዮርጊስን የክርስቲያኖች አምላክ ሰው መስሎ ወደ እኔ መጣ አለችው፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስም እኔስ የአምላክ አገልጋይ ነኝ እንጂ አምላክ አይደለሁም አላት፡፡ (#በግእዝ፦ ጊዮርጊስ መክብበ ሰማዕታት፡፡ ወረደ እግዚእነ ኀበ ቅዱስ ጊዮርጊስ ወይቤሎ ተንሥእ እምንዋምከ ዘዚኣየ ሐራ መስተጋድል፡፡ ጊዮርጊስ ኀያል መስተጋድል፡፡ ወረደ ቃል እምሰማይ ዘይብል ጥባዕኬ ዘዚኣየ ፍቁር ኅሩይ መስተጋድል ጊዮርጊስ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር፡፡ አባ ጊዮርጊስ በትዕግሥቱ ዘፈጸመ ገድሎ፡፡ ትቤሎ ብእሲት መበለት ለብፁዕ ወለቅዱስ ጊዮርጊስ ሠናየ ገድለ ተጋደልከ ዐምደ ቤትየ ዘአቀጻልከ ሰላም ለከ ጊዮርጊስ፡፡ በኀይለ አጥናን ዘሞፆ ለሰይጣን፡፡ ከመ ጸበል ዘነፋስ ዘረውዎ ደብረ ይድራስ ወወገርዎ ውስተ አዘቅት ይቡስ ለብፁዕ ወለቅዱስ ጊዮርጊስ አማን ፀሐየ ልዳ ኮከበ ፋርስ፡፡ መንገነ ሶበ ነጸረ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለስምዐ መዊት ጥሕረ፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሶበ ተከለለ ደም ወማይ ወሐሊብ እምነ ክሣዱ ፈልፈለ፡፡ ብፁዕ ጊዮርጊስ ዘተጋደለ ሠናየ ገድለ በእንተ ፍቅረ ክርስቶስ፡፡ ተውህበ ሎቱ ሥልጣን ረገጸ ምድረ አንሥአ ሙታነ፡፡ ትቤሎ ብእሲት መበለት ለብፁዕ ወለቅዱስ ጊዮርጊስ አምላኮሙ ለክርስቲያን ተመሲሎ ሰብአ መጽአ ኀቤየ ወይቤላ ቅዱስ ጊዮርጊስ አንሰ ኢኮንኩ አምላከ አላ ገብረ አምላክ አነ)፡፡

## ❤ዘርክበ ካህናት❤

**ነገረ ክርስቶስ፦** አምላክ ሲሆን ዲያቆን ሆነ ንፍ*ቀ ዲያቆንም ሆነ፡፡ የደቀ መዛሙርቱን እግርም አጠበ፡፡ የመድኃኒታችንን የትንሣኤውን መታሰቢያ እናድርግ፡፡ ሰማይን በከዋክብት ያስጌጠ የእሾህ አክሊልን ተቀዳጀ፡፡ ሰማይን በደመና ያስታጠቀው መታጠቂያን ታጥቆ የደቀመዛሙርቱን እግር አጠበ፡፡ (#በግእዝ፦ እንዘ አምላክ ውእቱ ኮነ ዲያቆነ ወኮነ ን*ፍቀ ዲያቆን ወሐፀበ እግረ አርዳኢሁ፡፡ ንግበር ተዝካረ ትንሣኤሁ ለመድኀኒነ፡፡ ዘከለሎ ለሰማይ በከዋክብት አክሊለ ዘሦክ ተቀጸለ፡፡ ዘአቅነቶ ለሰማይ በደመና ቀነተ ለንጻ ወሐጸበ እግረ አርዳኢሁ)፡፡

**ጻድቃን፦** ጻድቃን ማኅበራችንን በሰላም ጠብቅልን ብለው ጮሁ፡፡ የዓለም ብርሃን ቅዱሳን ሕዝብ ናችሁ፡፡ (#በግእዝ፦ ጸርሑ ጻድቃን እንዘ ይብሉ ማኅበረነ ባርክ ዕቀብ በሰላም፡፡ ሕዝብ ቅዱሳን አንትሙ ብርሃኑ ለዓለም)፡፡

## ❖ሚያዝያ 30 ዘማርቆስ❖

**ቅዱስ ማርቆስ፦** የእግዚአብሔር ሰው፣ ወንጌላዊ፣ ሐዋርያና ሰማዕት የሆነ የከበረ ማርቆስ የወልደ እግዚአብሔርን ትንሣኤውን ሰበከ፡፡ (#በግእዝ፦ ማርቆስ ክቡር ወንጌላዊ ብእሴ እግዚአብሔር ሐዋርያ ወሰማዕት ሰበከ ትንሣኤሁ ለወልደ እግዚአብሔር)፡፡

## 💔ግንቦት 1 ዘማርያም💔

**ነገረ ማርያም፦** እመቤታችን ማርያም ምግባሯ መልካም አንደበቷ ጥዑም ነው። ማርያም የገነት እንኮይ ናት። ሙሴ በደብረ ሲና ያያት የለመለመች ዕፅ ናት። የመና ሙዳዩ ናት። (#በግእዝ፦ ጥዕምት በቃላ ወሠናይት በምግባራ እግዝእትነ ማርያም። ማርያም ዘገነት ኮል። ሐመልማላዊት ዕፅ ሙሴ ዘርእያ በደብረ ሲና እግዝእትየ ሙዳዩ ለመና)።

## 💖ግንቦት 8 ዘዕርገት💖

**ነገረ ክርስቶስ፦** ኃጢአት የሌለበት ኃጢአታችንን ነሣ። ወልድ በምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ። (#በግእዝ፦ ኃጢአተነ ነሥአ ዘአልቦ ኃጢአት። ዐርገ ወልድ በስብሐት ውስተ ሰማያት)።

## 💗ግንቦት 11 ዘያሬድ💗

**ቅዱስ ያሬድ፦** ፀሐይዋ ካህኑ ያሬድ ኢትዮጵያን በምስጋና አስጌጣት። ከእርሱ በፊትም ከእርሱ በኋላም እንደ እርሱ ያለ ማሕሌታይ የለም። የእንስሳት፣ የሰው የአራዊት [ድምፅ] ከያሬድ ከሦስቱ ዜማዎች አያልፉም። (#በግእዝ፦ አሠርገዋ ለኢትዮጵያ በስብሐት ወሃሌ ሉያ ያሬድ ካህን ፀሐያ። አልቦ እምቅድሜሁ ወአልቦ ድኅሬሁ ማሕሌታይ ሰብእ ዘከማሁ። እንስሳ ወሰብእ ወአራዊት ኢየዐድዉ እምነ ሠላስ ዜማሁ ለያሬድ ካህን)።

## 💝ግንቦት 24 ዘበአተ ግብጽ💝

**ትርጓሜ፦** እነሆ እግዚአብሔር በቀላል ደመና ተጭኖ ወደ ግብጽ ምድር ይመጣል። ደመና ያላት አማኑኤልን በጀርባዋ ያዘለችው ድንግል ማርያም ናት። (#በግእዝ፦ ናሁ ይመጽእ እግዚአብሔር ውስተ ምድረ ግብጽ ተጽዒኖ ዲበ ደመና ቀሊል። ደመናሰ ዘይቤ ይእቲኬ ድንግል ዘሐዘለቶ በዘባና ለአማኑኤል)።

**ነገረ ክርስቶስ፦** ጣዖታትን ይሽር ዘንድ የጣዖት ቅርጾችን ሁሉ ያፈርስ ዘንድ ወደ ግብጽ ገባ። (#በግእዝ፦ ብሔረ ግብጽ ቦአ ይሥዐር ጣዖተ ወይንሥት ኵሎ ግልፍዋተ)።

## †ዘጳራቅሊጦስ†

**ነገረ ሥላሴ፦** ሃይማኖት ከአብ ተፈጠራ ወደ ወልድ ታደርሳለች በመንፈስ ቅዱስ ትፈጸማለች። በአብ የምናምን የወልደ እግዚአብሔርን ሕማሙን እናምናለን (#በግእዝ፦ ሃይማኖት እንተ እምኀበ አብ ተፈጥረት ኀበ ወልድ ታበጽሕ ኀበ መንፈስ ቅዱስ ትትፌጸም። እለሰ ነአምን በአብ ነአምን ሕማሞ ለዘኢየሐምም)።

## 💟ዘክብረ ቅዱሳን💟

**ነገረ ክርስቶስ፦** ጌታ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ በመንገድ የሚያልፉ ሰዎች እስኪ ከመስቀልህ ውረድ እንይህና እንመንብህ አሉት። ጌታም ሸክላ ሸክላ ሠሪን ይጠይቅ ዘንድ ታዝዟልን አላቸው። (#በግእዝ፦ ጸረፉ ላዕሌሁ ኀለፍተ ፍኖት እንዘ እግዚእ ስቁል ዲበ ዕፀ መስቀል ወይቤልዎ ረድ እስኩ እመስቀልከ ንርአይ ወንእመን ብከ አውሥኦሙ ወይቤሎሙ እዙዝኑ ይግበር ልሕኩት ዲበ ለሐኩሁ)።

## ፠ዘሰንበት፠

**ነገረ ክርስቶስ፦** የጌታችን ልብሱ የእሳት ዙፋኑ የሐር እሳትን የተጎናጸፈ ነው። የአብ የመጀመሪያ ፍጥረት ሞትን አሸንፎ በዕለተ ሰንበት ተነሣ። ለፍጥረት ሁሉ ሰላምን አደረገ። ያላወረደውን አሳረገ። ዓለምን ያድን ዘንድ የእውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስን አወረደ። ሥርዓትን ሁሉ ፈጽሞ ወደ አባቱ ወደ ሰማያት ዐረገ። (#በግእዝ፦ ልብሱ ዘእሳት ለእግዚእነ መንበሩ ዘሜላት ወይትአጸፍ ነደ እሳት። ቀዳሜ ተግባሩ ለአብ ሞዖ ለሞት ወተንሥአ በዕለተ ሰንበት ገብረ ሰላመ ለኵሉ ፍጥረት። ዘኢያውረደ አዕረገ መንፈሰ ጽድቅ ጰራቅሊጦስሀ አውረደ ከመ ይቤዙ ኵሎ ዓለመ። ወፈጺሞ ኵሎ ሥርዐተ ኀበ አቡሁ ዐርገ ሰማያተ)።

## ዘዘወትር

**ነገረ ክርስቶስ፦** ያላወረደውን ሥጋን ነሥቶ ወደ ሰማይ ዐረገ። ስቀለው ስቀለው ያሉት የት አሉ? ወደ ሰማይ ያረገውን ክርስቶስን መጥተው ይዩአ። በኵሩን ወደ ዓለም በላከው ጊዜ ለሰማይ አልነገረውም ከመላእክቶቹ ጋርም አልተማከረም። ክርስቶስ ማለት በትርጓሜው የእግዚአብሔር ልጅ ማለት ነው። በታላቅ ምስጋና ወደ ሰማይ ያረገውን ቤተክርስቲያን ታመሰግነዋለች። (#በግእዝ፦ ነሢኦ ሥጋ ዘኢያውረደ አዕረገ ውስተ ሰማይ። አይቴ ሀለዉ እለ ይቤሉ ስቅልዎ ስቅልዎ ይምጽኡኬ ይርአዩ ኀይሎ ለክርስቶስ ለዘዐርገ ውስተ ሰማያት። አመ ይፌንዎ ለበኵሩ ውስተ ዓለም ኢዜነዎ ለሰማይ ወኢተማከረ ምስለ መላእክቲሁ። ክርስቶስ ብሂል ወልደ እግዚአብሔር ብሂል በትርጓሜሁ። ትዌድሶ ቤተክርስቲያን ለዘዐርገ ውስተ ሰማያት በዐቢይ ስብሐት)።

## ❧ሰኔ 11 ዘገላውዴዎስ❧

**ገላውዴዎስ፦** እግዚአብሔር ለገላውዴዎስ በምድር ላይ መንግሥትንና ጠላትን ማሸነፍን ሰጠው። መንገዱ እውነት ነው በጽድቁም ትክክለኛ ነው። ከሰው ቸር ገላውዴዎስን የሚመስል የለም። ተድባበ ማርያምን የመሠረታት ገላውዴዎስ ሲሆን ሕንፃዋን የፈጸመ ደግሞ ሠርፀ ድንግል ነው። (#በግእዝ፦ መንግሥተ ዘበምድር ወመዊዐ ላዕለ ፀር ለገላውዴዎስ ወሀቦ እግዚአብሔር። ጽድቅ ውእቱ ፍናዊሁ ወርቱዕ በጽድቁ ለገላውዴዎስ ኄር አልቦ እምሰብእ ዘከማሁ። ለተድባበ ድንግል ማርያም ገላውዴዎስ ኮነ ሣራሪሃ ወሠርፀ ድንግል ፈጸመ ሕንፄሃ)።

## 🌹ሰኔ 12 ዘሚካኤል🌹

**ነገረ ክርስቶስ፦** በዕርገቱ መላእክት ሁላቸው ደስ ተሰኙ:: ሞገስን የተሞላ፣ በጸጋ በሃይማኖትና በጽድቅ ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ሚካኤል መለከትን እየነፋ፣ መላእክት በብዙ ምስጋና እያመሰገኑት ወልድ ወደ ታላቅ ዙፋኑ ከፍ ከፍ አለ:: የሚካኤል ጌታ ኀሊና ወደማይደርስበት በደመና ዐረገ:: ወልድ ወደ ዙፋኑ ሲያርግ በሰማይ ታላቅ ዜማ የመላእክት ዝማሬ ተሰማ:: ሁሉም መላእክት በትንሣኤው አመሰገኑ:: የሚካኤል ጌታው የነቢያትን ትንቢት ሁሉ ፈጽሞ ወደ ሰማይ ዐረገ:: የሚካኤል ጌታው ከአባቱ ዘንድ መጥቶ ምርኮን ማርኮ ጠላቱንም አሸንፎ በመልካም ምስጋና በመለከት ድምፅ ከፍ ብሎ ወደ ሀገሩ ገባ:: ሙታንን የሚያስነሣቸው ተነሣ:: (#በግእዝ፦ በዕርገቱ ተፈሥሑ ኵሎሙ መላእክት:: ምሉአ ሞገስ ፍጹመ ጸጋ ወጽድቅ ወሃይማኖት ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሐር:: ሚካኤል ቀርነ እንዘ ይነፍህ ተለዐለ ወልድ ዲበ መንበሩ ነዋኀ እንዘ ይሴብሕዎ መላእክት በስብሐት ብዙኀ:: ኀበ ዘኢይክል በጺሐ ኀሊና እግዚኡ ለሚካኤል ዐርገ በደመና:: ዐቢይ ዜማ ተሰምዐ በሰማይ ዘመላእክት ግናይ እንዘ የዐርግ ወልድ ውስተ መንበሩ:: ኵሎሙ መላእክት ትንሣኤሁ ዘመሩ:: እግዚኡ ለሚካኤል ዐርገ አርያሞ ትንቢተ ነቢያት ኵሎ ፈጺሞ:: እግዚአ ሚካኤል ፀሮ አግሪሮ እምኀበ አቡሁ ዔዋ በርቢሮ ውስተ ሀገሩ ቦአ ሠሪሮ በንፍሐተ ቀርን በሐዋዝ ዘምሮ:: መንሥኤሆሙ ለሙታን ተንሥአ)::

**ቅዱስ ሚካኤል፦** ሚካኤልን በፍጥረታት ላይ ሁሉ ሾመው:: ሚካኤልና ገብርኤል ሱራፌልና ኪሩቤል ለእግዚአብሔር በሰማይ ምስጋና ይሁን በምድርም ሰውን ለወደደ ለእርሱ ምስጋና ይሁን እያሉ አመሰገኑ:: የመላእክት አለቃ ሚካኤል መለከትን በነፋ ጊዜ ሙታን ይነሣሉ:: (#በግእዝ፦ ሤሞ ለሚካኤል ላዕለ ኵሉ ፍጥረት:: ሚካኤል ወገብርኤል ሱራፌል ወኪሩቤል ይሴብሕዎ እንዘ ይብሉ ስብሐት ለእግዚአብሐር በሰማያት ወሰላም በምድር ለዘሠምሮ ለሰብእ:: ወሚካኤል ሊቀ መላእክት አመ ይነፍሕ ቀርነ ይትነሥኡ ሙታን)::

## ✿ሰኔ 17 ዘገሪማ✿

**አባ ገሪማ፦** አባ ገሪማ በግርማ የከበረ ነው:: አባ ገሪማ በድካም ፍጹም የሆነ ነው:: ቅድስት የሆነች ጸሎትህ ትቀድሰኝ ቀጥ ያለች ሃይማኖትህ ትባርከኝ:: እንደ ምታበራ ጨረቃ እንደ ብሩህ ኮከብ በጸሎትህ ሰይጣንን አሸነፍከው:: አባ ገሪማ ጠዋት በጥበቡ ይዘራል በሠርክ ከእርሻው ይሰበስባል:: የመደራ ቄስ አባ ገሪማ ሆይ ሰውነቴ በፊትህ ትክበር:: (#በግእዝ፦ አባ ገሪማ ዘክሉል በግርማ አባ ገሪማ ዘፍጹም በፃማ ጸሎትከ ቅድስት ትቀድሰኒ ሃይማኖትከ ርትዕት ትባርከኒ:: ከመ ወርኅ ንጹሕ ወከመ ኮከብ ብሩህ በጸሎትከ ሞዕኮ ለሰይጣን:: አባ ገሪማ በጸሎቱ ነግሀ ይዘርዕ ኪነቶ ወሠርከ የዐርር ገራህቶ:: አባ ገሪማ ቀስ ዘመደራ ትክበር ነፍስየ በቅድሜከ)::

## 💐ሐምሌ 5 ዘጴጥሮስ ወጳውሎስ💐

**ጴጥሮስ ወጳውሎስ፦** በሕይወታቸው ጌታቸውን ያስደሰቱ ጴጥሮስና ጳውሎስ ክብር ይገባቸዋል። በጴጥሮስ ጥላ ብዙ ሕመምተኞች ይድኑ ነበር። በልብሱ ጫፍና በጥምጥሙም ይድኑ ነበር። ጴጥሮስና ጳውሎስ በቀና ሃይማኖታቸውና በጸሎታቸው ሕመምተኞችን ፈወሱ። (#በግእዝ፦ ጴጥሮስ ወጳውሎስ በሕይወቶሙ እለ አሥመርዎ ለእግዚአሙ ክብር ይደልዎሙ። በጽላሎቱ ለጴጥሮስ የሐይዉ ኵሎሙ ብዙኃን ዱያን ወበጽንፈ ልብሱ ወሰበኑ የሐይዉ። ጴጥሮስ ወጳውሎስ በጸሎቶሙ ወበርትዕት ሃይማኖቶሙ ፈወሱ ዱያነ)።

## ⚘ዘሐዋርያት⚘

**ነገረ ክርስቶስ፦** የጽድቅ ፍጻሜው የዘለዓለም ሕይወት በሆነው በክርስቶስ ማመን ነው። እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል። (#በግእዝ፦ ወማኅለቅቱሰ ለጽድቅ አሚን በክርስቶስ ሕይወት ዘለዓለም። ዘእግዚአብሔር ፈነዎ ቃለ እግዚአብሔር ይነግር)።

## ❁ዘዘወትር❁

**ሐዋርያት፦** ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አጋንንትን አውጡ ለምጻሞችን አንጹ ስጦታን ተቀብላችሁ እናንተም በስጦታ ስጡ [ገንዘብ አታስከፍሉ] አላቸው። [አቤቱ] መልካም ዜናን ለሚናገሩ እግሮቻቸውን ቀልጣፋ አድርግ። የቤተክርስቲያን ምሰሶዎች የምድር ዓይኖች ሆይ ሐዋርያት ትባላላችሁ። የሐዋርያት አኗኗር ትእዛዝን እየጠበቁ በጥንቃቄ ነበር። የክፉዎችን እሾህ እያስወገዱ የዘለዓለም የሕይወት ቃልን ዘሩ። የሚያልፈውን ዓለም ቸል አሉ። ሐዋርያት ክርስቶስን መሰሉት። ዓለም እኔን መጥላትን እንደቀደመ እወቁ ሲል ሰምተውታልና። እናንተ የምድር ጨው ናችሁ። (#በግእዝ፦ ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ አጋንንተ አውፅኡ እለ ለምጽ አንጽሑ ጸጋ ነሢአክሙ በጸጋ ሀቡ። ከዋው እገሪሆሙ ለእለ ይዜንዉ ዜና ሠናየ። ሐዋርያተ ትሰመዩ አዕይንታተ ምድር አዕማደ ቤተክርስቲያን። ሕይወቶሙ ለሐዋርያት በኵሉ ጥንቃቄ እንዘ የዐቅቡ ትእዛዘ። እንዘ ያነጽሑ አሥዋከ ረሲዓን ቃለ ሕይወት ዘለዓለም ዘርኡ። ይትኄየዩ ኀላፌ ዓለመ። ሐዋርያት ተመሰልዎ ለክርስቶስ እስመ ይሰምዕዎ እንዘ ይብል አእምሩ ከመ ኪያየ ቀደመ ጸሊዐ ዓለም። አንትሙ ፄዉ ለምድር)።

## ❖ሐምሌ 7 ዘሥላሴ❖

**ቅድስት ሥላሴ፦** ከዓለም በፊት በነበረ በአንድ እግዚአብሔር እያመንን እንገዛለን። አብን ለሚመስለው በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። ምእመናን ሆይ የሥላሴን ምሕረቱንና መልካም ሥራውን ተናገሩ። በሥላሴ እናምናለን። ለሥላሴ እንሰግዳለን። ፈጥሮናልና ሥላሴን እናመሰግናለን። አምላኮቻችን ሥላሴ ሆይ የሙሴ ምስጋና መሥዋታችሁን እነሆ [እናቀርባለን]። የሥላሴ መንግሥት በእውነት ለዘለዓለም ነው። ወልድ ወደ አባቱ አቀረበን ወደ መንፈሱም አደረሰን። ሥላሴ ፈጽማ ትደነቃለች። ሁሉ ለሥላሴ ይሰግዳል። ሁሉም ለሥላሴ መንግሥት ይገዛል። የማይነዋወጥ አምላክ በአንድነት በሦስትነት ጸንቶ ይኖራል። (#በግእዝ፦ ነአምን ወናመልክ በአሐዱ

እግዚአብሔር ዘእምቅድመ ዓለም ሀሎ ወነአምን በካልዑ እግዚአብሔር ዘበምልክናሁ ለአብ ይመስሎ ወነአምን በሣልሱ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ዘይመልክ ኵሎ:: ንግሩ ምሕረቶ ለሥላሴ ወዜንዉ ሠናይቶ መሃይምናን:: ነአምን በሥላሴ ወንሰግድ ለሥላሴ ወንዜምር ለሥላሴ እስመ ፈጠረነ:: ነዋ መሥዋዕቲክሙ ስብሐተ ሙሴ አማልክቲነ ሥላሴ:: አማን መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም:: ኀበ አቡሁ አቅረበነ ወልድ ወኀበ መንፈሱ አብጽሐ ኪያነ:: ሥላሴ ትትረመም ወትትነከር:: ኵሉ ይሰግድ ለሥላሴ ወይትቀነይ ኵሉ ለመንግሥተ ሥላሴ:: ይሄሉ በሥላሴ ወበዋሕድናሁ ዘኢያንቀለቅል አምላክ)::

**ነገረ ክርስቶስ፦** እኛ የሥላሴ ቤተሰቦች የሙሴን መና አንመኘውም:: ምግባችን የሚቀድስ ተናጋሪ ነውና:: (#በግእዝ፦ እስመ ሲሳይነ ነባቢ ቀዳሲ ኢንትሜነዮ ለመና ሙሴ ሰብአ ቤቶሙ ለሥላሴ)::

## ✿ሐምሌ 8 ዘብሶይ✿

**አባ ብሶይ፦** ንዑድ ክቡር አባ ብሶይ በመልካም ሥራ ያጌጠ እንደ ወርቅ ጽዋዕ የጠራ ነው:: ዋጋውን በሰማይ አዳራሽ ይቀበላል [ተቀብሏል]:: (#በግእዝ፦ ብፁዕ አባ ብሶይ ሥርግው በምግባረ ሠናይ ከመ ጽዋዐ ወርቅ ጽሩይ ይነሥእ ዕሴቶ በታዕካ ሰማይ)::

## ❁ሐምሌ 19 ዘቂርቆስ❁

**ቅዱስ ቂርቆስ፦** የአንጌቤን ሰው ሕፃን ቂርቆስ የአንጌቤናዊት ሴት [የኢየሉጣ] ልጅ ነው:: ሕፃኑን ስምህ ማን ነው? አሉት:: እርሱም የሕይወት ውሃ ምንጭ ክርስቲያን ነኝ ያጠመቀኝ ካህን ቂርቆስ ብሎኛል አላቸው:: ሕፃንና እናቱ ሁለታቸው ገድላቸውን ፈጸሙ:: ቂርቆስና እናቱ በጽናትና በትዕግሥት በኀይልና በሥልጣን ሰይጣንን አሸነፉት:: የሀገር ገዢው ኢየሉጣን ያዛት:: ለአማልክቶቹ እንድትሠዋም አዘዛት:: ሕፃን ቂርቆስም በጎልማሳ መንፈስ ለእናቱ ከስሕተት መዳኛ ሆናት:: [ቂርቆስን] አናቱን ከቆዳው ጋር ላጩት:: ሕፃኑ ፍሕምን አልፈራም የሚያስፈራ ነበልባልም አላስደነገጠውም:: ጌታው ለሕፃኑ ከእኔ ከፈጣሪህና ከዮሐንስ መጥምቅ በስተቀር በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥህ የለም:: ሥጋህም እንዳይጠፋ በኤልያስ ሠረገላ በዚያ አኖርሀለሁ አለው:: እናቱ ኢየሉጣ ቂርቆስን ወደ መንግሥተ ሰማያት መሪ የሆንከኝ ልጄ ሆይ ኑርልኝ አለችው:: (#በግእዝ፦ ቂርቆስ ሕፃን አንጌቤናይ ወልደ አንጌቤናዊት:: ይቤልዎ ለሕፃን መኑ ስምከ ወይቤሎሙ ነቅዐ ማየ ሕይወት ክርስቲያናዊ አነ ካህን ዘአጥመቀኒ ቂርቆስ ሰመየኒ:: ሕፃን ወእሙ ክልኤሆሙ ፈጸሙ ገድሎሙ:: በጽንዕ ወበትዕግሥት በኀይል ወበሥልጣን ምዕዎ ለሰይጣን ቂርቆስ ወእሙ:: ለኢየሉጣ መኰንን አኀዛ ለአማልክቲሁ ትሡዕ አዘዛ ቂርቆስ ሕፃን በመንፈሰ ወሬዛ ኮና ለእሙ እምስሕተት ቤዛ:: ላጸይዎ ድማሑ ዘምስለ ማዕሱ:: ኢፈርሆ ሕፃን ለውእቱ ፍሕም ወኢያደንገጾ ነበልባል ግሩም:: ይቤሎ እግዚኡ ለሕፃን አልቦ ዘየዐብየከ በመንግሥተ ሰማያት ዘእንበለ ዮሐንስ መጥምቅ ወአነ ፈጣሪከ ወዓዲ ከመ

ኢይማስን ሥጋከ ዲበ ሠረገላ ኤልያስ ህየ አነብረከ። ትቤሎ እሙ ኢየሉጣ ለቂርቆስ ሕየወኒ ወልድየ ዘኮንከኒ መርሐ ለመንግሥተ ሰማያት)።

**ቅድስት ኢየሉጣ፦** ኢየሉጣ የጽጌረዳ ምንጭ የሆነ ቂርቆስን ወለደች። የጽድቅ ፀሐይ ይከባታል። (#በግእዝ፦ ኢየሉጣ ወለደት ነቅዐ ጽጌረዳ ፀሐየ ጽድቅ የዐውዳ)።

## ☁ሐምሌ 21 በጸሎተ ሚካኤል☁

**አባ በጸሎተ ሚካኤል፦** አባታችን በጸሎተ ሚካኤል ሆይ እንደ አብርሃም እንግዳ ሆንክ። እንደ ኤልያስ ድንግል ሆንክ። እንደ ሰማዕታት ተጋደልክ። የሁሉን [መልካም] ጠባይ ተከተልክ። ድንግልና ሰማዕት የሆነ በጸሎተ ሚካኤል አፉን በጾምና በጸሎት ዘጋ። ጉልበቱን በቁመትና በስግደት አደከመ። (#በግእዝ፦ ከመ አብርሃም ተአንገድከ ወከመ ኤልያስ ተደንገልከ ወከመ ሰማዕታት ተጋደልከ በጸሎተ ሚካኤል አቡነ በግዕዘ ኵሉ ተለውከ። አፉሁ ለጎመ በጾም ወበጸሎት አብራኮ አድከመ በቀዊም ወበስግደት በጸሎተ ሚካኤል ድንግል ወሰማዕት)።

**ነገረ ማርያም፦** የነቢያት አለቃ በሲና ያያት መና ያለባት የወርቅ መሶብ ደም ግባቷ [ውበቷ] መልካም ነው። (በግእዝ፦ አዳም ሥና መሶበ ወርቅ ዘመና ሊቀ ነቢያት ዘርእያ በሲና)።

## ●ሐምሌ 27 ዘሰላማ●

**አባ ሰላማ፦** ለምድራችን ብርሃን የሆንክ ታላቅ ጳጳስ አባ ሰላማ ስለእኛ ጸልይልን። [አባ ሰላማ] ወደ ሀገራችን የተላከ ሐዋርያና ለእኛ ሰማዕት የሆነልን ነው። [አባ ሰላማ ሆይ] ክርስቶስ ሃይማኖትን ታቀና ዘንድ ሾመህ። ቸር ሰው በምድር ያለ ተድላ ደስታን ያልመረጠ ይህ ክቡር አባ ሰላማ ነው። የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ይህ ሰው የሰማዕታት አለቃቸው ነው። (#በግእዝ፦ አባ ሰላማ ዐቢይ ጳጳስ ብርሃነ ዘኮንከ ለምድርነ ሰአል ወጸሊ በእንቲኣነ። ሐዋርያ ዘተፈነወ ውስተ ምድርነ ወሰማዕት ኮነ ለነ። ሜመከ ክርስቶስ ታስተራትዕ ሃይማኖተ። ብእሲ ኄር ወመምህር ዘኢያብደረ ሐውዘ ዘበምድር ዝንቱ ውእቱ አባ ሰላማ ክቡር። ዝንቱሰ ብእሲ ብእሴ እግዚአብሔር መክብቦሙ ለሰማዕት)።

## 🍎ነሐሴ 1 ዘደናግል🍎

**ደናግል፦** ሰነፎች ተኙ ብልሆች ግን ነቅተው ሙሽራውን ይቀበሉ ዘንድ ሄዱ። [ብልሆች] በታላቅ ደስታ ወደ ሠርጉ ወደ ሙሽራው አዳራሽ ከሙሽራው ጋር ይገቡ ዘንድ የዚህን ዓለም ጥበብ አቃልለው በትዕግሥትና በመልካም አምልኮ የሕያዋን ምድርን ወረሱ። ቅዱሳት ሴቶች ራሳቸውን በመልካም ሥራ አስጊጠው ኢየሱስ ክርስቶስን ተከተሉ። የጻድቃን ነፍሳት ደናግል ይባላሉ። (#በግእዝ፦ አብዳት ኖማ ጠባባት ነቅሓ ወሖራ ከመ ይትቀበላ መርዓዌ። በሠናይ አምልኮ ወበትዕግሥት ወረሳ ምድረ ሕያዋን አስተሐቀራሁ ጥበባቲሁ ለዝንቱ ዓለም ከመ ይባኣ ውስተ ጽርሑ ለመርዓዊ ምስሌሁ በሰላም ውስተ ከብካብ በዐቢይ ፍሥሓ። ቅዱሳት አንስት

አሠርገዋ ርእሶን በምግባረ ሠናይ ወተለዋ ድኅሬሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ:: ደናግለ ይሰመያ ነፍሳቲሆሙ ለጻድቃን)::

**ትርጓሜ፦** በጥበብ መብራት በፊቱ የሚሄዱ ዐሥሩ ደናግል ስማቸው እምነት፣ ተስፋ፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥትና ፍቅር ናቸው:: (#በግእዝ፦ ዐሥሮን ደናግል የሐውራ ቅድሜሁ በማኅቶተ ጥበብ አስማቲሆን ከመዝ አሚን ወተስፋ ፍሥሓ ወሰላም ትዕግሥት ወተፋቅሮ)::

## ነሐሴ 3 ዘሶፍያ

**ቅድስት ሶፍያ፦** ንግሥት ሶፍያ ስለእውነት ተጋድለን ዋጋችንንና ተስፋችንን እናገኝ ዘንድ ልጆቼ ውጡ እንጋደል አለች:: (#በግእዝ፦ ትቤ ሶፍያ ንግሥት ፃኡ ደቂቅየ ንትጋደል በእንተ ጽድቅ ንንሣእ ዕሴተነ ወንርከብ ተስፋነ)::

## ዘአንስት

**ቅዱሳት አንስት፦** ቅዱሳት ሴቶች በነላፊ ወርቅ፣ ጸጕርን በመሠራትና ዋጋው ብዙ በሆነ ልብስ ያይደለ [በመልካም ሥራ] ራሳቸውን አስጌጡ:: (#በግእዝ፦ ቅዱሳት አንስት አሠርገዋ ርእሶን አኮ በወርቅ ኀላፊ ወአኮ በጽፍሮ ሥእርቶን ኢ በአልባስ ዘዕፁብ ሤጡ)::

## ነሐሴ 10 ዘማኅበር

**ትርጓሜ፦** [እግዚአብሔር] ለእስራኤል ጠባቂ ሆናቸው:: እስራኤልም የተባልን [በእርሱ] ያመንን እኛ ነን:: (#በግእዝ፦ ኮኖሙ ኖላዊ[ዌ] ለእስራኤል እስራኤልሰ ንሕነ እለ አመነ)::

**ማኅበረ ጻድቃን፦** የቅዱሳን ማኅበርና ሰማዕት ሁሉ የሚያድን እርሱን [እግዚአብሔርን] ያመሰግናሉ:: ጽድቅህን በታላቅ ማኅበር ተናገርኩ:: ማኅበራችሁን በእውነት ቀድሱ:: (#በግእዝ፦ ኵሎሙ ማኅበረ ቅዱሳን ወሰማዕት ኪያሁ ይሴብሑ መድኅነ:: ዜኖኩ ጽድቀከ በማኅበር ዐቢይ:: ቀድሱ ማኅበረክሙ በጽድቅ)::

## ነሐሴ 13 ዘደብረ ታቦር

**አርእያነት፦** እንደ ሐዋርያት አስተምሩ:: እንደ መላእክት አመስግኑ:: አክሊሎችን ተቀዳጁ:: በማኅበር መካከል አጨብጭቡ [አመስግኑ]:: የደብረ ታቦርን በዓል አድርጉ [አክብሩ]:: (#በግእዝ፦ ከመ ሐዋርያት ስብኩ ወከመ መላእክት ወድሱ በአክሊላት ተቀጸሉ ወበማእከለ ማኅበር ጥፍሑ በዓለ ደብረ ታቦር ግበሩ)::

**ደብረ ታቦር፦** ዛሬ በዚህ ተራራ የአብ የጸጋው ክብር ታየ:: ደብረ ታቦር የእግዚአብሔር መቅደስ ነው:: ብርሃን የጋረደህ ደብረ ታቦር ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን:: [የደብረ ታቦር] ውበቱ ከተራሮች ሁሉ ያምራል:: (#በግእዝ፦ ዮም በዝንቱ ደብር አስተርአየ ብዕለ ጸጋሁ ለአብ:: ደብረ

ታቦር መቅደሱ ለእግዚአብሔር፡፡ ሰላም ለከ ኦ ደብረ ታቦር ዘከለሎ ብርሃን ይሤኒ ላሕዩ እምኵሉ አድባር)፡፡

## ❀ነሐሴ 16 ዘማርያም❀

**ነገረ ማርያም፦** እመቤቴ እልሻለሁ የጌታዬ እናትም እልሻለሁ፡፡ የአብ የእውነት ቃሉ ከአንቺ ተወለደ፡፡ የጳውሎስ ፍጽምት ድንኳን የልጇ አገልጋይ ዳዊት በመሰንቆ እየዘመረ[ላት] ከሚያረጀው ዓለም ወደማያረጀው ዓለም ሄደች፡፡ ማርያም ሆይ ልጅሽ ወደ ሕይወትና የክብር መንግሥት ጠራሽ፡፡ ስለ የዋህነቷ ርግቤ ይላታል፡፡ ስለዝምታዋ መልካሟ ይላታል፡፡ በደል የሌለባት ነጭ ፀምር ናት፡፡ እመቤቴ የምስጢር ደጅ፣ የምትናገር ተራራ፣ ጠልን የተቀበለችው ንጽሕት ፀምር ናት፡፡ ማርያም አዲስ መርከብ የኢሳይያስ የተጠማች ምድር ናት፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ናት፡፡ ማርያም የአዳም መድኀኒቱ ናት፡፡ አፏ እንደ እንኮይ ነው ማለት አንደበቷ መልካም ነው፡፡ ዓይኖቿ የርግብ ናቸው፡፡ መናን የተሸከመች ፈጣን ደመና ማርያም ናት፡፡ መለኮትና ፍቅር በእርሷ ላይ ያደረ የወልድ ሽልማት [ጌጥ] ናት፡፡ ማርያም በምድርና በሰማይ ያለች አዳራሽ ናት፡፡ ከሩቅ ሀገር የምትታይ የክርስቶስ በግ ናት፡፡ እርሱ ተሸክሟት በማሕፀኗ ተሸከመችው፡፡ በሁሉ አንደበት የምትመሰገኚ ማርያም ሆይ ንዕድ ክብርት ነሽ፡፡ ኪሩቤል ያመሰግኑሻል ሱራፌልም ያመሰግኑሻል፡፡ መላእክት በየነገዳቸው ይገዙልሻል፡፡ የእግዚአብሔር ሀገር ንጽሕት አዳራሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ፡፡ አንቺ መንፈሳዊት ሀገር ነሽ፡፡ ፍሬዋ ለማየት ያማረ በፈሳሽ ውሃ አጠገብ የበቀለች ዕፅ ናት፡፡ ማርያም ከፍጥረት ትበልጣለች ትከብራለች፡፡ (#በግእዝ፦ እግዝእትየ እብለኪ ወእሙ ለእግዚእየ እብለኪ፡፡ ወተወልደ እምኔኪ ቃለ ጽድቁ ለአብ፡፡ ደብተራ ፍጽምት ዘጳውሊ ፈለሰት እምዘይበሊ ኀበ ኢይበሊ በመሰንቆሁ እንዘ የኀሊ ዳዊት አቡሁ ዘወልዳ ወዓሊ፡፡ ኦ ማርያም ወልድኪ ይጼውዐኪ ውስተ ሕይወት ወመንግሥተ ክብር፡፡ ርግብየ ይቤላ በእንተ የዋህታ ወሠናይት በእንተ አርምሞታ፡፡ ፀምር ጸዓዳ እንተ አልባቲ ርስሐት፡፡ አንቀጸ ምስጢር እግዝእትየ ነባቢት ደብር እንተ ተወክፈቶ ለጠል ንጽሕት ፀምር፡፡ ማርያም ሐመር ሐዳስ ምድር ጽምዕት ዘኢሳይያስ፡፡ ማኅደሩ ይእቲ ለመንፈስ ቅዱስ፡፡ ማርያም መድኀኒቱ ለአዳም፡፡ አፉሃ ከመ ኮል አዕይንታ ዘርግብ፡፡ ደመና ቀሊል ዘትጸውር መና ማርያም ይእቲ፡፡ ትርሲተ ወልድ መለኮት ወፍቅር ኀደረ ላዕሌሃ፡፡ ማርያም ታዕካ በምድር ወታዕካ በሰማያት፡፡ እንተ ክርስቶስ በግዕት እንተ ታስተርኢ እምርጉቅ ብሔር፡፡ ፆረቶ በከርሣ እንዘ ውእቱ ይፀውራ፡፡ ብፅዕት አንቲ ማርያም ውድስት በአፈ ኵሉ ኪሩቤል ይሴብሑኪ ወሱራፌል ይቄድሱኪ፡፡ መላእክት በበነገዶሙ ይትቀነዩ ለኪ፡፡ ጽርሕ ንጽሕት ማርያም ተፈሥሒ ሀገረ እግዚአብሔር፡፡ አንቲ ውእቱ መንፈሳዊት ሀገር፡፡ ዕፅ ዘበቈለት ኀበ ሙሐዘ ማይ ፍሬሃ ሠናይ አዳም ለርእይ፡፡ ማርያምሰ ተዐቢ ወትከብር እምኵሉ ፍጥረት)፡፡

**ነገረ ክርስቶስ፦** እግዚአብሔር ድንግልን ከእርሷ ሰው የሆንኩት እኔ ራሴ ፈጠርኳት አለ፡፡ ቃል በእርሷ በተሞሸረ በቅድስት ማርያም በዓል መልካሙ ዘመን ደረሰ፡፡ (#በግእዝ፦ ለልየ በእዴየ ለሐኵዋ ለድንግል እንተ እምኔሃ ተሰባእኩ ይቤ እግዚአብሔር፡፡ በጽሐ ሠናይ ወአልጸቀ ዘመን በበዓላ ለቅድስት ማርያም እንተ በላዕሌሃ ተመርዐወ ቃል)፡፡

**ትርጓሜ፦** የበቀለች የአሮን በትር ናት። ይህቺ በትር የቅድስት ማርያም ምሳሌ ናት። (#በግእዝ፦ በትረ አሮን እንተ ሠረፀት ይእቲ በትር አምሳለ ማርያም ቅድስት ይእቲ)።

## ❦ነሐሴ 24 ዘተክለ ሃይማኖት❦

**ተክለ ሃይማኖት፦** አባታችን መምህራችን ከብዙዎች የተመረጠ ነው። ተክለ ሃይማኖት የጋዲ የወይን ቦታ ነው። ገዳሙ ደብረ ሊባኖስ ተክለሃይማኖትን በመከራው ብዛት መጠን ታመሰግነዋለች። (#በግእዝ፦ አባ አቡነ አቡነ መምህርነ እምአዕላፍ ኅሩይ። ተክለ ሃይማኖት አፀደ ወይን ዘጋዲ። ትዌድሶ ደብረ ሊባኖስ ገዳሙ ለተክለ ሃይማኖት ጻድቅ መጠነ ብዝኀ ሕማሙ)።

## ✽ነሐሴ 28 ዘአብርሃም፣ ዘይስሐቅ✽

**መልካም ሥራ፦** ራስህን ከፍ ከፍ አታድርግ። ትዕቢት ባለበት ውርደት አለና። በእውነት ያለ ትሕትና ይበልጣል። (#በግእዝ፦ ኢታዕቢ ርእሰከ እስመ ኀበ ሀሎ ትዕቢት ህየ ሀሎ ኀሣር። ይኄይስ ትሕትና ዘበጽድቅ)።

**ይስሐቅ፦** አብርሃም ይስሐቅ ልጁን ሊሠዋው ወሰደው። [እግዚአብሔር ግን] ቤዛ የሚሆነው በግን አወረደለት። ክርስቶስ ከእርሱ ስለሚወለድ ይስሐቅ ያዕቆብን ባረከው። (#በግእዝ፦ አብርሃም ወሰዶ ለይስሐቅ ወልዱ ከመ ይሡዖ አውረደ ሎቱ ቤዛሁ በግዐ። ባረኮ [ይስሐቅ ለያዕቆብ] በእንተ ዘሀሎ እምላዕሌሁ ይትወለድ ክርስቶስ)።

## ❦ነሐሴ 30 ዘእንድርያስ❦

**እንድርያስ፦** መላእክት እንድርያስን ተሸክመው ሰውን ከሚበ*ሉ ሰዎች ሀገር አደረሱት። ማን ነህ ስምህስ ማን ነው በማንስ ታመልካላችሁ አሉት። እንድርያስም እኔስ ብቻውን ታላላቅ ብርሃናትን የሠራ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስን አመልከዋለሁ አላቸው። (#በግእዝ፦ መላእክት ፆርዎ ለእንድርያስ ወአብጽሕዎ ሀገረ በላዕተ ሰብእ ወይቤልዎ መኑ አንተ ወመኑ ስምከ ወበመኑ ታመልክ። አውሥአ እንድርያስ ወይቤሎሙ አንሰ አመልኮ ለእግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘገብረ ብርሃናተ ዐበይተ ባሕቲቱ)።

## ✝ጳጕሜን 5 ዘሩፋኤል✝

**ቅዱስ ሩፋኤል፦** ዓውደ ዓመት ይባረክ ዘንድ መልአኩ ሩፋኤል ሆይ ወደ አምላክ ጸልይልን። ለነፍሳት የሚቆሙ ሊቃናት፣ ዑራኤል፣ ሩፋኤል ከልዑል ዘንድ ለይቅርታ ይላካሉ። ሩፋኤል ካህን ነው። የብርሃን መልአክ ሩፋኤል የትጉሃን አእላፍ አለቃ ነው። (#በግእዝ፦ ጸሊ ኀበ አምላክ ሩፋኤል መልአክ ዐውደ ዓመት ከመ ይትባረክ። ቀዋምያን ለነፍሳት እሙንቱ ሊቃናት ዑራኤል ወሩፋኤል ይትፌነው ለሣህል እምኀበ ልዑል። ሩፋኤል ካህን ሩፋኤል መልአከ ብርሃን አማን ሊቀ አዕላፍ ትጉሃን)።

## ☘ዘክረምት☘

**እግዚአብሔር፦** የበልግ ዝናምን ይሰጣችሁ ዘንድ እግዚአብሔርን ለምኑት። በረከትን ለእናንተ ያዘንባል። ክረምትን በየዓመቱ የምታስገባ አቤቱ ዕውቀትን ስጠን። ሰማይን በደመና የሚጋርድ ለሥጋ ሁሉ ምግብን የሚሰጥ ነው። በምድር ሁሉ ዝናምን ያወርዱ ዘንድ ደመናትን የሚያዝዛቸው ነው። ለቸሮች ቸር ለይቅር ባዮች ይቅር ባይ የሆነ [እግዚአብሔር] በምድር ላይ ዝናምን ያወርዳል። [አቤቱ አንተ] ለነገሥታት ሰላምን ትሰጣለህ ለአብያተ ክርስቲያናትም ጸጥታን ትሰጣለህ። በኖኅ ጸሎት ይቅር በለን። አንተ ሕይወትን የፈጠርክ በረከትን የምትሰጥ ነህ። አንተ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ነህ። ከፍጥረት ሁሉ ሰውን ከፍ ከፍ ያደረግህ ከዕለታት ሁሉ ሰንበትን ያከበርክ አንተ ነህ። ወደ ምድረ በዳ ብሄድም ኀይሌ እግዚአብሔር ነው። ብወድቅና ብፍገመገም በመስቀልህ እነሣለሁ። (#በግእዝ፦ ሰአልዎ ለእግዚአብሔር የሀብክሙ ዝናመ ጸደይ። ያዝንም ለክሙ በረከተ። ዘአንተ ታርኁ ክረምተ በበዓመት ሀበነ እግዚኦ አእምሮ። ዘይገለብቦ ለሰማይ በደመና ዘይሁብ ሲሳየ ለኵሉ ዘሥጋ። ዘይኤዝዞሙ ለደመናት ያውርዱ ዝናመ ውስተ ኵሉ ምድር። ኄር ለኄራን መሓሪ ለመሓርያን ያወርድ ዝናመ በዲበ ምድር። ትሁብ ሰላመ ለነገሥት ወኅድዐተ ለአብያተ ክርስቲያናት። በጸሎቱ ለኖኅ ተሣሀለነ። አንተ ውእቱ ገባሬ ሕይወት ወሃቤ በረከት። አንተ ኬንያሁ ለኵሉ ፍጥረት። እምኵሉ ፍጥረት ሰብአ ዘአዕበይከ ወእምኵሉ ዕለት ሰንበተ ዘአክበርከ። እመኒ ሖርኩ ውስተ በድው ኀይልየ እግዚአብሔር እመኒ ወደቁ ወተንተንኩ እትነሣእ በመስቀልከ)።

**ክረምት፦** የዝናም ኮቴው ተሰማ። ዝናም በሚዘንብ ጊዜ የተራቡት ይጠግባሉ። ዝናም በሚዘንብ ጊዜ ችግረኞች ደስ ይላቸዋል። (#በግእዝ፦ ደምፀ እገሪሁ ለዝናም። ሶበ ይዘንም ዝናም ይጸግቡ ርኁባን። ሶበ ይዘንም ዝናም ይትፌሥሑ ነዳያን)።

**ምጽአት፦** ወልድ ከሰማይ ኀይላት ጋር በሚያስደነግጥ ግርማ በመጣ ጊዜ። የዕለታት ሁሉ በኵር የሆነች እሑድ ትሰለጥናለች። ያን ጊዜ ጨረቃ የለም፣ ፀሐይም የለም፣ ክረምት የለም በጋም የለም። (#በግእዝ፦ አመ ይመጽእ ወልድ በግርማ መደንግፅ ምስለ ኀይለ ሰማያት ትሰፍን እሑድ ርእሰ ኵሎን ዕለታት። አሜሃ አልቦ ወርኅ ኢ ፀሐይ ኢ ክረምት ወኢ ሐጋይ)።

## 🍎ዘዘወትር🍎

**እግዚአብሔር፦** ክረምትን ለምድር ያዘጋጃል። በተራሮች ላይም ሣርን ያበቅላል። ደመናትም ቃሉን ይሰማሉ። [አቤቱ] አንተ ነዳያንንና ባዕለ ጸጎችን ትመግባቸዋለህ። ለሙት ልጆች አባት ነህ። ስለችግረኞች ሕዝብ ብለህ የምድርን ፍሬን ባርክ ለዘርና ለመከር አድርስ። የክርስቶስ ጥበቡ ድንቅ፣ ነገሩ መልካም፣ ቃሉ ያማረ ነው። ውሃን በደመና ሲያቁር ደመናው አይቀደድም። እግዚአብሔር ምክሬ እንደ ምክራችሁ ሐሳቤ እንደ ሐሳባችሁ አይደለም አለ። በምድር ላይ ዝናምን የማዘንብ በተራሮች ላይ ሣርን የማበቅል እኔ ነኝ። ለእንስሳት ምግባቸውን እሰጣቸዋለሁ። ይህንን ሁሉ እጄ ፈጥሮታልና። ከአብ በስተቀር የወልድን ሐሳብ የሚያውቅ

የለም። ከወልድ በቀርም የአብን ሐሳብ የሚያውቅ የለም። አቤቱ አንተ የማትጎድል መዝገብ ነህ። አንተ ክብራችንና ጌጣችን ነህ። አንተ የመድኀኒታችን አክሊል ነህ። (#በግእዝ፦ ያስተዴሉ ክረምተ ለምድር ወያበቊል ሣዕረ ውስተ አድባር። እስመ ደመናትኒ ይሰምዑ ቃሎ። አንተ ትሴስዮሙ ለነዳይ ወለባዕላይ ለፅጓለ ማውታ አብ። ባርክ ፍሬሃ ለምድር አብጽሕ ለዘርዕ ወለማዕረር በእንተ ነዳያን ሕዝብከ። ጥዑም ቃሉ ወሠናይ ነገሩ መንክር ጥበቢሁ ለክርስቶስ። ዘየዐቍሮ ለማይ በደመና ወኢይሰጠጥ ደመናሁ። ይቤ እግዚአብሔር ኢኮነ ምክርየ ከመ ምክርክሙ ወኢኮነ ኀሊናየ ከመ ኀሊናክሙ። አነ ውእቱ ዘአወርድ ዝናመ ዲበ ምድር ወአበቊል ሣዕረ ውስተ አድባር እሁቦሙ ሲሳዮሙ ለእንስሳ እስመ እደውየ ገብሮ ለዝንቱ ኵሉ። አልቦ ዘየአምር ኀሊናሁ ለወልድ ዘእንበለ አብ ወአልቦ ዘየአምር ኀሊናሁ ለአብ ዘእንበለ ወልድ። አንተ ውእቱ ዘኢይቀብል መዝገብ። አንተ ውእቱ ክብርነ ወትርሲትነ። አንተ ውእቱ አክሊለ መድኀኒትነ)።

**ምስጋና፦** በየዘመኑ እንዴት እንደሠራ አይቼ እግዚአብሔርን እያመሰገንሁ ወደ ገዳም ወጣሁ። (#በግእዝ፦ ወፃእኩ ውስተ ገዳም እንዘ እሴብሖ ለእግዚአብሔር ርእይየ ኵሎ ዘከመ ገብረ በበመዋዕሊሁ)።

**ተፈጥሮ፦** ደመናት በእውነት በአቅማቸው ውሃዎችን ያካፋሉ። (#በግእዝ፦ ይነፈንፋ ጽድቀ ደመናት ማያተ በአቅሞሙ)።

## 🍒ዘተረስዐ ዘልደት ሰንበት🍒

**ነገረ ማርያም፦** እግዚአብሔር ማርያምን ዘመንሽ ዘመኔ ነው መጠንሽ መጠኔ ነው አላት። (#በግእዝ፦ ወይቤላ እግዚአብሔር ለማርያም አዝማንየ አዝማንኪ አምጣንየ አምጣንኪ)።